# ገመና

## (ረጅም ልብወለድ)

**ሰሎሞን ሹምዬ መኮንን**

አዲስ አበባ ጥር 1999

© 1999 ሰሎሞን ሹምዬ
የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

ሰሎሞን ሹምዬ
ስልክ:- 251-11-553 0349
251-11-114 0613
251-19-122 4741
ፖስታ :- 60015
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**
E-mail :- gebeyanu@ethionet.et
gebeyanu@yahoo.com

**ቴክስት ሌይአውት፡- ፊልሞን ፕሬስ**
**E-mail: filmonat@yahoo.com**

# ገመና

በዚህ መፅሐፍ
አናቴ
ወ/ሮ ገበያነሽ ወርቅነህ
ትታሰብበት
፣



# የማርያም ወዳጅ ሄደች

ሄደች የማርያም ወዳጅ
ጓዜን ሳትል ልጅ ውላጅ::
ሄደች እሙ-እኔ ትሁቷ
ድንግልን ብላ በዕለቷ::

ፊትማ ሳለች በቁሟ
በውኗም ይሁን በህልሟ
እኔ ነበርኩኝ ዓለሟ::
እንዲ ሳይያዝ ልሳኗ
ወሏ ሳይርቀኝ ጠረኗ::
ነበረች የኔ መመኪያ
የስሱ ነፍሴ መጠጊያ::
ህይወት ምሰሰው አዝምሞ
ዓለም ቢሸሽኝ አድሞ
ቢውጠኝ ቀኑ ጨልሞ::
በሷ እቆማለሁ ፀንቼ
ችግርን በድል ረትቼ::
ስጨቃ ጋሻ ምክቴ
ነበረች ለኔ ጉልበቴ::

ሄደች የማርያም ወዳጅ
ጓዜን ሳትል ልጅ ውላጅ::

ወላዲት አምላክ በቀኗ
በጎንደር ንግስ ስልጣኗ
ጠራቻት ከኔ ለይታ
እሷም እንደሰው አድልታ::

አልከሳት ለሹም ለዳኛ
አይደለች እሷ ዓለመኛ::
ሰማየ ሰማይ ደርሼ
ብችል ላቆማት ከስሼ፣
እዚያ ዳኝነት የልጇ
መች ያደርሰኛል ከደጇ::

ሄደች የማርያም ወዳጅ
ዞራም አላየች ልጅ ውላጅ::
ይብላኝ እንጂ እኔ፣ ለራሴ
ለማረበሸው መንፈሴ፣
ለእርሷማ አለቻት ወዳጇ
ሁሉ በጇ ነው በደጇ::
ሰምሮልኝ ልፋት ጥረቴ
ደስታ ሲያሰክረው ስሜቴ
ወደ ቤት ነበር በርሬ
ልሞገስ ለሷ ነግሬ::

'እሰይ አበጀህ' –'ምትለኝ
በጉያዋ አቅፋ –'ምትስመኝ
ሽልማት ነበር ሹመቴ
ወኔ ለቀጣይ ጥረቴ::
ዓለምን እንኳ ብመራ
ሐውልቴ በእንቁ ቢሠራ
እንደርሷ ግንባር ፈገግታ
የለውም ልቤ ደስታ::

ለካስ ደስታም በሷ ነው
የልቤ ዝሊያ ዳንኪራው::
ምን ቀረኝ ለኔ ምን ተወች?
ሳቄንም ይዛው ሄዷለች::

ባዶ ነው ውስጤ ብቸኛ
አጋር የሌለው ቤተኛ::

ካለም ቢዋህድ አካሌ
ሩቅ ነው የውስጥ አመሌ::
ህልሜን አልሞ እሚፈታ
የሚመግበኝ ፈገግታ::
ሳጠፋ ለኔ፣ ተጉድቶ
ሳለማ በኔ፣ ስም ኮርቶ፣
አይዞህ የሚለኝ ስከፋ
ሳዝን ከጉኔ -'ማይጠፋ
ከቶስ እንደሷ ማን አለ?
ዓለም በወረት አይደለ::
ከቶስ እንደሷ ማን አለ?
ዓለም በይምሰል አይደለ::

ሄደች የማርያም ወዳጅ
ከቁግዲህ፣
አላገኛትም ባማላጅ::
ጠሪዋ አይደለች እራስዋ
ማርያም፣
የጭንቅ አማላጅትዋ::

ህዳር 21 ቀን 1993
- ለገበያነሽ ወርቅነህ

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

Pathfinder
INTERNATIONAL

RH/FP & HIV/AIDS
PROGRAMS

## Acknowledgement

This book was made possible through support provided by Pathfinder International and U.S. Agency for International Development, under the terms of Award No. ET 825. The opinions expressed herein are those of the author and do not necessarily reflect the views of Pathfinder International or the U.S Agency for International Development.

## አመሰግናለሁ!

ዛሬ በህይወት ባትኖሪም ይህን ድርሰት ሳዘጋጅ ከጐኔ ነበርሽና ስማይተመን ምክርና ማበረታቻሽ ውድ እናቴ:-

ወ/ሮ ገበያነሽ ወርቅነህ

ጊዜያችሁን ሰውታችሁ ረቂቁን በማንበብ ገንቢ አስተያየትና ማበረታቻ የሰጣችሁኝ:-

አቶ ጌታነህ አንተነህ
አቶ አማረ በዳዳ
ዶ/ር ሉክማን ዩሱፍ
ወ/ሮ አታፈራሁ ወርቅነህ

በኮምፒውተርና በታይፕ ከመጀመሪያው ረቂቅ ጀምሮ በመፃፍና በማረም ቀና ትብብር ያደረጋችሁልኝ:-

ወ/ት የሺ እመቤት ጣሰው
ወ/ት ውበት ዓለሙ
ወ/ት አዲስዓለም ፍቅሬ

ሁላችሁንም ከልብ **አ መ ሰ ግ ና ለ ሁ!**

## እንደ መንደርደሪያ


ጡሃ ሲወሰድ እያሳሳቀ'እንዲሉ ጥበብም ፈገግ እያለች እንደምታንበረክክ ዘማዊት ናት:: ሲርቋት ጠቅሳ ሲቀርቧት የምትናከስ:: ምን ቢሸሹ ልክፍቷ መልሶ መልሶ ከሥሯ የሚጥል::

እንደ አጀማመሬ እስከ አሁን በርካታ ድርሰቶችን ስመፃፍ አቅሙ ነበረኝ:: ይሁን እንጂ በኛ አገር በድርሰት ገቢ መኖር ከባድ እንደሆነ በመገንዘቤ አቅጣጫዬን ስመቀየር ተገደድኩ:: እኔ መቼም ለጥበብ ሲሉ መራብ አይገባኝም:: ጥበብ ያለው በህይወት ነው:: ህይወት ደግሞ መኖር ነው:: የመኖርን ጥበብ ለሌሎች ሲያካፍል የሚነሳ 'ጠቢብ' ነኝ ባይ በቅድሚያ ራሱ መኖር መቻል አለበት:: መኖር ሲባል ደግሞ ራስን ከመመገብ ይጀምራል:: የእኔም ከጥበቡ ዓለም ጠፍቶ መሰንበት እንግዲህ ከዚህ ፍልስፍና የመነጨ ነው:: እውቀትን ፍለጋ፤ እናም እንጀራ ፍለጋ:: የሁለቱም ረሃብ ጥበብን ያመነምናል ባይ ነኝ::

እነሆ ዛሬ ጊዜው ደረሰና እንጀራዬን ሳድን እጄ ላይ የሰነበተ ድርሰቴን ለአንባቢያን አበረከትኩ:: ታዲያ እኩርፌ ሳይሆን የጥበብን ፈገግታ በፀጋ ተቀብዬ፤ ልንበረከክላት ሳይሆን ደግሜ ደጋግሜ ላንበረክካት ለራሴ ቃል ገብቼ ነው::

ይህን ድርሰት ለመፃፍ ከሁለት ዓመት በላይ ወስዶብኛል:: ከዚህ ጊዜ አብላጫውን የፈጀው በሥነ-ፅንስና ሥነ-ማህፀን ዙሪያ ዜሮ የነበረ እውቀቴን ለማዳበር ያደረኩት ንባብ ነው:: የተጀመረው በ1982 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መሐል ገበያ ቅርንጫፍ ሠራተኛ እያለሁ ሲሆን በሚኖረኝ ፋታ ሁሉ ካውንተር ተከልዬ እፅፍ ነበር:: እንደኔ ላለ ዝቅተኛ ገቢ ካለው ቤተሰብ የወጣ ፀሐፊ ከዚያ የተሻለ ምቹ ሥፍራ አልነበረም:: የሐምሌ 19 መናፈሻና የአራዳው

ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንም ባስውስታዎቼ ናው:: የመጨረሻውን ስድስት ወር ግን አንዲት ክፍል ቤት ተከራይቼ ነው የጨረስኩት:: ቀላል አንከራተተኝ! አስራ ዘጠኝ እና ሃያ ዓመት ዕድሜ ላይ ሆኜ የፃፍኩትን ድርሰት ዛሬ ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ ያነበብኩት ፍፁም በሌላ ሰው ዓይን ነው:: የሚስተካከል ነገር ፍለጋ ቢሆንም አንዲት የቃል ሰንጥር ማውጣት አልቻልኩም:: ይልቁንም በዚያን ጊዜ በነበረኝ አቅም አየተገረምኩ የመጨረሻው ገፅ ደረስኩ:: ለስቼ ይሆን? ፍርዱን ለአንባቢያን:: መልካም ቆይታ ከ'ገመና' ጋር::



ሰሎሞን ሹምዬ መኮንን
ጥር 1999



# 1

"አሎ? አሎ! አሎ?" አለ ከውጭ ተንደርድሮ እንደገባ የስልኩን እጀታ አንስቶ ጭቅቅታም ፊቱን ቋጠር ፈታ እያደረገ:: ወዲያው ደግሞ የሚፈልገውን ምላሽ ወይንም መረጃ እንዳገኘ "አሎ" ባይ ስልኩን መጉረስ እስኪቀረው ወደ አፉ በማስጠጋት፣ "አዎ! . . . አዎ!. . . አዎ!. . . አዎ!" አለና የወዲያኛውን ተናጋሪ በጽሞና እንደሚያደምጥ ንግግሩን አቆመ:: ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ ከቆየ በኋላ፣ "እ! ?..... ጉድ!..... አሎ! እንደገና! አሎ! እንደገና! አሎ! አ...ሎ!" አለ በንዴት ድምጹን ከፍ አድርጎ::

"ቺድ!" የስልኩን እጀታ አሽቀነጠረው:: "የራሷ ጉዳይ!" እያለ ወጣ::

"ዛሬ ይሄ ስልክ አልቆለታላ!" አሉ ወ/ሮ ብዙነሽ፣ የመጨረሻ ድምጹን ሰምተው ከኩሽና እየተንደረደሩ ሲመጡ እርሱ ወጥቶ ሲሄድ ተመልክተው:: አልፎ አልፎ አለሰዓቱ ሳያስቡት ከች ማለቱ የተለመደ ቢሆንም በዛሬው አጋጣሚ እንዳዲስ ተደናግጠዋል::

"ዳርምየለሽ! ዳርዋ! ውይ የለችም እንዴ?" አሉ እየተጣሩ ሲገቡ የክፍሉ ባዶ መሆን አሳፍሯቸው:: - ለብቻ ማውራታቸው::

የስልኩን እጀታ ከማስቀመጫው ትንሽ ጠረጴዛ ሥር ተንዘልዝሎ ሲያገኙ እንደልማዱ ወርውሮት መሄዱን አወቁ::

"የት ሄዳ ነው ልጄ! እንዲህ ስልኩን የተጫወተበት" አሉ ለራሳቸው:: እርሳቸው ወደ ኩሽና ሲሄዱ በፊት ለፊት በር ስትገባ አይተዋት በርቀት ሰላም ብለዋታል::

የስልኩን ደህንነት በጆሮአቸው ካረጋገጡ በኋላ የፊት ለፊቱን ዋና በር ቀረቀሩና ገርበብ ያለውን የመኝታ ቤት መዝጊያ ገፋ አድርገው ወደ ውስጥ አንገታቸውን አሰገጉ:: ዳርምየለሽ አልጋቸው ላይ ተዘርግታለች:: በሁኔታዋ ተደናግጠው በሩን እስከመጨረሻው ከፈቱና ገቡ::

"ዳርዋ!" አሉ ከአልጋው ጠርዝ እየተቀመጡ:: እጃቸውን ትከሻዋ ላይ

አሳርፈው አንገቷን ወደ እርሳቸው አቅጣጫ መለስ ለማድረግ ሲሞክሩ፣ "አቤ.. .ት!" አለች ገና ያልበረደ ልቅሶዋን እየተናነቀች። በእንባ የራሰ ፊቷን በሁለት እጆቿ ሸፈነችው።

እርሳቸው ልብ አላሏትም እንጂ ከውጭ ስትመጣም ገጽታዋ እንደተለመደው አልነበረም። እንደ ቢጋ ከዋክብት ጥርት ያሉት ትናንሽ ዓይኖቿ ይረጩት የነበረው የጭብት ብርሃን ደመና እንደጋረዳት ፀሐይ ቅዝዝ ብሎ፣ ከዓይኖቿ ጉድጓድ አፋፍ ላይ በተፈጥሮ ቅምቅም ብለው ከዓይኖቿ የሚወረወረውን የውበት ጮራ የሚያደምቁና የሚያጋኑት ቀናድቧ ተኮማትረው እየተርገበገቡ ነው የመጣችው። ወ/ሮ ብዙ ግን የተቀላቢዎቻቸው ራት ሰዓት በመቃረቡ ጥድፊያ ላይ ስለነበሩ ልብ አላሏትም።

ዳርምየለሽም እናቷ ምን እንደሆነች ሳይጠይቋትና የፊቷን ለውጥ ሳይረዱ ወደ ሥራቸው በመሄዳቸው ተደስታ፣ እንደ ገባች ወደ እናቷ መኝታ ቤት ነው የተንደረደረችው። ደስታ፣ ከማልቀስ ፍላጐት፣ በልብ ውስጥ የታመቀና ሲጋና ነብስን ወጥሮ ያስጨነቀን ብርቱ ሀዘን ያለከልካይ ያለገላጋይ በእንባ ለመተንፈስ ከመቻኮል፣ ለዚህም አመቺ ጊዜና ቦታ ከማግኘት የመነጨ ደስታ።

የተደገፈችው ትራስ እስኪርስ፣ ዓይኖቿ ደፍርሰው የተፋቀ እንሶስላ እስኪመስሉ፣ የንፍጥ ዋንጫዋ ወልቆ አፍንጫዋ ደም እስኪመስል ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። ሆኖም የለቅሶ ምክንያትዋ ከሚወጣላት ይልቅ ከዕለቱ ገጠመኟ ባሻገር በነብስ ዐወቅ እድሜዋ ልክ የቆዩና እንደዋዛ የረሳቻቸው ነገሮች ሁሉ በሃሳቧ እየተሳሳቡና እየተያያዙ የደረሰባትን የስሜት ቃጠሎ ደግመው ደግመው በመጫር ረመጡን አፈሰሱባት። እንዲያ መፍትሔ አድርጋ ስትሮጥ የመጣችበት ለብቻ የማልቀስ ጉጉት ሲቃ በሲቃ አደረጋት እንጂ ብሶቷን አላስወጣላትም።

"ምን ሆነሻል ልጄ? ምንድነው እንዲህ የሚያስለቅስሽ?" አሉ በእንባ የረጠበውን ትራስና እርሷ ልትሸፍነው ብትሞክርም ጉም የለበሰ ፊቷን ተመልክተው።

"ምንም አልሆንኩም" አለች አነጋገሯ የለቅሶ መሆኑ እንዳይታወቅባት እየሞከረች።

"እንዴት ምንም አልሆንኩም? ይኼ ታዲያ ምንድነው?" አሉ የራሰውን ትራስ ጠቆም አድርገው ወደ ፊቷ በጥያቄ እያስተዋሉ።

"አመመሽ ወይስ አመነገድ ምን አጋጠመሽ?"

"አላመመኝም።"

"ታዲያ ምን ሆነሻል?"

"ምንም" አለች የዓይኖቿ ሽፋሽፍት ላይና ታች እየተያያዙ።

"እንዴት ምንም? ምንም ያልሆነ ሰው ያለቅሳል?" አሉ ጭንቅ



ብሏቸው።

"ዝም ብዬ ነው።"

"ዝም ብሎ እንዴት ይለቀሳል! ከሰው ተጣላሽ?"

"አልተጣላሁም"

"ነው ወይስ የዋልሽበት ሥራ ፍለጋ አልቀናሽም?"

"በርሱ አይደለም"

"ታዲያ ምን ጉደለብሽ? የምትፈልጊውና አቅሜ ሲፈቅድ ያልተሟላልሽ ነገር አለ?"

"የለም"

"እኔኮ ግራ ገባኝ! እሺ ምንድነው የሚያስለቅስሽ?"

"ምንም አልሆንኩም አልኩሽኮ!" አለች ባጭሩ እንዲለቋት አነጋገሯ መረር ብሎ።

"ምንም አልሆንሽም?" አሉ ልትነግራቸው እንዳልፈለገች ሲረዱ ቅሬታ ባዘለ ገጽታና አተያይ።

"ጥሩ፣ ከእናት ተደብቆ የሚለቀስበትና የማይነገር ብሶት ካለ ጥሩ ነው። እኔማ እናት ነኝ ብዬ እንጂ ልትነግሪኝ ላለመፈለግሽኮ መጀመሪያም ተደብቀሽ ማልቀስሽ በቂ ነበር" አሉ ወ/ሮ ብዙ ከልባቸው አዝነው ትተዋት እየተነሱ።

"እንደሱ እኮ አይደለም እማዬ! ቆይ ነይ እስቲ" አለች እናቷ ስላዘኑባት ተደናግጣ። ምን ብላ እንደምትነግራቸው ባታውቅም የምትወዳቸው እናቷ ገጽታ ሲጠቁርና ቅሬታ ሲያጠላበት ማየቱ የበለጠ ረብሿታል።

"ምን እሰራልሻለሁ! ደብቀሽኛል፣ ብቻሽን አልቅሺ።"

"እነግርሻለሁ እማ፣ እነግርሻለሁ"

"በይ ንገሪኝ እሺ! ምንድነው እርሱ እንዲህ የሚያስለቅስሽ?" አሉ ምልስ ብለው ከጐኗ እየተቀመጡ።

"ቆይ!" አለች ራዕይ እንደምትመለከት ሁሉ ወደፊቷ ትክ ብላ በማፍጠጥ ወደ ቤቷ ያበረራትን ብሶት ወደኋላ አጠንጥና ያለ ስክሪን በሃሳብ እያስተዋለች።

ትኩረቷ የተጋባባቸው እናት እርሷ ወዳፈጠጠችበት አቅጣጫ ግድግዳው ላይ ዐይናቸውን ተክለው በጉጉት ጠበቋት። ከምትናገር ይልቅ በውስጧ ተመስጣ ቀረች። መለስ ብለው ገጽታዋን ሲቃኙ ጉም እንዳረገዘ ሰማይ ጭግግ፣ ከብድ ብሏል።

"ንገሪኝ እንጂ ዳርዬ ምነው ተከዝሽ?" አሉ ሀዘንም ተግሳጽም በቀላቀለ አነጋገር።

"እሺ፣ እማዬ እንዴት ብዬ ልንገርሽ" አለችና ከዚያ ሁሉ ለቅሶ በኋላ ዓይኖቿ እንደ አዲስ የቋጠሩትን ዕንባ ዘረገፈችው። በመንገርና ባለመንገር መሐል ተወጥራ በጭንቀት ተንፈቀፈቀች። ለመንገር ድፍረቷን ተጠራጠረች። ላለመንገር ደግሞ የእናቷን ቅያሜ ፈራች። የግድ ግን አንድ ነገር ማለት እንዳለባት ተሰማት።

"እሺ ልንገርሽ" አለች ሩህሩህ የእናት ዓይናቸው እንባ አቅርሮ በጉጉት ቃሏን ወደሚጠብቁት እናቷ ትኩረቷን መልሳ፣ እንባዋን እየጠራረገችና ራሷን ለማረጋጋት እየሞከረች።

"በይ ንገሪኝ እስቲ የኔ ልጅ፣ እንዲህ ያንሰፈሰፈሽ ምንድነው? እኔ ስፍስፍ ልበልና ከእናት የሚደበቅ ምን ነገር አለ?"

"ስዓቱ. . ." አለችና ገጽታቸውን በጥያቄ ቃኘች።

"የምን ስዓት ልጄ!"

"የስጠሽኝ። እጄ ላይ የነበረው"

"ምን ሆነ?" አሉ ግራ እጇን በዓይናቸው እየፈተሹ።

"አውቶቡስ ላይ ተሳፍሬ" ብላ ስትጀምር ምን ማለት እንደፈለገች ገባቸውና አቋረጧት።

"ታዲያ ይጥፋአ። ለዚህ ነው እንዴ ይህን ያህል ለቅሶ! እልም ይበል። የሰው ነብስ አይደለ፣ ገንዘብ አይደለም የሚገዛው? ጦስሽን ይዞ ይሂድ። አንቺ ደህና ሁኚ እንጂ እኔ እናትሽ እስካለሁ ሠርተን እንተካለን። እኔ እንዳውም ሰሞኑን ከእጅሽ ስላላየሁት ስንት ጊዜ ልጠይቅሽ አስቤ እየረሳሁት።"

"ስሞኑንማ አውልቄ አስቀምጬው ነበር ። ዛሬ ምን እንዳንቀዠቀዠኝ አላውቅም ካስቀመጥኩበት አውጥቼ አደረኩት።"

" 'ውጣ ያለው ገንዘብ ግድግዳ ሲጭር ያድራል' ይባል የለም። አዞበት ነው። ጥፋ ብሎት። ተይው ይጥፋ፣ አንድ ማልቀስ አያስፈልግም። እስከዚህ ድረስ ምነው ልጄ! እኔ እናትሽ ክፉ ሆኜብሽ እንኳን አላውቅም። ሳታለቅሺ 'ጠፋ' ብትይኝ ምን እልሻለሁ?" አሉ ቅር ብሏቸው።

"ለሱ ሳይሆን ስንት ለፍተሽ በምታገኚው ገንዘብ የገዛሽውን እንደዋዛ ለሌባ ማስረከቤ ለራሴ ቆጭቶኝ ነው።"

"ቢሆንም ልክ አይደለሽም። ጤና ቢኮን አይደለም የሚለፋው። እግዚአብሔር ጉልበቴን እስካልነሳኝ ገንዘብ ቢጠፋ በገንዘብ ይተካል። እንኳን አንድ ስዓትና ስንት ሚሊዮን ብር ይወድም የለም። እኛ ብቻ ደህና። ይልቅ. . ." አሉና መናገር የፈለጉትን ሳይጨርሱ ትዝ አላቸው። - ድስቱ።

"ኡ! ዛሬ ቀን!" አሉና ወደ ኩሽና ሮጡ። እያቁላሉ ነበር ቶሎ ሊመለሱ ትተውት የመጡት።

ዳርምየለሽ ድንገት በፈጠረችው መላ እናቷን በማሳመኗ በተለይም ደግሞ ትተዋት በመሄዳቸው ደስታ ያልሆነ ደስታ ተሰማት። "አይ እማዬ!" አለች በልቧ በቀላሉ መታለላቸው ለሷ ካላቸው ጥልቅ ፍቅር እና እምነት የመነጨ መሆኑን አስባ። ለምን በስዓቱ እንዳመካኘች ግን ከነከናት። ጠፋ ያለቻቸውን አዲስ ሲኮ ፋይቭ ሰዓት ከገዙላት ሦስት ወር እንኳን አይሞላውም።

ያለፈው እሁድ የእርሷና የእንዳለ ነፃ እሁድ /ፍሪ ሰንደይ/ ነበር። ሲላፉ እንደቆዩ እንደዋዛ ከእጇ ላይ የተፈታውን ስዓት አውልቆ ራሱ እጅ ላይ አሰረው። እንዲመልስ አልጠየቀችውም። ረስታው ሳይሆን ፈቅዳው።



ይልቁንም የርሷን ሰዓት በማሠሩ ተደስታ። የእርሱን ደግሞ እርሷ ብታስር ደስ የሚላት ቢሆንም ሠሪ ቤት ስለሰጠው አላሰረም ነበር። ሲለያዩ "ያንተ እስኪሠራ ተጠቀምበት" አለችው። እንዳለ ከወደደላት እንኳን ሰዓቷን ነፍሷን አውጥታ ብትሰጠው አያረካትም። - ትወደዋለቻ።

ይሁን እንጂ ስጦታ እንዳልስጠችውና መመለሱም እንደማይቀር ታውቃለች። ታዲያ ለምን ለእናቷ መጥፋቱን ዋሸቻቸው? ሲመልስላት ምን ልታደርገው ነው? ውስደው፣ አልፈልገውም ልትለው? ወይንስ ከየት ተገኘ ልትላቸው? 'የራሱ ጉዳይ' እንደማለት አንገቷን ወደ ትከሻዋ ስበር አረገችና ተመልሳ ያስለቀሳትን እውነት ማብጠልጠል ያዘች።

ማምሻዋንም እንቅልፍ እንደተጫነው ሰው ዓይኗን ጨፍናና ድምጿን አጥፍታ ባጠገቧ የሚደረገውን ሁሉ እንዳላየችና እንዳልሰማች ሆና አሳለፈች።

ሁለቱ እህቶቿ ከትምህርት ቤት፣ ወንድሟ ከዋለበት፣ ቀለብተኞቹም ለራት ሲመጡ ከሳሎኑ ወደ ዕቃ ቤቱ መግቢያ በር አጠገብ ካለች ባለመደገፊያ የእንጨት ወንበር ላይ እግሮቿን በመቀመጫዋ ትክክል አጥፋ በመቀመጥ መጽሐፏን አለዚያም የእጅ ሥራዋን በደረቷ አቅጣጫ ጉልበቷ ላይ ዘርግታ የሚያገኟት ዳርምየለሽ በተለመደው ቦታዋ አልነበረችም።

"ዳርምየለሽ የለችም እንዴ?"

"ዛሬ ዳርምየለሽ የት ሄዳ ነው?". . .

እንደየአመጣጣቸውና የአነጋገር ስልታቸው ሁሉም የሚሰነዝሩት ጥያቄ ነበር። በተለይ ቀለብተኞቹ ከዚያ በፊት ልብ ብለውት ባያውቁም የተለመደ ድርጊትና ባህሪዋን ለምደውት ኖሮ፣ ገና ሲገቡ ባማረ ሳሎን ውስጥ የነበረ ትልቅና ደማቅ ጌጥ ተነስቶ ሲቆይ የሚሰማውን ዓይነት ጭርታና ቅሬታ ነው የተሰማቸው። ዳርምየለሽ ካንዳቸውም ጋር ዘና ብላ ተቃልዳና ተጫውታ አታውቅም። ሆኖም አንዳንዴ መጽሐፏን አጠፍ ወይንም እጅሥራዋን ጉልበቷ ላይ ጣል አድርጋ በጨዋታቸውና በክርክራቸው መሐል ሠንዘር የምታደርገው ከንባብና ከተፈጥሮአዊ አስተውሎቷ ያገኘችው በሳል ሃሳብ ስለሚያስደንቃቸው እያደር እንዲወዷት፣ እንዲለምዷትና የቤቱ ጌጥ፣ የቤቱ ውበት፣ ግርማ ሞገስ አድርገው እንዲቆጥሯት ያላወቁትን ተጽዕኖ አሳድሮባቸው ቆይቷል። ይህን በጉልህ የተረዱት ግን ዛሬ ከተለመደው ቦታና ድርጊት ተለይታ ለዐይናቸው ሲያጧት ነው።

የተቀላቢዎቹን እግር ጠብቃ የእናቷን መኝታ ለቀቀችና ከእህቷ ጋር ወደምታድርበትና የራሷ መኝታ ወዳለበት የዕቃ ቤት አመራች። ዓይኖቿን መግለጥ ፈርታ ጨፍኝ ጨፍኝ እያላት።

ዓይኗን በሚገባ ከገለጠች ያን ያህል ያስለቀሳት፤ ነው ብላ ላለማመን ስትከላከለውና ከህሊናዋ ሲያሚግታት ያመሸው ህሳብ የሚያሸንፋት፤ እንደጨፈነች ከቆየችና በዚያው እንቅልፍ ከወሰዳት ግን እንደመጥፎ ህልም ወደ እውኗ ለትመለስ አለመሆኑን አረጋግጣ እርሷ የምታሸንፈው፤ ሲነጋም ሆና የነበረችው እና ወደፊትም ቢሆን የምትመርጠው ህይወትና እምነቷ የሚቀጥል መስሎ እየተሰማት ከብፍድ ልብሱ ጀርባ ተደብቃ እንቅልፏ እንዲመጣ መማጠን ያዘች:: ህሊናዋን ካስጨነቀው የነገር ጦር ለመሸሽ፣ ለማምለጥና ለመጥፋት:: - በእንቅልፍ ጌረስ::



2

ብዙ ተነጋግረውና ተከራክረው የጀመሩትን ገደብ የለሽ የፍቅር ውሎ "ፍሪሰንደይ" ማለትም "ነፃው ዕሁድ" ብለው ነው የሚጠሩት:: ዕሁድን ጠብቀው ለለሚወጡ::

ምንም እንኳ ፍቅር ከውጥኑ በሁለቱም ላይ ብርቱ ቢሆን፤ዳርምየለሽ ከልጅነት ባደገባት ወንዶችን የመጠራጠር ባህሪ ምክንያት ፍቅራቸው ከልባዊ መፈቃቀድ ባሻገር አካላዊ ውህደትንም እንዲጨምር እንዳለ ለሚያቀርብላት ጥያቄ ራሷን አሳልፋ ላለመስጠት ከፍተኛ ጥንቃቄ ታደርግ ነበር:: ትምህርቷን ከግብ አድርሳ በሥራ ዓለም እስክትሠማራ እንዲታገስና እርሱም ቢሆን ራሱን በትምህርትና በሥራ አሻሽሎ ፍቅራቸው በትዳር ሲቋጭ እንደሚደርሱበት፣ ዞሮ ዞሮ ላንዴም ለመጨረሻም ጊዜ የእርሱ መሆኗን እየገለፀች ተከራክራዋለች:: የሚገናኙባቸውም ቦታዎች ከሰው እይታ የራቁ ሆነው በድንገተኛ ስሜት እንዳይሳሳቱ ራሷንም ሆነ እርሱን ትቆጣጠር ነበር::

እንዳለም ቢሆን ከእርሷ ፈቃድ ውጪ አታሎና አስገድዶ ሊደፍራት የሞከረበት አጋጣሚ አልነበረም:: ቀስ በቀስ ስለአካላዊ የስሜት ውህደት አስፈላጊነትና ከከንፈር ያላለፈ ፍቅራቸው በውስጡ የፈጠረበትን የስሜት ረብሻ በማንሳት ሲያግባባት፣ መረር ስትልበትም ሀሳቧን ሲቀበል፣ በክርክር ማላመን ያቃተውን ጨለማን ተገን አድርጐና ብቸኝነታቸውን ጠብቆ በእጆቹና በከናፍሩ ሲያዳክማት አንድ ዓመት ያህል አሳለፉ::ክርክሩ ግን ባፈቀረ አንጀቷ የምትቋቋመው አልነበረም::

"መቼም አስር ጊዜ እወድሻለሁ ዘጠኙ ሸንገላ ነው:: መውደድ ማፍቀር አንዴ ነው:: እውነተኛ ፍቅር ቀን አልፎ ቀን ሲተካ የሚደበዝዝና ደግሞ ደግሞ ካልተቀባ የሚያረጅ የግድግዳ ቀለም አይደለም:: የግድግዳ ቀለም ባዲስነቱ አምሮና ደምቆ የሚታየውን ያህል ሲያረጅ ለዓይን እስኪያስጠላ ተላልጦ ይኾጐረጐራል:: እንደ አዲስ ካልተቀባም ግድግዳውን በእርጅና ያስገምተዋል:: ፍቅር ግን እንደ ጥሩ ህትመት አንዴ ነው:: ወረቀቱ እስካልተቀደደ የህትመት ቀለሙ ብቻውን አይለቅም:: ወረቀቱ እስካላረጀም አያረጅም:: ቢያረጅም እንኳ በሌላ ወረቀት በሌላ ቀለም ተመሳሳዩን ካልሆነ በነበረበት ወረቀትና ሁኔታ ደግሞ ደጋግሞ ለማተም መሞከሩ ወረቀቱን ከማጐሳቆልና ከማበላሸት

በስተቀር ሊያሳምረውና ሊያጐላው አይችልም::

"እኔም ታዲያ እንዳዲስ 'እወድሻለሁ፣ ስለምወድሽ' እያልኩኝ በፍቅር ያሳለፍነውንና ያለንበትን ሁሉ ከምደመስሰው አንቺነትሽን በነፃነት ላገኝሽ እንደምፈልግ ብቻ ብነግርሽ በቂ ይመስለኛል::" ይላታል አዘውትሮ::

"አሁንስ መች አጣኸኝ? ከዚህ ወዲያ መገናኘት አለ?" ወይንም "እንዳታገኘኝ ማን ከለከለህ?" ትለዋለች፤የሚለው ቢገባትም ለመከላከል::

"ይሄ ሰው አየን አላየን እያልንና እየተሸማቀቅን ያለንበት ሁኔታ አያስደስተኝም:: ለመሳሳም ተሸማቀን፣ ለመተቃቀፍ ተሸማቀን፣ ለዚያውም መሽ አልመሸ ተጠብቆ:: ሌላው ቀርቶ ሴትና ወንድ እጅ ለእጅ ተያይዘው ማየት እንደጉድ በሚያስደንቀው ህብረተሰብ መሀል እኮ ነው ያለነው::"

"ምን ይደረግ ታዲያ. . . ." ትልና ክፍል ቢይዙም ለአንድ ቀን ለዚያውም ቢውሉ ለማያድሩበት መሆኑን፤ እስካልተጋቡ እርሱ የሚለው ዓይነት ነፃነት ሊኖራቸው እንደማይችል፤ ዓላማቸውን አሳክተው በአንድ ጐጆ ማደር እስኪጀምሩ መታገስ ካቃተው ግን የሚወዳት ለጊዜአዊ ፍላጐት ተገዝቶ እንጂ በዘላቂ የልብ ፍቅር ተገዶ እንዳይደለ፤ ቅንድቧን እየቋጠረች ተቆጥታ ትከራከረዋለች:: አንዳንዴም ታኮርፈዋለች:: ሁለተኛ ላይጠይቃት ቃል ገብቶ ይተወዋል:: ይሁን እንጂ በሌላ ጊዜና ሁኔታ፤ አቀራረብና ቋንቋውን ቀይሮ ማንሳቱ አይቀርም::

ዳርምየለሽ በልጅነት አዕምሮዋ ቀርፃ የያዘችው፤ ፍቅር ለዓላማ እንቅፋት የመሆኑ፤ ገና ሳይጋቡ ከወንድ ጋር መውደቁ ብልግና የመሆኑ፤ ከፍቅር በፊት ለትምህርትና ለሥራ ቅድሚያ የመስጠቱና ልብን በወንድ ፍቅር ያለማስደፈሩ፤ ሌላም ሌላም ራስን የመጠበቅ ግብረገብነቷ ከፍላጐትነት አልፎ የእንዳለን ውትወታና አስጨናቂ የስሜት ፈተና ሊቋቋምላት አልቻለም:: በከናፍሯ፤ በእጆቿና በጡቶቿ የሚረጭባትን ኤሌክትሪካዊ የፍቅር ሰደድ ነድዳና ተቃጥላ ሳትጠግበው የሰው ኮቴ ወይንም የአጥር መብራት ወይንም ሌላ እንቅስቃሴና ብርሃን ሲረብሻቸው ደንብረውና በተላላፊ ዓይን ተሸማቀው እንደተብከነከኑ መለያየቱ እርሷንም እየሰለቻት መጣ::

እንደልቧ አቅፋውና ታቅፋት ለብዙ ደቂቃዎች ብትስለመለም የልቧ ትርታ ቀንሶ የታመቀ ፍቅሯ እንደ ሸክም ከላይዋ የሚቀል፤ ጉጉቷንም የሚቀንስ መስሎ ተሰማት:: አንድ ቀን ታድያ ስትግደረደር ለተለመደው የእንዳለ ጉትጐታ ፈቃደኛ ሆነች:: "ላንተ ስል" ብላ:: እርሷም እርሱም ራሳቸውን ተቆጣጥረው ከፈቃደ ሥጋ ውጭ ለሆነ የቤት ውስጥ ጨዋታ ብቻ ተስማሙ:: ስምምነታቸው ግን ከሁለት ተከታታይ እሁዶች አላለፈም:: እርሷም እርሱም በሌሉበት፤ በፍቅር ፈረስ ጋልበው ከዚህች ዓለም በጠፉበት አጋጣሚ ሆነ::

"እ!—እ!" ብላ የዚህ ዓለም ጩኸቷን ስትለቀው ከነበሩበት ጣፋጭ ገነት ተመለሱ::



ከዚያ በኋላ የ"ፍቅርን በገደብ" ኪላ ተሰብሮ በነፃነት ተያያዙት:: የእንዳለ ሥጋትና የዳርምየለሽ ቁጥብነት ዓይነጥላ ማረፊያቸውን ፈልገው ተሰደዱ:: ሁለመናዋን ሰጠችው:: ሁለመናውን ሰጣት:: እርሱ በእርሷ እርሷ በእርሱ ሰውነት አዛዥና ናዛዥ ሆነው ተሾሙ:: የእርሷ በረታናም የሴትነት ይሉኝታዋን አሳጥቶ ትምህርቷን ሳይቀር አስዘነጋት::ደብተሯ ላይ የምትጽፈው፤ በየመጽሐፉ የምታነበው፤ የምታየውና የምትሰማው ሁሉ 'እንዳለ'፤ ዓላማዋም ምኞቷም ፍላጐቷም ሁሉም ነገሯ 'እንዳለ' ሆነ::

በዚህ ከቁጥጥር ውጪ በሆነችበት ፍቅር ተጠምዳ የተቀመጠችው የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናም የአሥራ ሁለት ዓመታት ትጋቷን በስተመጨረሻ በመርሳቷ 'አላውቅሽም' አለና የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ነጥቧን ነፈጋት:: ባመጣችው ያልተጠበቀ ውጤት ማትሪክን ከዕድል አዛምዶ አለዚያም በ 'ምን ነካት?' ተጠያይቆ ከትምህርት ቤቷ እስከ ሰፈሯ የሚያውቃት ሁሉ ቢገረምና ቢቆጭም እርሷ ግን ሥራዋን ስለምታውቅ ዕለቱን አልቅሳ 'እንዳለን አያሳጣኝ' ብላ ተጽናናች:: ይልቁንም ቀድሞውኑ የነበራትን የመጻሕፍት ፍቅር ከእንዳለ ፍቅር ጋር አጠናክራ ያዘችው:: ፍላጐቷን የተገነዘበው እንዳለም እንግሊዝኛ መጻሕፍትን ሳይቀር ቀለል ካለ ወደ ከባድ የቋንቋ ደረጃ እያለማመደ ማቅረቡን ተያያዘው:: እርሷም በተለይ ከፍቅር ልቦለዶች ጥሩ ጥሩዎቹን በራሷና በእንዳለ እየመሰለች የገፀ ባህሪያቱ ታሪክና የፍቅራቸው ስኬት በደስታ ሲያስከራት፤ መጥፎ መጥፎው ደግሞ ሲያሸማቅቃትና ሲያስለቅሳት ፍቅሯ ነዶ የማያልቅ ጣፋጭ ነበልባል ሆነ::

እንዳለም በበኩሉ ከእርሷ ባላነሰ ሁኔታ እሚይዝ እሚጨብጠውን እስኪያጣ በፍቅር ከነፈ:: ይሁን እንጂ ከዳርምየለሽ በስድስት እንቁጣጣሽ ቀደም ያለ ዕድሜውና ተወልዶ ያደገበት የችግር ህይወት ባጐናጸፈው ብስለት ታግዞ ሥራውን ጠንቅቆ ከመሥራት አልተደናቀፈም:: እንዲያውም በፕሬስ መምሪያ ኮንትራት የተቀጠረው ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባህል ዓምድ ረዳት አዘጋጅነት ሲሆን ከአሥር ወር በኋላ የዓምዱ ዋና አዘጋጅ የነበረው ጋዜጠኛ ሥራውን ለቆ በመውጣቱ እንዳለ ቦታውን ሸፍኖ እንዲሠራ በቋሚነት ተመደበ:: ማታ ከእርሷ ተለይቶ ሲሄድ ያለፈቃዱ ሊታሠርበት የሚሄድ ያህል ቤቱን እንዲጠላውና እንዲፈራው፤ ጧትም ሥራ ሲገባ ስላሳ ዓመት በእሥር ቆይቶ ዛሬ ትፈታለህ እንዳሉት አስረኛ ከሥራ የመውጫውን ሰዓት በተስፋና በጉጉት እያሰላ እንዲናፍቅ አድርገው ሲያቅበጠብጡት የነበሩ ግንፍል የፍቅር ቀናት፣ ሳምንታትና ወራት በርካታ ነበሩ::

አንድ ሰሞን ታዲያ ከየቀኑ መተያየት ሌላ በተከታታይ የተለቀቁበት 'ፍሪ ሰንደይ' ከበስተኋላው የፀረ-ነፃነት መዘዙን ጥሎባቸው አለፈ:: ሳያዛንፍ ያዘንብ የነበረው የሴትነት ተፈጥሮዋ ወርሃዊ ደመና እንዳንዣበበ ቀረ::

ዳርምየለሽ ብቻዋን ተጨንቃና ተጠብባ የሁለተኛ ወሯን መጀመሪያ አሥራ አምስት ቀን ስትጨርስ የማይቀር ነውና ነገረችው:: ማርገዟን በሀኪም ካረጋገጡ በኋላ ተሯሩጠው ማንም ሳያውቅ የሁለት ወር ቅሪቷን አስወገደች::

ከዚያ በኋላ ሁሉም ዕሁድ እንደነገኙ የሚዘሉበት አልሆነም:: ከደረሰባቸው ተምረው በመከላከያው ላይ ተመካከሩ:: ከብዙ ውይይትና አማራጭ ፍለጋ በኋላም እንዳለ መጻህፍትን አገላብጠ ባገኘው መፍትሔ ላይ ተስማሙ:: ነፃው ዕሁድ እስኪደርስላቸው አንዳቸው የአንዳቸውን ገላ እየናፈቁ ቀናቱን መቁጠር እንጂ በመሐሉ የሚያሰቸግር የለም::

"ዝናብ ነው ፀሐይ ሰሞኑን?" ይላታል:: ጊዜው ሲቃረብ እያሳሳቀ::
"ዝናብ" ካለችው
"መቼ ያባራል?" ይላታል::

ቀኑን ትነግረውና በተከታዩ ዕሁድ ቀጠሮ ይይዛሉ:: ከዝነበ በሦስት ቀናት ውስጥ ያባራላታል:: "ፀሐይ ነው" ካለችው ግን ገና ነው ማለቷ ስለሆነ ጥያቄው በአጭር ይቆምና ከጥቂት ቀናት በኋላ እንደገና ይጠይቃታል:: ይህ የግል ሚስጥራዊ የመልዕክት ልውውጣቸው ለሌላ ሰው ግራ ከማጋባት በስተቀር ስለማይገባ በስልክ እንኳን ሲነጋገሩ ተዝናንተው ነው::

በእነሱ አባባል ዘንቦ ካባራ በኋላ የመጀመሪያውን፤ ከዚያም አሥራ አምስት ቀን ያህል ለበጋ ዘልለው የሚቀጥለው ክረምት ሊመጣ ሲቃረብ ሁለተኛውን 'ነፃ እሑድ' ይውላሉ:: በዚህ ሁኔታ ራሳቸውን እየጠበቁ መውጣት ከጀመሩ ወዲህ ባሳለፏቸው ጊዜአት ሁሉ አንድም ቀን ለችግር ተጋልጠው አያውቁም:: ያለሥጋት ተገናኝተው ሲለያዩም በሙሉ ደስታና ርካታ ነው:: ተከታዩን ቀን እየናፈቁ::

በአራት ማዕዘን ተከልሎ የብርሃን፣ የሰው ዓይን ፈርቶና ሸሽቶ የሚገኝ የመደበቅ ነፃነት:: ከከባቢ ዓለም ትዕዝብት ርቆ መንሾካሾክ፣ መስለምለም፣ መተነፋፈስና መወራረስ በሚፈጥረው ረቂቅ ዓለም መመሸግ:: ከሁለት አንዶች በማያልፍ የገለልተኝነት ሚስጥራዊ ድግስ መሳከር:: ሙሉ ርካታን ሸምቶ በጤናማ ስሜት መለያየት:: ከተለያዩ ማግስት ሳይመጣ እንደገና መነፋፈቅ:: በምሽት ፅልመት ከለላ እየተሳረቁ ሌላ ፍቅር፣ ሌላ ጉጉት፣ ሌላ ናፍቆት መደገስ:: - ዳርምየለሽና እንዳለ::



# 3

"የቀን ቅዱስ" የሚባለው ዕለተ ሀሙስ 'የቀን ርኩስ' ሆኖባት ህሊናዋን ከወጋው የነገር ጦር ያጋጠማት ዳርምየለሽ በተከታዮቹ ቀናት ቀርቶ ለዳግመኛው ሀሙስ እንኳ ከደረሰባት የህሊና ጉዳት አላገገመችም:: እህል አትበላም:: አትናገርም:: ለይምሰል ተነቦ የማያልቅ መጽሐፏን እያገላበጠች ተዘግታ ትውላለች:: አንዳንዴ ብቻ የእናቷ ጉትጉታና ቁጣ ሲበረታባት፤ ከምግቡም እየተናነቃት፤ ከንግግሩም እንባ እንባ እለዚያም ቁጣ ቁጣ እያላት በትንሹ ትሳተፋለች:: በተረፈ እህልና የሰው ዓይን ማየት ጠልታለች:: ወደ ውጭ ወጥታ አታውቅም:: በዙሪያዋ ያለ ነገር ሁሉ ያበሳጫታል:: ያናድዳታል:: እናም ወደ ውጭ ለማየት የተፈጠሩ ዓይኖቿን ጨፍና ውስጠ ውስጧን ታያለች:: እናም ይህን በማድረጓ ከዓለም በሙሉ /ከምታየውና ከሚያናድዳት/ ሸሽታ የተሰወረች መስሎ ይሰማታል:: በዓይኖቿ መከደን የሚፈጠርላት ጨለማ ዘለዓለማዊ ሆኖ ስትገልጣቸውም ዙሪያዋን ቢጋርድላት ምኞቷ ነው:: ከፋቱ ግን ዓይኖቿን ስትጨፍን የጆሮዋ ስሜት ይጨምራል:: ከእግር ጥፍሯ አንስቶ እስከ ራስ ጠጉሯ ያለው መላ ሰውነቷ ብሶቷንና ጭንቀቷን እያደመጠ ሲያባብስ፣ በተለይ ጆሮዋ የማትፈልገውን የከራሷ ውጭ ግንኙነት እያመጣ ይረብሻታል:: ኮሽታን እንደ መብረቅ እያጋነነ ከተደበቀችበት ያወጣታል:: የጠላችውን እና የፈራችውን ዓለምም እንድትማትር ያስገድዳታል:: ብስጭትጭት ጭንቅንቅ ያደርጋታል:: እናም ድምጹን የፈጠረውን ቤተሰብ ይሁን የውጭ ሰው፤ ህያው ይሁን ግዑዝ ነገር ብቻ ካይኗ የገባውን ሳትመርጥና ሳታመዛዝን ቅንድቧ በንዴት እየተርገበገበ ትገላምጠዋለች:: ወይንም ሰድባና ቁጣዋን ታዘንብበታለች::

በዚህ የሰሞኑ እንግዳ ፀባይዋ የተደናገጡት ቤተሰቦቿም ከአጉቷ ባላነሰ ሁኔታ ነው እየፈሯት ያሉት:: እንዲያውም የእርሱ እንደሚሻል ይሰማቸዋል:: - ለይቶለታላ::

የትም ውሎ ሲጨላልም ወደ ቤቱ ይመጣል:: የፊት ለፊቱ ዋና በር ተከፍቶ ካገኘው ብሎ ወደ ስልኩ ያመራል:: ከተዘጋበት ወይንም ተጠባብቀው ከተቆጡት ኩሽናው ገብቶ ዳግመኛ ሳያስቸግር ያድራል::

እርሷ ግን 'ምግብ ብይ' - ቁጣ:: ስልክ ጮኸ - ቁጣ:: 'ምን ሆነሽ ነው?' - ቁጣ:: ሁሉ ነገር ያበሳጫታል:: ትንሽም እናቷን ታከብራለች እንጂ እህቶቿ ንና ወንድሟንማ በግልምጫና በስድብ አጠገቧ እንዳይደርሱ አድርጋቸዋለች::

ሳሎኑን ለብቻዋ ለቅቀውላት ሲሸኟት ይውላሉ።

የምሳና የእራት ሰዓት ሲደርስ ብቻ ቀለብተኞቹ ሳይመጡባት ራሷ ክፍሉን ለቅቃ ወደ መኝታ ቤት ትገባለች። እናቷም ሆኑ እህቶቿ በሰበብ አስባብ መኝታ ቤት እግር ስለሚያበዙ ቀን ቀን ከዕርሱ ይልቅ ጭር ብሎ የሚውለውን ሳሎን ትመርጣለች።

እናቷ ወ/ሮ ብዙነሽ የልጃቸው ኻይታሰብ እንዲህ መሆን ሲያስጨንቃቸው ነው የሰነበተው። እንዲያውም በልጅቸው የነበራቸው ትምክህትና ተስፋ እየደበዘዘባቸው ነው።

የመጀመሪያው ዕለት ምክንያት አድርጋ የነገረቻቸው የሰዓቷ መጥ ፋት ሽፋን እንጂ እውነተኛው የለቅሶዋ መንስኤ እንዳልሆነ ተረድተውታል። ከዚያ ወዲህ በማባበሉም፣ በቁጣውም፣ በመሳሰለው ሁሉ ሞክረዋት የደረሱበት የመጨረሻ መልስ 'ራሴን ያመኛል' የሚል ነው።

ለርሱውም ቢሆን ሀኪም ቤት ቢሏት ፀበል እንደማትሞክረው ቁጣና ምሬት ባዘለ አስፈሪ አስተያየቷ ጭምር ገልጻላቸዋለች። አስገድደው እንዳይወስዷት ደግሞ ጫን ብለው ሲያናግሯት የምትመልስላቸው እንደ እሬት የመረረ ቃል እርሳቸው እንደሚሉት ምናምን ከዞረበት ሰው ሳይሆን ከጨካኝና ክፉ ሰው የሚሰነዘር ዓይነት በመሆኑ ፈሯት። አንድ ነገር እንደሆነች ግን አላጡትም። ባትሆንማ ለእናቷም ሆነ ለቤተሰቧ የነበራት ፍቅርና አክብሮት በቀናት ውስጥ ተሟጦ ከአውሬ ባላነሰ ሁኔታ እንደማትሸሻቸው ለእናትነት ስሜታቸው ግልጽ ነው።

"ልጄን አንድ ነገር ተጠናውቷታል እንጂ መቼም ያለምክንያት እንዲህ አትሆንም" ይላሉ በልባቸው። ያ! አንድ ነገር ግን ምንነቱ ሊገባቸው አልቻለም። አንዳንዴ የችግሯ መንስኤ ጧት ከማታ አንቃ የምትውለው መጽሐፍ ይመስላቸዋል። በደህናውም ጊዜ ከመጽሐፍ ጋር ችክ ብላ መዋሏን አይወዱላትም ነበር።

"እንዳው ልጄ አንድ ቀን እንኳን ቢቋረጥ ትሞቻለሽ ልበል! የምን ጭንቅላት ማዞር ነው እሱ! ትምህርቱን እንደሁ ጨርሰሸዋል። እስቲ ትንሽ ረፍት አርጊ" ይሏታል። 'እንብላ' ም ይሁን እንዲህ እናርግ ሲሏት "ቆይ ትንሽ ላንብብ" ወይንም "ይቺን ገጽ ልጨርሳት. . ." ማለቷ የተለመደ በመሆኑ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ 'ፍቅር ይዟት ይሆን?' ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። አወንታዊነቱን ሊቀበሉት ባይፈቅዱም የሚያስቡትን አጥተው ግራ ግብት ሲላቸው፣

'ግን ፍቅር እንዲህ ያደርጋል?'



# 4

የቅዳሜው ለሊት ሸሽቶ የጥቅምቱ አራተኛ ዕሁድ ውርጫማ ማለዳ ብቅ ማለቱ ነው። ተዘግተው ያደሩ በሮች መከፈት ሲጀምሩ በእማማ ሸዋርካብሽ መሪነት ገብርኤል ሠፈር ደርሰዋል። ጥቂት በመንደሩ ውስጥ ለውስጥ እንደሄዱ ቆም አሉና አጥር የሌላትን ትንሽ ቤት መዝጊያ መደብደብ ያዙ። - እማማ ሸዋ።

"ደረስን ማለት ነው?" አሉ ወ/ሮ ብዙ በልባቸው "ይቅር ይበለኝ ጌታዬ! እስቲ የፈጣሪን ደጅ በመጥኛው ሰዓት!"

'ጉሽ ለልጂ ስትል . . .' ሆኖባቸው እንጂ የዛሬውን አመጣጣቸውን አልወደዱትም። ባር ባር ፍራት ፍራት ብሏቸዋል። የመጡትም በእማማ ሸዋ ግፊት ነው።

"ኤዲያ ምንድነው እሱ! እገሌን ግደልልኝ፣ እገሊትን አጥፋልኝ አይሉ። ይቅር ይበልሁ እቴ! ክርስቶስ የልብሁን ንጽህና ያውቃል። ደሞኮ ለቃልቻ ሊሰግዱ፣ እጣን ሊያጨሱ አይደለም። ይልቅ የባሰ ሳይመጣባት እንሂድና መላ እንበልላት" ብለዋቸው።

እርሳቸውማ "ወላዲት አምላክ ታውቃለች! እርሷ እንደፈቀደች ታርገኝ።" ነበር ለሚገጥማቸው ችግር መከታ አድርገው የሚያነሱት መፈክር።

"ይቅር ይበልሁ እቴ! እንመጣለን ብዬዎትም አልነበር!" አሉ እማማ ሸዋ በሩ ሲከፈት መጋኛ እንዳያጮላቸው ወደ ኋላ እየሸሹ።

"እሱስ አዎ! እኔም አልረሳሁ፤ እንቅልፉ ተጫጫነኝና ነው እንጂ" አሉ ደስ በማይል የጧት ድምጽ እርሳቸውም ከመዝጊያው ኋላ ተከልለው። - አባ ደርበው።

"ይቅር ይበልሁ! አርጅተሁ ነዋ። አሮጌ ሰው ምን አቅም አለው። ወይ ወንድሜን!" አሉ እራሳቸው ቀደም ብለው ወ/ሮ ብዙን 'ግቡ' እንደማለት ባይናቸው እየጠቀሱ።

"እንዴት ባክሽ! ሥራ እኮ አላቃተኝም" አሉ በጉንዮሽ እማማ ሸዋን

ፊት ለፊት ደግሞ ያስከተሏቸውን እንግዳ እያስተዋሉ::

"አዬ! እንቅልፉን ማሸነፍ ያቃተው ሰው ተጋድሞ ማደር እንጂ ምኑን ሥራ ይሠራዋል!" አሉ እማማ ሸዋም ያባ ደርብ አማርኛ ስለገባቸው በተመሳሳይ ዘይቤ እየመለሱ::

"ተይ እንጂ ከእንግዳ ፊት አታዋርጂኝ:: ኧረ እኔ ሠራተኛ ነኝ:: የሚሠራው ጠፋ እንጂ...ይቀመጡ እሜቴ" ፈገግ እያሉ በእጃቸው ለወ/ሮ ብዙ ወደ አግዳሚው በመጠቆም:: እማማ ሸዋም ወ/ሮ ብዙን ተከትለው ተቀመጡ::

አባ ደርብ ሠረቅ አድርገው ተመለከቱ:: ያሁኗን ፊታቸው እሳት የነካው ላስቲክ የመሰለ አሮጊት ሳይሆን የጥንቷን አበባ የመሰለች ድምቡሽቡሽ የገጠር ወይዘሮ::

አቀረቀሩ እማማ ሸዋ:: አባ ደርበው የተመለሱበት ትዝታ እንደ ጠራቸው ሁሉ ሰፋ ባለ ትከሻው ላይ እንደበረዶ የነጣ ጋቢውን እንዝርግግ፣ አምሮ እንደተሠራ ልቃቂት የተስተካከለ ጥምጣሙን በራሱ ላይ ያስቀመጠ፣ 'ምነው እንደልብ የሚገኝ በሆነ' የሚያሰኝና ቄስ ለመባል የሚያሳሳ መልከ መልካም ወጣት ከመሬት እንደሚፈለፍሉ ሁሉ በሀሳባቸው እያመጡት::

ወ/ሮ ብዙ የሁለቱም ሁኔታና የቃላት ጨዋታ አልጣማቸውም:: "አንድ ዘመዴ የሆኑ ቄስ አሉ" ብለው ነበር ያመጧቸው:: አሁን ሲያዩዋቸው ግን እርሳቸውም ዘመድ ቄስ የተባሉትም ቄስ አልመሰል አሏቸው::

"እንግዲያውማ የውነት ቄስ ቢሆኑ ሌላው ቀርቶ በሰንበት ምድር እዚህ አጠገባቸው ገብርኤል እየተቀደሰ እቤታቸው ይተኛሉ?" ብለው በሃሳብ ራሳቸውን ጠየቁ::

ብቻ ሁሉም ነገር አላማራቸውም:: የራሳቸው ሃጢአት፣ አባ ደርበው፣ እማማ ሸዋ፣ ቤቱ ራሱ ሽታና ከሽታውን ጨምሮ፤ ሁሉም ወደ ሲኦል የሚወስዱ አስፈሪ መንገዶች ሆነው ተሰሟቸው::

"ወ/ሮ ብዙ ነው ስምዎ? እንደተቸገሩ በቀደም ሸዋ ነግራኛለች::" አሉ አባ ደርብ ኮስተር ብለው ዳዊት ይሁን መጽሐፍ ቅዱስ የማይለይ በቆዳ የተደጐሰ ጥራዝ ከማህደሩ እያወጡ የተመሳቀለ የጠፍር አልጋቸው ላይ በመቀመጥ::

ጭንቅላታቸውን በአወንታ ወዝውዘው ዝም አሉ ወ/ሮ ብዙ ምን ማለት እንዳለባቸው እያሰላሰሉ::

"እሺ እንግዲህ በውነቱ ለመናገር አይደለም፣ የዚህ ዓይነቱን ነገር



ለማንም አልሠራም:: እግዚአብሔር አይወደውም:: ሆኖም ግን በሸዋርካብሽ በኩል ስለመጡብኝ ለምወዳት እህቴ ስል አይልዎታለሁ፤ እንጂ በፍጹም ክልክል ነው:: ሌላው ቀርቶ በተስኪያኒቱም አትቀበለውም::" ሲሉ እማማ ሸዋ ካፋቸው ነጠቁና፤ "የትም ቢሄዱ አዳኙ ያው አንድዬ ነው:: ሥልጣኑን መፈታተን እንዳይሆን መጻፉ ከለከለ እንጂ ይሄም ቢሆን የእግዚያብሔር መንገድ ነው:: የመጽሐፉን ትዕዛዝ በማለፋችን መቼም ተቸግረን ነውና እርሱ ይቅር ይበለን::" አሉ አንድ ቀን ከራሳቸው ከአባ ደርበው አፍ የሰሙትን በመድገም::

"እውነት ብለሻል:: እርሱ ምህረቱን እያወረደልን እንጂ እንደኛ ሀጢአትማ . . ." አሉ አባ ደርብ እግዚአብሔርን ያዩት ይመስል ወደላይ አንጋጥጠው::

ወ/ሮ ብዙ ጭንቅ እንዳላቸው በልባቸው ወላዲት አምላክን ደጋግመው ተማፀኑ:: እንድታድናቸው::

"ስም ይንገሩ!"

"የማን? የኔ?" አሉ ወ/ሮ ብዙ ሳያስቡት በመሆኑ ተርበትብተው::

"ኧረ የለም፤ የልጅቷን" አሉ አባ ደርበው::

"ዳርምየለሽ"

"ዳርም የለሽ፣ ዳርምየለሽ" አሉና የሥም ዝርዝር ይፈልጉ ይመስል ገልጠው ባዘጋጁት ገጽ ላይ አመልካች ጣታቸውን ወድረው ከላይ ወደታች ከታች ወደላይ አንቀሳቀሱት:: ትንሽ ቆዩናም

"የርስዎ?"

"ብዙነሽ" አሉ እማማ ሸዋ ተሽቀዳድመው:: ወ/ሮ ብዙ እንደበታቸው የተዘጋ ይመስል ዓይናቸውን አቁለጭልጨው ዝም አሉ::

"ብዙነሽ ብዙነሽ ብዙነሽ" እያሉ አባ ደርብ ስማቸውን ሲደጋግሙ ገና እንደመጡ በስማቸው የጠሯቸውን አስታወሱና አሁን ከምን ጊዜው እንደረሱት ተገረሙ::

ገጽ እየቆጠሩ ጥቂት ከገፉ በኋላ ቆም ብለው ማንበብ ያዙ::

"እነሆ ይስሙ እሜቴ!" አሉ ከአቀረቀሩበት ወደ ወ/ሮ ብዙ መለስ ብለው::

"እሺ!" አሉ የመጨረሻ ፍርዱን ሊሰማ ዳኛ ፊት እንደቆመ ወንጀለኛ በስጋት ተርበትብተው::

"ይህች ልጅዎ የሰው ፍቅር አላት:: ቁም ነገረኛና ነገር አዋቂ ነች:: ደግ ምክርና ነገር አመላለስ ታውቃለች::"

ወ/ሮ ብዙ ድንጋጤና ፍርሃት መገረምን ቀላቅሎ አሸበራቸው::

ስለዳርምየለሽ የተናገሩት ትክክል በመሆኑ እርሳቸው እየተጠራጠሩ መምጣታቸውንም እንዳያውቁባቸው ፈሩ::

"አይደለም?" አሉ አባ ደርበው::

"ልክ ነው" አረጋገጡ ጭንቀት አፋቸውን ያዝ አርጓቸው::

"እረ እሷ የልጅ አዋቂ እግዚአብሔር መርቆ የፈጠራት ነበረች፣ ምን እንደነካባቸው እንጃ እንጂ::" አሉ እማማ ሸዋ::

"የነካትንማ አሁን ይነግረናል፡፡" አሉና ቀጠሉ አባ ደርብ:: "እግረ ቀጭን መልከ ደማም ናት:: ወላድም ናት:: ህብታምና ባለ ብዙ ፍሬ ትሆናለች:: ትንሽ ቀን ትቀነዝራለች:: በወሊድ ጊዜም ደም ይፈሳታል:: ዕጣንና ከርቤ ትታጠን:: እጅዋ ለመስጠት ቸርና ለጋስ ናት የተናገረችውና ያሰበችው ፈቃድዋ ካልሞላ በጅ አትልም:: በነጭ የአዳል በግ ብራና ላይ የሚጻፍ አለ እርሱን አስጽፋ መያዝ አለባት::"

"ደጋግ ልጆች ትወልዳለች:: የቤት አያያዝ ታውቅበታለች:: ቁጠባና ብልህነትም ዕድልዋ ነው:: እድሜዋ ከአምሳ አምስት እስከ ስድሳ ነው:: አሁን ግን ድርካቡ የሚባል ከዛር የተወለደ ጋኔን ደም ላይ ወግቷታል:: ማክሰኞ ቀን ነው የወጋት::"

ወ/ሮ ብዙነሽ 'ዛር' እና 'ጋኔን' የሚሉትን ቃላት ሲሰሙ "በስመአም፣ ሰአሊለነ ቅድስት" አሉ ሳይታወቃቸው በድንጋጤ በሚንቀጠቀጥ እጃቸው እያማተቡ::

"አይዘዎ አይደንግጡ! ማርከሻውም አለ" አሉ አባ ደርብ "የት አባቱ ይህ አረመኔ በምን አየብዎ!"

"እንድዬ ይማራት እንጂ፣ ሁሉስ ይታመም የለ! መጨረሻውን ምህረቱን እንዲልክላት መለመኑ ይሻላል::" አሉ እማማ ሸዋ ወደላይ እያንጋጠጡ::

አባ ደርብ መግለጫቸውን በጥያቄ ቀጠሉ:: "ራሷን፣ ወገቧን፣ ልቧንና ሆዷን ያማታል? ተቅማጥ ትውከትና ነስር አለባት?"

"ራሴን ትላለች:: ልቧንም ያማታል ጭብጥ ብላ እንደተኛች እንቅልፍ የለ ምን የለ ስትገላበጥ ታድራለች:: ሽለብም ካረጋት መቃዠት መለፍለፍ ነው:: ቀንም ይኼ መከረኛ መጽሐፍ አለ! እንዲህም ሆና ዓይኗን ስታፈዝዝበት ትውላለች:: ሌላው ሌላውማ ምኑን አውቄ:: ብቻ ተቅማጥ ትውከት የለባትም:: ለዚያውስ ምን በልታ? እህል አትቀምስ ዝም ብላ ውሃ ብቻ መጋት ነው::" አሉ ወ/ሮ ብዙ እንባቸው እየተንቸረፈፈ::

"አይ ልጄን! ይሄ መናጢ አስሯት ነዋ! ስንት ቀን ሆኗታል?"

"ያለፈው ሐሙስ ስምንት ቀን አለፋት:: ፊክ የሚካኤል ዕለት ጀምራ ነው::"

"ስምንት ቀን፣ ስምንት ቀን"እያሉ ለራሳቸው በማልጐምጐም ካሰቡ በኋላ እንግዲያው ምንም አይላት:: ትናንት አስር ቀኗም አይደለም? ይለቃታል:: እስከትናንት ነበር የሚያስጋት:: አሁን ወደእግዚአብሔር ትፀልይ:: ለሦስት በተስኪያናት እጣንና ዘቢብ ትሳል:: ቀይ ያልተጠቃች ፍየል ትብላ:: ቀይ ዶሮም አርብ ቀን አርደው ከመንገድ ይጣሉላት:: ከዚያ በኋላ የገብርኤልን



ጠበል ለስምንት ሳልስት አከታትለው ያስጠምቋት::"

"ይቅር ይበልሁ እቴ እርስዎ ደግሞ እንዳው! ምን ያስለቅስዎታል? ይልቅ በጽሞና ሰምተው የሚደረገውን ማድረጉ አይሻልም? ምንም አትሆን አሉዎትኮ:: እንድዬ ምህረቱን እንዲሰጣት መለመኑ ነው የሚበጀው:: ሁላችንስ የማን ነን? እሱ የቋጠራት ነብስ ከርሱ በስተቀር አዛዥ የላትም:: ካለ መድሃኒአለም እንኳን የተለከፈ ጨርቁን ጥሎ ያበደ ይድናል::"አሉ እማማ ሸዋ የወ/ሮ ብዙን ለቅሶ እየገሰጡ::

"ይስሙ እንጂ እሜቴ! ምንድነው ለቅሶ! ለቅሶ መድሃኒት ይሆናል?" አሉ አባ ደርብም እየተቆጡ:: "ይኼን የሚጻፈውንም፣ ጠበሉንም፣ ፀሎቱንም ስትል ይለቃታል:: የት አባቱ ይኼ አመዳም! ቅዱስ ገብርኤል በሰይፉ ቀንጥሶ ይጥለዋል::"

ብራናውን ፈልገው እስኪጽፉላት ወ/ሮ ብዙ ሌላ ሌላውን እያደረጉላት እንዲቆዩ አዝዘው ለአሥራ አምስት ቀን ቀጠሯቸው:: በሰባ አምስት ብር ተስማምተው::

"ለኔ አይደለም" አሉ አባ ደርብ ለማሳመን :: "እውነትን መናገር ጥሩ አይደለም? ብራናው እንኳን ዋጋው ሰማይ ደርሷል:: ለዚያውም ቢገኝ:: ለመዳኒት ያሉት ሁሉ ነገር ጨው ነው:: መቸም እርስዎ ሆነውብኝ እንጂ እንዲህ ያለው ሥራ ባሁኑ ጊዜ ቀርቷል:: ለራሴም ምንም ጥቅም አላገኝበትም::"

ወ/ሮ ብዙ አመኗቸው:: ባያምኗቸውም ምንም ማድረግ አይችሉም:: ለልጅ ህይወት የወላድ አንጀት የማይፈቅደው ነገር የለምና ከብሩ ይልቅ የቀኑ መርዘም አሳሰባቸው::

"ታዲያ ቀኑ አልራቀም አባ?"

"ይደርሳል ግዴለም:: እስተዚያው ብስራቱንም ድርሳኑንም ስሟን አንስቼ እደግምላታለሁ:: አይዘዎ! እርስዎም ቢሆኑ ጠበሉን ምኑን አሁን የነገርኩዎን ሁሉ ያድርጉላት::"

"አዬ ፀበል" አሉ መህረባቸውን እየፈቱ:: እምቢታዋን በልባቸው አሰቡናም ቅር አላቸው::

"እንግዲህ ለጊዜው የያዝኩት ይኼንን ነው:: ላስራምስት ቀን ስመጣ እሟላለሁ:: ይቸግርዎት ይሆን?" አሉ ሁለት ባለ አስር ኖቶችን እየዘረጋጉ::

"ግዴለም:: ለጊዜው ይበቃል እሜቴ! የቀረውን ከራሴም ቢሆን ሞላልቼ እሰራውና ላስራምስት ቀን ይሰጡኛል:: ታዲያ ሰው አስቀምጥልኝ ካለኝ ገንዘብ ስለሆነ የማነሳው አደራ እንዳያስተላልፉብኝ::" አሉ አባ ደርብ ብሩ እጃቸው እስኪገባ ቋምጠው::

"ራሴው ልምጣ ወይስ እሷም ታስፈልጋለች? መቼም እሺ አትለኝ"

አሉ ወ/ሮ ብዙ ቀሪውን ከቀኑ እንደማያሳልፉ አረጋግጠው የያዙትን ከሰጧቸው በኋላ ሊሄዱ ሲነሱ::

“ግድየለም እሜቴ አይቸገሩ:: ወደርሷ ሠፈርም አይደል ቤትዎ?” አሉ ወደ እማማ ሸዋ በእገጫቸው እየጠቆሙ::

“አዎ ወደ ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሲወርዱ ከምንገድ በስተቀኝ ቤተክህነት ፊት ለፊት ነው:: የእማማ ሸዋ ቤት በኗ አጥር ሥር አልፎ ገባ ይላል::”

“እኔው እመጣለሁ:: ከጠፋኝም እሷ ቤት እሄድና ታመጣኛለች:: ተዚያ ወዲህም ታገኝሁ ቀደም ብዬ እጽፍላታለሁ:: አይዘዎ እሜቴ!”

እስከ ደጅ አፉ ሸኝተዋቸው ተመለሱና የአጠና አልጋቸው ላይ ተዘረገፉ:: የሽማግሌ ልባቸው እንደ አፍላ ጐረምሳ ከአቅሟ በላይ በደስታ እየደነከረች::

‘ያልታሰበ ሲሳይ’ በጥዋቱ ሃያ ብር ሃያ ጉሮሮ መከደኛ::

“ፈጣሪ አምላክ የከፈታትን ጉሮሮ ሳይዘጋት አያድርም:: ተመስገን! ተመስገን ፈጣሪዬ!” አሉ አሁንም ፈጣሪ አምላካቸውን ያዩት ይመስል ወደ ቅርብ ጣሪያቸው አንጋጠው እያልጐመጐሙ:: መለስ አረጉናም ደስታቸውና ምስጋናቸው ወደ ፍርሃት ተለውጦ “ይቅር በለኝ ፈጣሪዬ!” አሉ ባመስገኑበት አቅጣጫ ልመናቸው የማይደርስ ይመስል ወደ መሬት እያቀረቀሩ::



# 5

“ጭርርርር” ብሎ ጮኸ ስሜቷን ያላጤነው ስልክ:: ቀና ብላ አፈጠጠችበት:: ገላመጠችው:: አልተሸማቀቀም ወይንም አልተደናገጠም:: ይባስ ብሎ ጩኸቱን ደጋገመው:: ታናሽ እህቷ ኑንሽ እንደ ሌባ እየተጠራጠረችና እየተሸማቀቀች ገብታ አነሳችው:: ዳርምየለሽ ደግሞ የስልኩን ንዴትና ግልምጫ ወደ ኑንሽ አዞረችው:: እርሷ ጩህባት ያለችው ይመስል::

“ስልኩ ላንቺ ነው::” አለች ኑንሽ እንዳትቆጣት ስትፈራ ስትቸር:: ዳርምየለሽ በቅንድቧ ጠርዝ አነሳቻትና ወደ ስልኩ ተጠጋች::

ተነጋግራ ስትጨርስ እዚያው ስልኩ አጠገብ ተቀመጠች:: “ለምን እሺ አልኩት?” አለች በሃሳቧ:: ቀጠሮው ገና ለከሰዓት በኋላ ቢሆንም ካሁኑ በመሄድና ባለመሄድ መሀል እያመነታች::

ተንቀዥቅዣ መጣችና “ሚያው”እያለች ጉልበቷ ላይ ወጣች:: - ውሮ:: ብድግ አድርጋ አሽቀነጠረቻትና በድንጋጤ ደርቃ ቀረች:: ያላሰበችው ነገር:: ከእጇ የተወረወረችው ድመት ድንክዬዋ ጠረጴዛ ላይ ከነበረው የውሃ ጠርሙስና ብርጭቆ ላይ አረፈች:: እርስ በርሱ ተገጫጭቶ ሲንከሻከሽ የደነገጠችው ድመት ከተሰበረው ጠርሙስ የደረሳትን ውሃ ተቀብላ ሰውነቷን እየሰበቀች ተፈተለከች::

ዳርምየለሽ ተሸማቅቃ ወደ ስብርባሪው ስታመራ ኑንሽ ቀድማ ደረሰችና መለቃቀም ጀመረች:: አሁን አልተቆጣቻትም:: እንዲያውም የሦስቴ ታናሿን እንደ ሦስቴ ታላቋ ፈራቻት::እናም ወደ ኋላ ተመልሳ በተላላጠው አሮጌ ሶፋ ላይ የመውደቅ ያህል ተቀመጠች:: ኑንሽ ስብርባሪውን አንስታ የቀረውን እንደነበር አስተካክላ ወጣች:: ዳርምየለሽም ጉልበቷን ወደ ደረቷ አጥፋ የፀጉሯን ጫፍ እያፍተለተለች ራሷን መውቀስ ያዘች:: ለዛሬው ብቻ ሳይሆን ለሰነበተችበት ሁሉ::

“ምን ነካኝ ?. . .”

በውስጧ ተቀብሮ የኖረው ሚስጥር በእናቷ አኙት ያላዋቂ ቆፋሪነት ተነካክቶ ልብቀል እያለ ሲተናነቃት፣ እርሷ ልትነቅለው መልሳም እድሜ ልኳን

ልትቀብረው ስትታገል፣ ሥሩን ስትለው ቅርንጫፉ፣ ግንዱን ስትለው ቅጠሉ እየተዝረከረከባት ስትወራጭና ስትበሳጭ ከራሷ አልፋ ቤተሰቧን መረበሿ ይታወቃታል። የዛሬው ደግሞ ብሶ ታያት። ዛሬ ዕቃ ለመስበር ደርሳለች ነገ እንዳትፈታ. . . ከዚህ ሀሳብ ከዚህ ጭንቀትና ብስጭት ለመውጣት በውስጧ ከሚራኮተው ሁለትዮሽ ሀሳብ በየትኛው ላይ ትወስን?

አንደኛው ልቧ ከእስካሁን ህይወቷ ጋር ድርና ማግ ሆኖ የቆየውንና አሁንም እንዲቀጥል የምትፈልገውን ሀሳብ ደግፎ፣ ሌላኛው ልቧ ደግሞ የእናቷ አጉት ቀኛዝማች ከፍያለው ከተቀበረበት ምሰው ያወጡትንና እርሷ ልትቀበለው የማትፈልገውን አዲስ ሀሳብ ደግፎ። - ፍልሚያ።

አንድ ልብ ከሁለት ሲከፈል ህሊና የሁለት ተቃራኒ ሀሳቦች መድረክ ሆኖ በአንደኛው ላይ መወሰን ሲያቅተው የመድረኩ /የአዕምሮ/ ሥርዓት ይዛባል። በሁለት ወገን የህሳብ ጦርነት ሲወጋ መላ ሰውነት ይቆስላል። ከእግር ጥፍር እስከ ራስ ፀጉር ያለው የነርቭ ሥርዓት ይፋለሳል። መክሳትና መገርጣት፣ ባጠቃላይ ጤናማ ያልሆነ አካላዊና መንፈሳዊ ለውጥ ይከተላል። ዳርምየለሽም ከሰሞኑ ሁኔታዋ ያተረፈችው ውጤት ቢኖር ይኸው ነው።

አጠር ደልደል ብለው ከአደባባይ የሚገነጠል ጉዳና የመሰለ በራ ያላቸው ባለረዥም ጢም አባቷን በሐሳብ ወይንም በፎቶ እያየች ክፋትና ደግነታቸውን፣ አባታዊና ኢ-አባታዊ ቀረቤታና ርቀታቸውን ለማነጻጸር የኋልዮሽ ዕውቀ ነብስ እስካገኘችበት ዕድሜ ዘመኗ ለፍተሻ ትማስናለች።

አቶ ባህሩ ፍስሐ በአውራ ጉዳና መ/ቤት የግሬደር ኦፕሬተር በመሆናቸው ኑሮአቸው ባመዛኙ ድርጅቱ ፕሮጀክቱን በዘረጋበት ክፍለ ሀገር ሁሉ አንዱ ሲያልቅ ወደ ሌላው እየተዘዋወሩ ነው። ለዓመት በዓል ብቻ ከየትም ይሁን ከየት እንደምንም መጥተው ከቤተሰባቸው መሃል ይገኛሉ። እናም ቆይተው ቆይተው በበዓል ምክንያት ይሁን ካንዱ ተቀይረው ወደሌላ ሥራ ቦታ ለመሄድ እግረ መንገዳቸውን ሲመጡ እርሷና ሌሎቹም እህቶቿና ወንድሟ በናፍቆት እየሮጡ የሚቀበሏቸው፣ በግም ይሁን ዶሮ፣ ፍራፍሬም ይሁን ጥራጥሬ ምን እንዳመጡላቸው ለማየት የሚጓጉት፣ እርሳቸውም ከናፍቆት ሰላምታቸው በኋላ ከሁሉ አስቀድመው ስለትምህርቷ የሚጠይቋት፣ ውጤቷንም ሰምተው "ጉሽ የኔ ልጅ!" በማለት እንደገና እየሳሙ ለታናናሾቿ በአርአያነት የሚጠቅሷት፣ . . . ከልጅነቷ ጀምሮ ያለው በጎ ነገራቸው ሁሉ ደምቆና ጉልቶ ይታያታል። በዚህም የመልካም አባትነት ፍቅርና ውለታቸው እንጂ 'የ. . .አባት' ተብሎ ለመጠራት እንኳ የሚያደርስ ጥላቻና ክፋታቸው አይታያትም።

"ውሽታም ናቸው! አባቴ ባህሩ እንጂ ማንም ሊሆን አይችልም። ሌላ



አባት እንዲኖረኝም አልፈልግም።" ትልና ሁለተኛ አዕምሮዋን ስለሚያስጨንቀው የአባቷ ማንነት ጥያቄ ሳታስብ ትወስናለች።

ወዲያው ደግሞ እኒያ 'የተረገሙ' የእናቷ አጉት በህሳብ ይመጡባታል። ". . . . ያ! እንጀራ አባትሽ. . . ." ኢያሉ። - ቀኛዝማች ከፍያለው።

ቀኛዝማች በጣሊያን ጊዜ በአርበኝነት የታገሉ ጀግና በመሆናቸው አሁን በዕድሜ ለደከመ ጉልበታቸው ማፅናኛ አኩሪ ትዝታና ወግ የማያጡ ጠንካራ ሽማግሌ ናቸው።

ከአርበኞች ማህበር ከተሰጣቸው ካኪ ዩኒፎርም ጋር የድሮ ክቡር ዘበኛ ባርኔጣ ደፍተው ከወገባቸው ወርዶ እሚያውቅ እማይመስል ባዶ ዝናራቸውን እንደታጠቁ ጭራቸውን ግራና ቀኝ በመነስነስ የጦርነቱን ወግ መተረክ ከጀመሩ አፍ ያስከፍታሉ። በአወራራቸው ስሜታቸውን ኦጋብተው አድማጫቸውን በወኔ የሚነሽጡ የሰባዎቹ መጀመሪያ ግድም አዛውንት ናቸው።

ዳርምየለሽ የምትወዳቸው በዚሁ የጣሊያን ጊዜ ጨዋታና ታሪካቸው፣ በተለይም በአተራረካቸው ነበር። የግንባራቸው ንብርብር የፈጠረው ተከታታይ መስመር ካነጋገራቸው ጋር እጥፍ ዘርጋ ሲል ስታይ ታሪካቸው ከአዕምሮአቸው የትውስታ ማህደር ሳይሆን ከግንባራቸው ላይ የሚፈታ ይመስላታል። አዘወትራም ስለእሳቸው ስትናገር፦

"እያንዳንዱ የግንባራቸው መስመር በፊተኛው ዘመን ያሳለፉትን ታሪክ ቋጥሯል . . . ገጽታቸው ከአፋቸው ቀድሞ ስለእርሳቸው ይናገራል። አባባ ከፍያለው እኮ ያለፈው ትውልድ የታሪክ ማህደር እንዲያውም ቅርስ ናቸው። . . ." ትላለች። አዘውትራ ወደቤታቸው በመሄድም ታነብባቸዋለች። የተረፈውንም የሽማግሌ ከማይመስለው ነጎድጓዳማ አንደበታቸው ታዳምጣለች።

ቀኛዝማችም ቢሆኑ ዳርምየለሽን ይወዷታል። የአዲሱ ትውልድ ናሙና እንደሆነች፣ በብሩህ አዕምሮዋና በብልህነቷ እንደሚደሰቱባትና እንደሚኩሩባት ለራሷ ሳይቀር ይነግሯታል። እንዳዋቂ ቁጭ አድርገው እስኪበቃት ትናንትን ዛሬ ላይ አምጥተው ያወጓታል። እያሞጋገሱና እያሞከሹ። - አሁን ግን ጠላቻቸው።

አሁን ስለእርሳቸው በጉልህ የምታውቀውና ከህሊናዋ ገብቶ የሚቆረቁራት ነገር ቢኖር ". . .ያ! እንጀራ አባትሽ. . ." የሚለው፣ አውጥታና አውርዳ ለመርሳት የደረሰችበትን ውሳኔ የሚያፈርሰው ሀረግ ብቻ ነው። - የማትፈልገው። ጭራቸውን እየነሰነሱ፣ የግንባራቸውን ቆዳ በንብርብር እያጠፉ ይመጡባታል። የሚያወሩት፣ የሚተርኩት ሁሉ ስላሳለፉት ህይወትና

ስለማሊያን ጊዜ መሆኑ ቀርቶ ስለወላጅ አባቷ ታሪክና ስለ እርሷ ዲቃላነት ይመስላታል:: እስካሁንም ከእርሳቸው የሰማችው ሁሉ 'እንጀራ አባትሽ' የሚል ይሆንባታል:: - በሀሳቧ:: በዚህ ምክንያትም ጠላቻቸው:: ያን ሁሉ ምክርና ፍቅራቸውን በሁለት ቃላት ሠረዙት::

". . .እንጀራ አባትሽ. . ."

ፌ

ምነው የዛን ቀን እግሯን በሰበራት:: ቤታቸው ሊጠይቃቸው ለሚሄድ ወዳጅ ዘመድ፣ 'አባ ዝናር' በሚል ቅጽል ለሚያውቃቸው የባሻ ወልዴ ችሎት ሠፈር ሠፈርተኛ ሁሉ ቁጭ ብለው ስለእርሷ ዲቃላነት የሚተርኩ ይመስላታል:: -እንዴት አሰጧት!

ለጭንቀቷ መንስኤ የሆነውን የአባቷ ማንነት ጥያቄ የጫረባት የቀኛዝማች ግልጽ ንግግር ቢሆንም ከዚያ ወዲህ በርካታ ትዝታዎቿን እያገናዘበች በአቶ ባህሩ አባትነት ላይ ያደረባት ጥርጣሬ ይበልጥ ጐልብቷል::

አንድ ጊዜ ገና ህጻን ሳለች ከጐረቤት ልጆች ጋር 'ዕቃ-ዕቃ' ሲጫወቱ ከአሰገዱ /የአሁኗ ሳቢ ጋይድ/ ጋር በሰርዲን ቆርቆሮ 'የኔ ነው የኔ ነው' ይጣላሉ:: እርሷ ቆርቆሮውን ይዛ ወደቤቷ ታመልጣታለች:: ከዚያም በአጥር ሲሰዳደቡ 'ዲቃላ' ትላታለች:: -አሰገዱ::

"ሂች! ዲቃላስ አንቺ" ትላታለች መልሳ::

"እኔ እንዳንቺ አባት የሌለኝ መሰለሽ! ዲቃላ" አለቻት አሰገዱ ከልጅ ሳይሆን ከአዋቂ የሚሠነዘር በሚመስል አስቀያሚና ሞጥሟጣ አንደበቷ::

"ው.. .ይ! ሥራ ሄዶ ነዋ! የኔ አባት ውጪ ነው የሚሠራው::" ትላታለች ዳርምየለሽ::

"ማ? ጋሽ ባህሩ? እሳቸው እኮ ያንቺ አባት አይደሉም:: አንድ ቀን እኛ ቤት መጥተው ላባቴ ሲያወሩ ሰምቼ የለ::"

ከዚያ በኋላ ዳርምየለሽ ብሽቅ ብላ ሌላ ስድብ ብትሰድባትም አሰገዱ ግን እንደመዝሙር እየደጋገመች

"ዲቃላ ዲቃላ ዲቃላ

ዲቃላ ዲቃላ ዲቃላ !" በማለት የበለጠ አናደደቻት:: እያለቀሰች ወደ ቤት ገባችና ለእናቷ አሰገዱ 'ዲቃላ' ብላ እንደሰደበቻት ነገረቻቸው::

"ታዲያ ብትልሽስ ምን አስለቀሰሽ!"

"ዲቃላኮ ማለት አባት የሌለው ልጅ ማለት አይደል?"

"ታዲያ አንቺ አባት የለሽም? !" አሉ በቁጣ ፊታቸው ተለዋውጦ::

"እንጃላቷ 'ዲቃላ' እያለች ትሳደባለች"

"በይ ሁለተኛ እንዲህ ስትይ እንዳልሰማ እሺ!" በማለት አስጠነቀቋት::



አሰገዱንም ሁለተኛ 'ዲቃላ' ብላ ብትሰድባት ለአባቷ ነግረው እንደሚያስገርፏት አስፈራሯትና አስታረቋቸው:: ቢሆንም ዳርምየለሽ በአሰገዱ ላይ ከልጅነት የቋጠረችው "ቂምና ጥላቻ" እስካሁን አልተፈታም::

ይህ ብቻ አይደለም:: በታናናሾቿ የልደት ቀን ልብስና ጫማ ገዝተው የሚመጡ አንዳንድ የአቶ ባህሩ ዘመዶች የእርሷን የልደት ቀን ከነመኖሩም መርሳታቸው፣ አንዳንዴ ሊጠይቋቸው ሲመጡም ለከረሜላና ብስኩት መግዣ የሚሰጧቸው ሳንቲም ሳይቀር ለርሷ አነስ ያለ መሆኑ፣ እርሷም ዘና ብላ ያለመቅረቧና ሌላው ሌላውም እንቆቅልሽ ሆኖ ሲያስከፋት ያደገችበት ጥቃቅን ነገር ሁሉ አሁን የተፈታ ይመስላታል::

"ታዲያ አባቴ ማን ነው?" ትላለች በሃሳቧ ጮክ ብላ:: ቀኛዝማች ከፍያለው ግንባራቸውን እያጠፉ ጭራቸውን እየነሰነሱ ይመጡባታል:: አባቷን ይነግሯት ይመስል::

"ግን ለምን አልጠየቅኳቸውም? አባቴ ማን ነው? 'አሳ ጐርጓሪ ዘንዶ ያወጣል' ትልና እርሳቸው ጋ የሄደች ዕለት ያጋጠማትን ሁሉ እንደገና ታስባለች::"

♣ ♣ ♣

የሥራ ማስታወቂያፍለጋ ከአንዱ ሥፍራ ወደ ሌላው ስትዞር እንደዋለች እግረ መንገዷን ባሻ ወልዴ ችሎት ሠፈር ወደሚገኘው ቤታቸው ጎራ አለች:: ቀኛዝማች ባለቤታቸው የሞቱት ገና ከለውጥ በፊት ቢሆንም ባህርማዶ ያሉት ሁለቱ ልጆቻቸው ከሚልኩላቸው ድጐማ ጋር በሚያገኙት ጡረታ እየታገዙ ሠራተኛ ቀጥረው ጥሩ ኑሮ ነው የሚኖሩት:: ምሳዋን ያለሃሳብ በልታ ወደ በረንዳው ወጡና የማይጠገብ ጨዋታቸውን ሲታዳምጥ ዋለች:: ጀምበር ዘቅዝቅ ስትል በመሀከላቸው በተፈጠረው የዝምታ ፋታ ሽቅብ ወደ እንጦጦ አቅጣጫ ያነጣጠረውን የቀኛዝማች ገጽታ ባክብሮትና በፍቅር አስተውላ ነፍስ ካወቀች ጀምሮ ስታሰበው የነበረ አንድ ጥያቄ ጠየቀቻቸው::

"አባባ?"

"አቤት ልጄ!" አሉ ከሰመጡበት ሀሳብ ይሁን ትዝታ እንደመባነን ብለው::

"ለምንድነው እኛ ቤት የማይመጡት? እኔ እስከማውቀው አንድም ቀን እኛ ቤት ሲመጡ ትዝ አይለኝም::"

"ተይኝ ልጄ አጉል ጥያቄ ነው" አሉ ቀኛዝማች::

"እንዴት? ዘመድ ለዘመድ እኮ ሲጠያየቅ ነው ወግና ማዕረጉ:: እናቴስ ብትሆን ከርስዎ በስተቀር ማን ዘመድ አላት?"

"ምነው እየመጣች ትጠይቀኝ የለም ታዲያ!"

"እሷማ ትጠይቅዎታለች::ለምን እርስዎ እኛ ቤት አይመጡም አልኩ

እንጂ”

“እዚሁ ሆኜ በፀሎት እገኛችኋለሁ፡፡” አሉና ድንገት ፊታቸው ተለዋወጠ፡፡

“እኔ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ቢመጡ እንዴት ደስ ይለኝ ነበር!” አለች በገጽታቸው መለዋለጥ ብትደነግጥም አንዴ ያሰበችው ሆነና አፏን ተቆጣጥራ ነገሩን ለመተው ተስኗት፡፡ ከዚያ ወዲያ አነርሱ ቤት ስለመምጣታቸው ምንም ነገር ላታነሳባቸው በልቧ ወስናለች፡፡

ቀኛዝማች ግን የቁጣ ስሜታቸውን ሲተናነቁት እያስታወቀባቸው “አይ ልጄ አንቺ እማታውቂው ብዙ ነገር አለ፡፡” አሉና ጭራቸውን ነስነስ ነስነስ አያረጉ ትንሽ ከተከዙ በኋላ፣ “ያ! አርጉም እንጀራ አባትሽ . . .” ብለው ሲጀምሩ ጆሮዋን መብረቅ የመታት ያህል ባረቀባት፡፡ -ድምጻቸው፡፡

በቃት፣ ከዚያ በኋላ የሚያወሩትን አትሰማም፡፡ የሰማችበት ጆሮ የእርሷ መሆኑን፣ የሚናገረው ድምጽ የእኒያ የምትወዳቸው አና አጠገቧ ያሉት የአባባ ከፍያለው መሆኑን ተጠራጠረች፡፡

ሰውነቷ ቀዝቅዞ ልቧ ብቻ ከውስጥ አየነጠረ ደረቷን ሲደበድብ በርቅሶት የሚወጣ መሰላት፡፡ በውስጧ ያደገው የአባባ ከፍያለው አባታዊ ፍቅር ወጥቶ በምትኩ ቅያሜና ጥላቻ ሲያቆጠቁጥ ተሰማት፡፡ በክፉ ቃል የተሚሸ ጆሮ ደግ ቃል አይገባውም፡፡ አይሰማም፡፡ ቢሰማም እንኳ ገልብጦ ነው፡፡ ቀኛዝማች ይናገራሉ፤ እርሷ ግን አትሰማም፡፡ አልፎ አልፎ ብቻ “አጐትሽ እንደታመመ ሰምን ነው፡፡ . . አንቺ ገና ተረግዘሽ. . . . አፈር ይብላና ሊበላ ብሎ. . . . . ምናምኒት ሳይይዝ ገብቶ. . . . አንድ ነገር አቅምሷት እንጂ. . . . ከሞላ ቤት. . . በገዛ ቤቱ እሱን ኩሸና ጥለው. . . እብድ ተብሎ ሲቀር. . . ጠበል እንኳ ማንን ገደለ?. . . እንዴት . . . ብዬ ብለው. . . ‘አትፈትፍት’ ይበለኝ!? በሉ አፍ!. . . እኔ ከፍያለው በዘመኑ የተከበርኩ የተፈራሁ. . . አሁንም ቢሆን . . . ” የሚሉትን ቁርጥራጭ ቃላት ብታስታውስም ትርጉማቸው ‘ያ! እንጀራ አባትሽ’ ነው የሆነባት፡፡

በአግባቡ እንኳን ሳትሰናበታቸው ወሬአቸውን አቋርጣ ወደ ቤቷ በረረች፡፡ ክብድ ያላትን፣ ግንባሯ ላይ የተቋጠረ ደመና ተሸከማ፡፡ ‘. . . እንጀራ አባትሽ. . .’ የሚለው ነጐድጓድ እያምባረቀባት፡፡

“እንጀራ አባትሽ -እንጀራ አባትሽ -እንጀራ አባትሽ. . .”



# 6

ጠዋት እንዳለ በስልክ የሰጣትን ቀጠሮ ብትቀበልም ደስተኛ አልነበረችም፡፡

“ለምን እሺ አልኩት?” ትላለች ደጋግማ፡፡ ለራሷም መልስ ያጣችለት ጥያቄ፡፡ እንደሰሞኑ ሁሉ ምክንያቷን ደርድራ መቅረት ትችል ነበር፡፡ ግን ለምን ትቀራለች? እንዳለ እኮ ነው፡፡ ቢቀየማትስ? እንኳን ለእርሱ ለማንም ማፍረስ የማትወደውን ቀጠሮ ለሦስት ጊዜ አሳከበረችም፡፡ እንደርሷ መውደድ በየደቂቃው ብታገኘው ደስ ይላታል፡፡ ጭንቅ በሚያደርግ የፍቅር አስተቃቀፍ ደረቱ ላይ ለጥፎ በሚያስለመልም ስመመን ከክንዶቹ መሃል ድብቅ ቢያደርጋት ትመርጣለች፡፡ ብታገኘው ጭንቀትና ብስጭቷ የሚለቃት ይመስላታል፡፡ ለዚህም ነው በስልክ ሲያናግራትና ሲቀጥራት እምቢታ የሚከብዳት፡፡ ሆኖም ስልኩን ስትዘጋው በተለይም የቀጠሮው ሰዓት ሲቃረብ ፍርሃት ፍርሃት ይላታል፡፡ እንዴት ብላ ቀጠሮው ቦታ እንደምትደርስ፡፡ ሰዉም መንገዱም ታክሲ መኪናው ሁላ፡፡

‘ዲቃላ-ዲቃላ- ዲቃላ’

‘ዲቃላ-ዲቃላ-ዲቃላ’ እያለ የሚጠብቃትና የሚያፌዝባት ይመስላታል፡፡ እንደ አስገዱ እንደ ልጅነት ፀባቸው፡፡ -በህሳቧ፡፡ እናም ቀጠሮዋን ስትወድ እንደጠላ ትሠርዛለች፡፡

ዛሬ ግን መሄድ እንዳለባት ወሰነች፡፡ የአራት ዓመት የፍቅር ህይወቷ፣ ያለፈው ብቻም ሳይሆን የወደፊቱም ተስፋና ውጥኗ እንዳይቋረጥ ሰጋች፡፡ እንደዋዛ የገባችበት የፍቅር ወጥመድ ስሜትና አካሏን ጠላልፎ ከተዋሃዳት፤ ወጥመድነቱ ሳይሆን ፀጋን የተላበሰ የመንፈስ ነፃነትነቱ ከተሰማት በኋላ እንደዋዛ እንዲፈታባት አልፈለገችም፡፡ የተገናኙበት አጋጣሚ በሃሳቧ እየተመላለሰ መለየትን ስታስበው ባር ባር አላት፡፡

# 7

፩

በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ነበረች። የከሰዓት በኋላ ፈረቃ ትምህርቷን ጨርሳ ወደ ቤቷ ስትመለስ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን አጠገብ ሁለት ሆነው ቆመዋል። ከአንዳንድ ሁኔታቸው ሆን ብለው እንደጠበቋት ቢገባትም ተዋጊ በሬ ይመስል ቀንዷን ሰጥታቸው አለፈች። አፏጨላት። እንዳላወቀ ተከሳትራ መንገዷን ቀጠለች። ጥቂት ርምጃዎች እንደቆጠረች ከኋላ ነካ አደረጋት። ዞር ብላ እንኳ ሳታየው ትከሻዋን መንጭቃ ርምጃዋን ጨመረች። ክንዷን ያዝ አድርጎ አስቆማት።

"ሲጠሩሽ አትሰሚም እንዴ?" ሲል ከድርጊቱም ይልቅ ጉሮሮ እሚከረክር ድምጹ አናደዳት።

"ለምንድነው እምትጠራኝ?እጄን ልቀቅ!" አለችው ተቆጥታ።

"አልለቅሽም ምን ያስቆጣሻል? እንደ ፋራ አትሁኝ!"

"እንደምንም ልሁን" ፊቷ ላይ የተፈነጣጠቀውን ርጥበት እየጠራረገች በጥርጣሬ ወደ ሠማይ አንጋጠጠች። ካፊያ ቀርቶ ደመና እሚሉ ነገር የለም።

"ምን መሰለሽ. . ." አለ። ዳርምየለሽ አሁንም ፊቷ ላይ ፍንጥቅጣቂ ሲያርፍባት ነገሩ ገባትና ዓይኖቿን ገጹ ላይ አሳረፈች። ሲያወራ የላይኛው ከንፈሩን ወደ አፍንጫው አግልሎ እኔ ልቅደም የሚል ጥርስ። "ገጣጣ! ምናለ አፉን ባይከፍት" አለች በሆዷ አሁንም ድምጹ እየቀፈፋት።

"ምንም አይመስለኝም" እጇን መነጨቀችው። እንደገና ያዛት።

"እሺ ምንድነው እምትፈልገው?" ልታናግረው ፈልጋ ሳይሆን ችክ ስላለባት ቶሎ ለመገላገል። ጓደኝየው ራቅ ብሎ በመቆም ሰረቅ እያደረገ ሲያይ ተመለከተችው። በምን እንደሆነ ባታውቀውም ከሚያናግራት ችኮ ጋር ስታነፃጽረው ጨዋ መስሎ ታያት። እንዲያውም ዓይኑ ከዓይኗ ተጋጠሙና አንገቱን ሰበር አድርጎ ዞረ።

"በመጀመሪያ እንተዋወቅ! ሀብታሙ ወልደገብርኤል እባላለሁ።ጋዜጠኛ ነኝ!" አለ። ሁልጊዜም ሰው ሲተዋወቅ ጋዜጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ይቸኩላል። እንደዚያ በማለቱ ክብርና ዝናን የሚያተርፍ እየመሰለው።

"ታዲያ ምን ይጠበስ? ጋዜጠኛ ምንድነው?" አለችና በልቧ "ጥሩ ነው" አለችው።



"ያንቺስ ስምሽ ማን ይባላል?"

"አትቀመስ" አለችው ዘና ብላ በንቀት እያስተዋለችው።

"አትቀመስ? የውሸት የውሸት ይመስላል" አለ ዝናቡን እያርከፈከፈ።

"የውነት ስሜ ነው" አለች፣ በልቧ "ቀፋፊ!" ብላ ተሳድባ።

"ይልቅ የምርሽን ንገሪኝ?"

"ይልቅ አትትፋብኝ" ብትለው ትወድ ነበር። ለአፏ ግን "የራሴን ስም የማውቀው እኔው ነኝ። አይደለም ካልክ አንተ የምታውቀውን ንገረኝ"

"እሺ ይሁን ግን ምን አስሸሸሽ?"

"መቼ ሸሸሁህ?"

"ማለቴ እኔ ፍቅርሽ. . ." ብሎ አፉ ሲጋመድ

"እ!?" አቋረጠችው። "የምን ፍቅር? በል ልቀቀኝ።" አለችና በእልህ መንጭቃው ሮጠች። በብሽቀት እያጥላላትና እየተሳደበ ቀረ።

በማግስቱ በዚያው ሰዓት በዚያው ቦታ ሀብታሙ ሳይሆን የ በርቀት ሲመለከታቸው የነበረ ጓደኛው ብቻውን ቆሞ ጠበቃት። የጉንዮሽ አይታው እንዳላየ ዘግታው አለፈች። እርሱም ምንም አላላት። በማግስቱም ለሁለተኛ ጊዜ ብቻውን ቆሞ ጠበቃት። አሁን ካሁን ይለከፈኛል ብላ እንደጓደኛው 'አልፈልግም' በማለት ልታሳፍረው ተዘጋጀች። እንዴት ተከሳትራ እንዴት እንደምትሰድበው ከዚያም እንዴት እንደምታመልጠው ስታስብ ቃል ሳይተነፍስ በማየት ብቻ ቆሞ አሳለፋት። በተመሳሳይ ሁኔታ ምንም ምንም ሳይላት በዓይን ብቻ ተቀብሎ እየሸኛት ሁለት ወራት አለፉ።

በዚያ ሁለት ወር ጊዜም እያደር ሳይታወቃት ከትምህርት ቤት እንደወጣች ቅድስት ማርያም አጠገብ ዓይኗ የለመደውን አንድ ነገር ማየቷ እንዳይታወቅባት በጥንቃቄ ሠረቅ አድርጋ መፈለግ ጀምራለች። ቀጠን ብሎ እጅግም ባልረዘመና አጭርም በማይባል መጠን የተዋቀረ ቁመና ያለው፤ ሳሳ፣ ቀላ ያለው ፀጉሩ ከወደ ግንባሩ ወደፊት ቀደም ያለ፤ ቀይ፣ ጥቁር ወይንም ጠይም ለማለት የሚያስቸግር፤ ነገር ግን በጠይምና በቀይ ዳማ መካከል ያለ ደብዛዛ መልክ፤ የሰካራም የሚመስል ሸካራ ገጽታ።

ታድያ አንድ ቀን፤ የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ፈተና ሰሞን ከተለመደው ቦታ ሳታገኘው ቀረች። ወደ ግራም ወደ ቀኝም የጉሪጥ ማየቷን ትታ በሙሉ ዓይኗ ፈለገችው። -የለም። ወደማትቀርበት ቤቷ ስታዘግም ቅር እያላት ነበር። ለምን እንዲያ እንደተሰማት ግን ለራሷም ገርሟታል። ብቻ ማምሻዋን ሁሉ ዕቃ እንደረሳ ወይንም እንደጠፋበት ሰው ልቧ ድንግጥ ድንግጥ ሲል አሳለፈችው። ሌሊቱንም ስትቃዥ።

አንድ የማታውቀው ቦታ ላይ ነው። መንገድ ለመንገድ ያሯሩጣታል። -ልጁ። ያ! ቅድስት ማርያም አጥር ሥር ይጠብቃት የነበረው። እርሷ እጆቿን

# 8

ህሊናዋን ወጥሮ ካስጨነቃት ህሳብ ላንድ አፍታ ተገልላ በእንዳለና በራሷ ፍቅር ትውስታ እንደተጋረደች ልብሶቿን ቀየረችና ማበጠሪያዋን ይዛ ከአሮጌው የልብስ ቁምሳጥን ሰንጣቃ መስታወት ፊት ለፊት ቆመች:: የከሳ የገረጣ ገጽታ፣ በልኩ የተሰፋለትን ቀሚስ ሳይሆን ሽንሽን ጣቃ ያንጠለጠለ የሚመስል ቁመና:: ከመስታወቱ ላይ የምታየው ምስል የራሷ መሆኑን ለመጠራጠር ባትደርስም ሁኔታዋ አስደነገጣት::

"ባስራ አምስት ቀን ይኼን ያህል! ምን ነካኝ?" አለች በራሷ ላይ ያየችው ለውጥ ተዓምር ሆኖባት:: ወትሮም ወፍራም አልነበረችም:: እንደዚያ ከስታ ግን አታውቅም:: ያልከሱና ያልተለወጡት ረዥም ጠጉሯ፣ ክርክም ያለ ቅንድቧ እና የጥርሷ ፍንጭት ብቻ ናቸው::

በግራና ቀኝ ትከሻዋ የተዘናፈለ ጠጉሯን በእጇ በተን አድርጋ ተመለከተችው:: በደህና ሁኔታ ላይ ነው ያለው:: አንገቷን ሰበር አድርጋ የፕላስቲክ መላጊያዋን ሰካችበት:: ከመላው አካላቷ ለፀጉሯ ያላት ፍቅር ለብቻ ነው:: መቼም ይሁን የት ሥራ ፈትታ ከተቀመጠች ፀጉሯን ማበጣጠር አለዚያም መነካካት ትወዳለች:: ሰሞኑን እንኳ ከህሳቧ ጋር ስትገምድና ስትፈታው በመሰንበቷ እንደሌላው ሰውነቷ አልተጐሳቆለም::

"የት ለመሄድ ነው ይሄ ሁሉ ሽር ጉድ? እሱ እንደሆነ እንኳን እንደዚህ ሆኜ ትንሽ ለወጥ ካልኩ ጥያቄው መከራ ነው:: ምን ሆንኩኝ አለዋለሁ? መቼም ያለአንድ ምክንያት እንዳልከሳሁ ይገባዋል::"

"በስልክ እንደምለው ታምሜ ነበር ልለው? ምንሽን? እንዴት ያረግሻል? ማለቱ አይቀርም:: ምን ብዬ እመልስለታለሁ? ሰውነቴስ እሺ፤ በተቅማጡም በትውከቱም ከሳ ልበለው:: ፊቴን ጨለማ አስመስሎ ቅስሜን ስብር የሚያደርገውንስ ምንድነው ልለው ነው? ነው ወይስ ግልጽ አድርጌ 'ራሴን ያመኛል፣ ሰውነቴን ይጫጫነኛል፣ ምግብ አልበላሽ፣ ሰው አልጥምሽ ብሎኛል:: ያበሳጨኛል:: ጨሂ ጨሂ ይለኛል::' ልለው ነው? ከዚህ ሌላ ብዋሽ ያውቅብኛል:: እርሱ እንደሆነ ህኪም ይመስል ምርመራው አይጣል ነው::



እንዲያውም ገና ሲያየኝ ሊገባው ይችላል::" አለችና ፊቷን በመስታወቱ ትክ ብላ አየችው:: መልኳ ራሱ የሚያስታውቅ መስሎ ተሰማት:: -ዲቃላነቷን::

'ዲቃላ ምን ይመስላል?' -አታውቀውም:: ብቻ ዲቃላ እንደምትመስል ይታያታል:: ዓይኗ ይሁን ጥርሷ ላይ፣ አገጯ ይሁን ግንባሯ ላይ፣ የት ላይ እንደሆነ ለይታ ማወቅ ባትችልም ዲቃላነቷን የሚገልጽ አንዳች ሁኔታ ይታያታል:: አሁን ወደ እንዳለ ስትሄድ በመንገድ የሚያገኟት ሁሉ ፊቷን አይተው በማወቅ ሲጠቋቆሙና 'አባቷን የማታውቅ ዲቃላ' እያሉ ሲያሸሟጥጧት አንዳንዶቹም አካላዊ ጉስቁልናዋን አይተው በህዘኔታ ከንፈራቸውን ሲመጥጡላት ታሰባት:: ዓይኗን ጭፍን አረገች:: በመስታወቱ ውስጥ ያለችውን ዳርም የለሽ ላለማየት:: ጭው ብሎ ዞረባትና ወደኋላ ተንገዳግዳ በርከክ አለች:: -እንዳትወድቅ::

# 9

አራት ሆነው ከትምህርት ቤቹ እንደወጡ ተንደርድሮ መሃላቸው ገባና ለቀም አድርጎ ያዛት። አብረዋት የነበሩ ጓደኞቿ ጭልፊት እንዳየ ጫጩት ተፈጥፍጠው ሲበተኑ እርሷ ደብተሯን በቁሟ ለቀቀችው። ብትንትኑ ሲወጣ እያየች ለማንሳትም ሆነ ለመነቃነቅ አልቻለችም። በገዛ ሹራቧ አንገትጌ የማነቅ ያህል ግጥም አድርጎ ይዟታል።

"ምን አደረኩኝ?" አለች በፍርሃት ተንቀጥቅጣ።

"ምን አረኩኝ? እናትሽ ትወቃ! የምረሳው መሰለሽ?" አለና የሹራቧን አንገትጌ ባነቀበት እጁ አገጯን ደጋግሞ ገጫት። ለመጠባበቂያ ቀኝ እጁን ቡጢ አስጨብጦ ወደ መሬት ወድሮታል።

ልጅቷ የባሰ እንዳይመጣ ፈርታ ልምምጥ ያዘች። "እሺ! ምን አጠፋሁ? አጥፍቼም ከሆነ ሁለተኛ አይለምደኝም።"

"እናትሺንና! ዛሬ ቀሚስሽን ገልቤ ነው እማስጣሽ።"

"ውይ! ውይ! ውይ! ለምን? የፈለግሽውን ላድርግልሽ። ገንዘብም ከሆነ. . ."

"ገንዘብ? እናትሽንና የምን ገንዘብ ነው እሱ?. . . እሺ ግን ስንት?"

"ሦስት ብር ናት ያለችኝ" አለች ልጅቷ መሬት የወደቀውን የስክሪብቶ መያዣ ባይኗ እየማተረች።

"እሱን ለእናትሽ ስጫት! እሺ! አሁን ከእኔ ጋር ትሄጃለሽ አትሄጅም?"

"ወዴት?"

"ወዴትም ይሁን"

ልጅቷ እሺም እምቢም ሳትል በፍርሃት ተውጣ ዝም አለች።

"ካለበለዚያ እዚህ ሁሉ ሰው መሃል እንደናትሽ ነው -ምስራሽ። በይ ቶሎ! ቀጥ ብለሽ እኔን መከተል ወይንም ቂጥሽን ተገልበሽ ለህዝብ ማስመረቅ።" ብሎ አንገቷን ለቀቀና ቀሚሷን ሳብ ሲያደርግ፣ "እሺ!" አለች ያለውዷ ቀሚሷን እየተከላከለች።

"እሸውዳለሁ ብትይ ጥርስሽን ነው የማስቆጥርሽ።"

ልጅቷ ደብተሯን ሰብስባ ተከተለች።



ከአንድ ቡና ቤት ገብተው ተቀመጡ። ወዲያው ከኋላ ሲከተላቸው የነበረ አንድ ጐረምሳ ገባና ሦስተኛው ወንበር ላይ ተቀመጠ። ልጅቷ የመጣችበት ምስጢርም ገባት።

"ስንት ሰዓት ነው?" አለችው ሳቢ እንደ ወንድ የጠቀለለችውን የጃኬቷን እጅጌ ወደ መዳፏ እየበተነች።

"ለአሥራ አንድ ሃያ ጉዳይ" አለ ጐረምሳው።

"አ! ሃያ ጉዳይ? እኔ ልሂድ ተጫወቱ።" አለችና ወዳመጣቻት ምርኮ ዞራ "አንድ መነጫነጭ የለም። እፈነግላለሁ ብትይ . . ." አለችና ቡጢዋን አሳይታት ወጣች። በወንዳወንድ አረማመዷ እየተጣደፈች።

♣ ♣ ♣

አሰገደች መኩሪያ ወንዳወንድ ቅርጽና አለባበስ ያላት፣ በሴት የቁመት ንጽጽሮሽ 'ረዘም ያለች' የምትባል ናት። ከርዳዳ ፀጉሯን አጭር አፍሮ አበጥራ የወንድ ጃኬት ወይንም ሸሚዝ ከሱሪ ጋር በመልበስ በአደባባይ ስትጀነን፣ ለሚያውቋት ካልሆነ በስተቀር ወንድ ተብላ የምታሳስት ናት። ከአካላዊ አወቃቀሯ መሃል ጐልቶ እሚታይላት ውበት ቢኖር በጥቋቁርና ሸካራ ከናፍሯ መሃል የምሽት ደመና እንደሚሰነጥቅ መብረቅ ብልጭ የሚለው ጥርሷ ብቻ ነው። ቡተረፈ ብዙ ወንዶች የሚወዷትና የሚያቀርቧት በወንዳወንድ ድርጊትና ሁኔታዋ ነው። እንደ ወንድ ጓደኛቸው በማየት። በተለይ ሴት የመቅረብ ዓይነ ጥላ ላለባቸው ወንዶች ጥሩ መሰላል ናት። ተፈላጊዋ ልጃገረድ የምኒልክም ትሁን የዩኒቨርሲቲ ተማሪ፣ የአራት ኪሎም ትሁን የሌላ ሠፈር ልጅ የአራት ኪሎን ጐዳናዎች ረግጣ አስካለፈች፣ ሲሆን በመግባባት እና በማታለል፣ እንዲያ ካለም በጉልበት ተጠቅማ ለፈላጊዋ ታስረክባለች።

አሰገደች መኩሪያ በጥላቻም ሆነ በመውደድ ያለፈ ያገደመው ድርጊቷን አይቶ ከሚሰጣት ተባራሪ ሥም ሌላ በሁለት ስሞች ትታወቃለች። አንደኛው ራሷን በራሷ የምታስተዋውቅበት 'ሳቢ ገርል' ሲሆን በሰፈው የምትጠራበት ሌላኛው ስሟ ደግሞ ራሷን ከምታስተዋውቅበት ስም 'ገርል' የሚለውን በመቀየር ወንድ ጓደኞቿ 'ሳቢ ጋይድ' ብለው በሰየሟት ነው።

ከአራት ኪሎ አንስቶ በስድስት ኪሎ እስከ ሸሮሜዳና ፈረንሳይ ለጋሲዮን፣ በቀበና መስመር እስከ አቧሬና ሾላ፣ በፒያሳ እስከ አራዳና አካባቢው፣ ብቻ በየአቅጣጫው በዓይን ማወቅ ቢቀር ስለ እርሷ ያልተሰማበት ሠፈር የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም።

"አራት ኪሎ. . . . አለች አሉ" እየተባለም ቢሆን።

አራት ኪሎ ከየአቅጣጫው የሚመጣ ኩተሜም ሆነ ገጠሬ ሳይረግጣቸው

ከማይውሉት የአዲስ አበባ ሠፈሮች አንዷ ናት:: የአራት ኪሎና አካባቢዋን መንገዶች ከወዲያ ወዲህ በመመላለስ አለዚያም መንገድ ዳር ተገትሮ ግራና ቀኝ መንገደኛን በመላከፍ እግር ሲቆጥሩ በመዋል ደግሞ ሳቢ ጋይድን የሚወዳደር የለም:: ስለዚህ እንደ ጥሩ ተግባር ዝናዋ በከተማው ወጣቶች በአድናቆትም፣በትችትም፣በጥላቻም፣እንደየተመልካቿ ስሜትና አስተያየት ተጋንኖ ይወራላታል::

ፍ

ይሁን እንጂ ገና በፈጣኑ ፣የአጉጠጉጤ ዕድሜዋ ሥራዬ ብላ የጀመረችውን ወንዳወንድነት ወጣት ልጃገረዶች በተለይም አብሮ አደግ እኩዮቿ አይወዱላትም::

"ሲታሰጠላ! አማረብኝ ብላ ነው?" ይሏታል ለመጀመሪያ ጊዜ ያዩዋት::

"ወዳ መሰላችሁ? ሴት ልሁን ብትልና እንደሴት ብትለብስ ስለማያምርባት እኮ ነው" ሌላም ሌላም ይሏታል ነገረ ሥራዋ የሚያናድዳቸው:: -ሳትሰማ:: ከሰማችማ የት ሊገቡ:: ንክሻና ቡጥጫ አታውቅም:: -እሱ እሱ 'የሴት' ነው:: በቦክስ፣ በቴራና በጥፊ ስትማታ 'ምን ወንድ. . .' ታሰኛለች:: በተለይ ልጅቷ ረዥም ፀጉር ካላትማ ተመቻት:: ጥቅልል አድርጋ በመያዝ እያሽከረከረች መርገጥ ነው:: በዚያ ላይ ካፏ የሚወረወረው ልቅ ቃል ከዱላ የበለጠ ይፈነክታል:: በሰው መሀል እንዳገኘች ስትዘረጥጥ መሬት ትቀብራለች:: ባጠቃላይ ፀቧ ለሴት ቀርቶ ለወንድ ያስፈራል:: ለዚህም ነው ወጣት ልጃገረዶች በመግባባትና በሰላምታ የሚይዟት::

ወታደሩ አባቷ አምሳ አለቃ መኩሪያ ከሶማሌ ጋር በተደረገው ጦርነት ወቅት የወደቁት ገና በዕድሜዋ የአሥራዎቹን መጀመሪያ አጋማሽ ስታገባድድ በመሆኑ ከእናቷ ከወ/ሮ ፋናዬ በስተቀር ተቆጭ የላትም:: እርሳቸውም ቢሆኑ በርሷ የተነሳ ስሞታና ክሱ ሳያንሳቸው ግልምጫና ስድቧ ስልችቷቸው ትተዋታል::

"አብይኝ አልኩሽ አጠጪኝ? ያባቴ ቤት እኮ ነው:: እንደፈለገኝ መሆን እችላለሁ::" ስትላቸው "እንቺን ማን ይችላል እቴ!" ብለው ዝም ነው::

አንድዬ ልጃቸው በመሆኗ በተፈጥሮ የእናትነት ስሜት ይውደዷት እንጂ ከህፃንነቷም ቢሆን ገና አፏን መፍታት ስትጀምር ንግግሯ እንደ ልጅ ከሚጣፍጣቸው ይልቅ እንደ አዋቂ ያስፈራቸውና ይመርራቸው ነበር::

ከዕድሜዋ በላይ ነገር ስታሳካና ስትሞጣሞጥ የሚያዩዋት ሠፈርተኞችም "ይች ከፍ ስትል አትቻልም!" ይላሉ ::



"ኧረ! እንደው እሷስ የልጅ ለዛም የላት! ጥቁር ምላስ ናት! . . ." ሌላም ሌላም እያሉ ያጥላሏት ነበር:: ካደገች በኋላም ቢሆን እሁን በምታሳየው ሁኔታ 'ጉድ' ብለው አላበቁም::

እርሷ ግን ለማንም ደንታ የላትም:: ውሎዋ ከወንዶች፣ ድርጊቷ እንደወንዶች ነው:: ወንዶች ከሚፈጽሙት ድርጊት ሁሉ የሚቀራት ቢኖር አንድ ነገር ብቻ ነው:: እርሱንም ስላልፈጠረላት:: በተረፈ ሴት የሚባል ጓደኛ የላትም:: "ሴትና ቀሚስ አይሆነኝም" ማለት ታበዛለች::

## 10

ከወደ ጥግ ተቀምጦ ሲጋራውን በሻይ እያፈራረቀ ይምጋል:: ለአራት አመታት የቋጠረውን ፍቅርና ትዝታ በሀሳብ ጥርስ እያመነዠከ:: ሳይገናኙ ባሳለፏቸው አሥራ አምስት ቀናት ከልቡ ያደረውን ቅሬታም በቅናትና በቁጭት ጥርስ እያኘከ በፍቅር፣ በምህረትና በናፍቆት ትንፋሽ ይውጠዋል::

'ያም ሆነ ይህ ዓይኗን ልየው' ይላል የሀሳብ ፍጭቱ ማሳረጊያ:: ሰዓቱን ተመለከተ:: አሥር ሰዓት ከአምስት:: ቀጠሯቸው አስር ሰዓት ቢሆንም ሩብ ጉዳይ ሲል ነው የደረሰው:: ገና እንደገባ ሰው ዙሪያውን ቃኘት አደረገ:: ባለ ሦስት እግር ጠረጴዛዎቹ በሁለት፣ በሦስትና ከዚያም በላይ በሆኑ ተጠቃሚዎች ከበብ ከበብ ብለዋል:: አንዳንዶቹ አፍና ጆሮ ተጋጥመው ይንሾካሾካሉ:: ሌሎች ደግሞ ከጫጫታው በላይ ለመደማመጥ ይጮሃሉ:: የቡናው ማሽን አከታትሎ ቁና ቁና ይተነፍሳል:: በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረው ሙዚቃ በሌላው ሀብረ ድምጽ ተውጦ ሀልም ሀልም ይሰማል::

እርሱ ብቻ፣ ብቻውን ከራሱ ሲሟገት እንደቆየ ተሰማው:: ከርሱ ሌላ፣ ምን እንደሚያስብ ባያውቅም 'ተሼ ስልከኛው' ብቻ ነው በብቸኝነት የተዋጠ:: ዓይኖቹን ገንዘብ ተቀባይዋ አጠገብ ወዳለው ስልክ እንዳነጣጠረ ማጅራቱን አጥፎ በግራ እጁ መዳፍ እያሻሸ መግቢያው ላይ ተቀምጧል:: -ተሼ ስልከኛው::

"ስለምን ይሆን የሚያስበው?" ብሎ አሰበና ትክ ብሎ ተመለከተው:: -እንዳለ::

"እብድ ስለምን ያስባል? ስለዕብደቱ ወይስ ስለጤንነቱ? ማን ያውቃል:: እኛ ዕብድ ብለን የምናገልላቸው ሰዎች፣ የራሳቸው ጤንነት፣ የራሳቸው በጐና ጥልቅ ስሜት ይኖራቸዋል:: ምናልባትም ከእኛ የተሻለ:: ማን ያውቃል:: እኛ እነርሱን እብድ እንደምንላቸው እነርሱም እኛን ዕብድ አድርገው ያዩን ይሆናል:: ለእብድ ሰው ጤነኛው ዕብድ ነው::. . ."

አስተናጋጁን ጠራና ለራሱ ሻይ ለተሼ ስልከኛው ቡና እንዲሰጠው አዘዘ:: አሥር ሰዓት ከመሙላቱ በፊት እንደ ዓመታት የረዘሙበት ደቂቃዎች



ካለፉ በኋላ ከሰከንድ ባነሰ ፍጥነት በረሩበት:: -የቀጠሮ ሰዓት:: የእጅ ሰዓቱ ለአሥራ አንድ ሃያ ጉዳይ ሲያመለክተው ማመን አልፈለገም:: ጊዜ ቆየኝ አይባል:: ገና ቢሆንና ሰዓቱ ሲደርስ እንድትመጣ ቢመኝም ጊዜ የሚራመደው በራሱ እንጂ በእንዳለ ፈቃድ አይደለምና ወደ አሥራ አንድ ሰዓት መቁጠሩን ቀጠለ:: -ሩብ ጉዳይ::

"ምንድነው የምጠብቀው?" አለ በሃሳቡ፤ ከሰዓቱ በላይ እንደ ዋዛ ያሳለፈው አርባ አምስት ደቂቃ ውጤት አልባነት ተሰምቶት:: ብትመጣ ኖሮ ከአስር ሰዓት አታሳልፍም ነበር:: እንዲያውም ከሚወድላትና ከሚያደንቅላት ባህሪያት ቀዳሚውን ሥፍራ የሚሰጠው ለጊዜና ለቀጠሮ ያላትን አክብሮትና የአጠቃቀም ችሎታ ነው:: ካለፉት አሥራ አምስት ቀናት ለውጧ በቀር ቀጠሮ ከመያዛቸው በፊት አስቀድማ እንደማይመቻት ትገልጽለታለች እንጂ ቀጥራው መቅረት ቀርቶ አምስት ደቂቃ ያረፈደችበት ጊዜ ትዝ አይለውም::

"ቀጠሮ ቀልድ አይደለም:: ትንሽም ይሁን ትልቅ ቀጠሮ ቀጠሮ ነው:: ቀጠሮ ከማያከብር ሰው ቁም ነገር መጠበቅ ባልወጣ ሎተሪ ሀብት እንደመመኘት ይቆጠራል:: . . ." የሚል እምነት አላት:: በርግጥም የፈለገው ከባድ ጉዳይ ቢያጋጥማት ለቀደመው ቀጠሮዋ ሟች ናት:: ታዲያ በሰዓቱ ከች የምትለውን ያህል ማንንም ይሁን ለምንም ጉዳይ ከአሥር ደቂቃ በላይ አትጠብቅም:: አሥራ አንደኛው ደቂቃ ላይ አስገራሚ ተዓምር ታያለሽ ወይንም ዓለም ላንቺ ትዞራለች ቢሏት እንኳ የምትጠብቅ አትመስልም:: ይኼንንም ፀባይዋን እንደተዋወቁ ሰሞን ለራሱ ሳይቀር ካንዴም ሁለቴ አሳይታዋለች::

"ጊዜና ፍላጐትን ጠብቆ በወቅቱ ያልተገኘ ጥቅም አያረካም" ትለዋለች ::

እንዳለ የእርሷን ያህል ባይሳካለትም ለቀጠሮ ያለው አመለካከት ተመሳሳይ በመሆኑ ባህሪዋን አድንቆ ይወድላታል:: ያከብራልም:: ሰሞኑን ግን የዚህ ጽኑ ልምድና ባህሪዋ ተቃራኒ፤ እንዲያውም ሽፍጥ ያለበት የሚመስል ሁኔታዋ ከመጠን በላይ አስገርሞታል:: አበሳጭቶታል:: ባልተገለፀለት ምክንያት ራሱ በፈጠረው ግምትና ጥርጣሬ ላይ ከጆሮው እንደዋዛ የነፈሰበት የሀብቴ ዝናቡ አስተያየት ተጨምሮ ጥሩና መጥፎ ሀሳብ ሲፈራረቅበት በመሰንበቱ የዛሬው የመጨረሻ ማረጋገጫ ሆኖ ታየው:: -ለመለየት::

"መሆን አለበት" አለ በሀሳቡ ሰሞኑን ሀብቴ ዝናቡ የነገረውን ሁሉ እያስታወሰ:: "እንጂ የለምንም ምክንያት ችላ ልትለኝና ካንድም ሦስት ቀጠሮ. . . ከዛሬ ጋር አራተኛ መሆኑ ነው እንጂ! . . . ስንት ቀን ነው የሚያማት? በትክክል አሟት ከሆነ ለምን ቀጠሮ ስሰጣት እምቢ አትልም? እየቀረች በይቅርታ ከምታታልለኝ:: የልቧን እየሠራች . . ."

ጠረጴዛውን በቡጢ ነርቶ ሲነሳ በላዩ ላይ የነበረው የሻይ ብርጭቆ ወደ መሬት ነጠረ:: እርሱም ካወራጨው የሀሳብ ዓለም ወደ ዕውኑ ከብርጭቆው ጋር ነጠረ:: -ደንግጦ:: ደግነቱ ብርጭቆው አልተሰበረም:: ወለሉ ላይ ያረፈው በደንዳናው የቂጡ ጠርዝ በመሆኑ ተረፈ::

"ሺት! ምን ያስጮሃታል!" አለ ድምጹ ከራሱ ጆሮ ባያልፍም ከርሱ ፊንጠር ብለው ከአንድ ወንድ ጋር ዷተቀመጡ ሁለት ሴቶች ላይ የግልምጫ በትሩን እየሰነዘረ::

ሴቶቹ ብርጭቆው ወደመሬት ሲዘል አይተው ነበር የጮሁት:: እንግዲያውማ በዚያ ሁሉ ጫጫታና ሁካታ መሀል የብርጭቆ መውደቅ ቀርቶ ብረት ቢቀጠቀጥ ድምጹ የሚሰማ አይመስልም:: እንዳለንም ከብርጭቆው መውደቅ ይልቅ ያስደነገጠው፣ ያናደደውና ያሳፈረው የነርሱ ጩኸት! በጩኸታቸውም ሳቢያ እላዩ ላይ ያረፈበት የብዙ ዓይኖች ትኩረት ነው::

የቤቱ ሰው በሙሉ ዓይኑን ወደ እርሱ መልሶ ከሙዚቃው በቀር ለጥቂት ሰኮንዶች እረጭ አለ:: ሁካታው ወዲያው ቢቀጥልም የአብዛኞቹ ጭውውት ካቆመበት የቀጠለው "ሰውየው ምን ነካው?" በሚል እና በብርጭቆው አለመሰበር አስገራሚነት ተሟሽቶ ነው:: እዚያ ሲሚንቶ ላይ ተወርውሮ! እጁ እየተንቀጠቀጠ ሂሳቡን ከፈለና ጉልበትና ጉልበቱ እየተማታበት ወጣ::



# 11

ሮጥ ሮጥ አለና ከኋላ በኩል ክንዱን ያዝ አድርጎ አቆመው:: -ሀብቴ ዝናቡ::

"ጆሮህ አይሰማም ማለት ነው?"

"ተወኝ ባክህ ዛሬ ልክ አይደለሁም::" አለ እንዳለ ብስጭቱን መደበቅ ተስኖት::

"ምን ዛሬ ብቻ ሰሞኑንም እንጂ፣ ሰሞኑንም እኮ ልክ አልነበርክም:: ምን እንደሚያበሳጭህም ገብቶኛል:: ዛሬም አስደገፈችህ አይደል? ጠዋትኮ በስልክ 'ዛሬ ባስር ሰዓት የመጨረሻ' ስትል እርሷን እንደሆነ ገብቶኛል:: አንተ ለምን አትረሳትም::" አለው

"እኔኮ ምን እንዳስነካችኝ አላውቅም:: ሰው አንድ ቀን ይታለላል:: ሦስቴና አራቴ መታለል አለ?" ለሀብቴ ማማከር ፈልጎ ሳይሆን የራሱን የውስጥ ስሜት ሳይታወቀው በመተንፈስ::

"አልሰማሽኝም እንጂ ከዚህ ሁሉ በፊት አስቀድሜ ነግሬህ ነበር:: ይቅርታ አርግልኝና አሁንም በዚህ አያያዝህ ገና ብዙ ይደርስብሃል:: ከበስተጀርባ ያዘለችውን ጉድ ሳታስተውል 'ትወደኛለች' እያልክ የተመጻደቅክባት ዳርምየለሽ፣ ዳርምየለሽነቷ ለውበትና ባህሪዋ ሳይሆን ባንተ ላይ ለፈፀመችው በደል መጠሪያ እንደሚሆናት አልጠራጠርም " አለ ሀብቴ ::

"እኔኮ! ግድ ውደጂኝ ብዬ አልያዝኳት:: ለምን ቀጠሮ ስሰጣት ትቀበላለች? ለምንስ ትቀራለች? አልመጣም በቃኸኝ ብትለኝ በጉልበት አላስፈራራኋት:: ለምን እንደህጻን ታታልለኛለች?" እርሷን ያገኘ ይመስል ሀብታሙ ላይ አፈጠጠበት::

"ትቀልዳለህ! በቃኸኝማ እንዴት ትልሀለች? እንደዛ እንድትልህ ነበር የጠበቅካት? አትሳሳት:: እየህ ሴቶችኮ ከእኛ የተሻሉ ቆቆች ናቸው:: በዚህ አንተን ልቧ እስኪጠፋ እየተስለመለመች 'ወደድኩህ' ትልና በዚያ ደግሞ ከሌላው ጉያ ተለጥፋ 'ያላንተ ማን አለኝ!' ትለዋለች:: አንተንም እርሱንም ግራና ቀኝ በፍቅር አጥምዳ ስታማርጥ ከቆየች በኋላ ትርፍ ወዳለበት ዘወር ነው:: አሁን ታዲያ ምን አትርፋ አልፈልግህም ትበልህ? ለጊዜው ማበላለጫ ሚዛኗ አንተንና ሌላውን እኩል አድርጎ ካሳያት ያንዳችሁ ዕድልና ጥቅም

ሚዛን እስኪደፋ ሁለት ወገን እያባበለች ማቆየት አለባት:: ይኼ ደግሞ የማንኛዋም ሴት ባህሪ ነው:: አለው አፋን በግራ እጁ እንደከለለ::

እንዳለ ከኪሱ ሲጋራ አውጥቶ ሲለኩስ ሀብቴም የራሱን አወጣና በእንዳለ ላይተር ለኮሰ::

"ለምን ገብተን እንጫወትም? ሻይ ልጋብዝህ!"አለ ሀብቴ፣ እንዳለ ወደወጣበት ቡና ቤት እየጠቆመው "ሰውም አቁሜአለሁ::"

"የምን ሰው?" አለ የሀብቴን የእይታ አቅጣጫ ተከትሎ ፈንጠር ብላ የቆመችውን ወንዳወንድ ቢያያትም:: ሳቢ ጋይድን በሩቅ ስለሚጠላት አግባብ የለውም እንጂ እንደ አራት ኪሎ ህውልት ሁሉ አራት ኪሎን መርገጥ ሲጀምር አንስቶ ያውቃታል::

"እንግባና አስተዋውቃችኋለሁ:: አሁን እኮ ያንተኑ ጉድ ስትነግረኝ ነበር::"

"የምን ጉድ?" አለ አንዴ ወደ ሀብቴ አንዴ ወደ ልጅቷ ዓይኖቹን አቀባበሎ::

"ቆይ አትቸኩል፤ መርዝም ቢሆን ትሞታለህ" አለ እንጨት እንጨት በሚል ንግግሩ እየቀለደ:: "እንግባና ሁሉንም ትሰማዋለህ::"

እንዳለ ከሚያስቀው ይልቅ ውስጥ ውስጡን እያናደደው "እኔ እዚያ አልገባም" አለ::

"ለምን?"

"እሱን ሌላ ጊዜ እናወራለን"

"ምነው! ቀጥራህ የቀረችበት ስለሆነ ቡና ቤቱንም ተቀየምከው እንዴ?" አለ ሀብቴ አሁንም ደረቅ ፈገግታውን እያገጠጠ:: "እሺ ትንሽ ዝቅ እንበል?"

ቁልቁል ወደ አደባባዩ ወረዱና ወደ አድዋ ጉዳና ታጥፈው ካንድ ቡና ቤት ገቡ::

"የምትተዋወቁ ይመስለኛል::" አለ ሀብቴ ከመቀመጣቸው ሁለቱንም ተራ በተራ ተመልክቶ::

"ባይን የማውቃት ይመስለኛል:: በርቀት" አለ ምንም እንኳን ርግጠኛ ቢሆን በሩቁ ድርጊቷ የሚያስጠላውንና የምታናድደውን ዱርዬ በቀጥታ 'አውቅሻለሁ' ቢላት ራሷን እንደ ጥሩ ባለዝና እንደምትቆጥር ገምቶ::

"እኔ ግን ካሁን በፊት የማውቅህ አይመስለኝም"

'ብድር ነው!' አለ እንዳለ በልቡ አውቃ መሆኑ ከአነጋገሯና ከሁኔታዋ ገብቶት::

"እንዴት አታውቂውም? ከኔ ጋር አይተሽን አታውቂም? ታውቂዋለሽ እንጂ:: አንድ ላይ ነው የምንሠራው::"



"በፍጹም ላውቀው አልቻልኩም::" አለች ከዳርምየለሽ ጋር ለበርካታ ጊዜያት እንዳየችው ብታስታውስም ለሷ ያላት ጥላቻ እሱንም እንድትጠላው ስላደረጋት 'አላውቅህም' ማለቷ የጥላቻዋ መግለጫ እንደሚሆን አስባ::

"እንዴት ተጐዳሁ! እኒህ ታላቅ እመቤት አላውቅህም አሉኝ" ሲል በልቡ አሽሟጠጣት::

"እሺ አሁን ላስተዋውቃችሁ:: በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የ 'ባህል ዓምድ' አዘጋጅ ነው::" አለ ሀብቴ ቀኝ እጁን አንስቶ እንዲጨባበጡ እየጋበዘ::

"ሳቢ ገር. . .ል" አለች ሙዚቃ በመሰለ ቄንጠኛ አነጋገር::

እንዳለ የመወርወር ያህል ስሙን ጥሎላት እጁን መለሰና በጉጉት የሀብታሙን የከንፈር እንቅስቃሴ ጠበቀ:: 'ያንተኑ ጉድ . . .' የተባለውን ለመስማት::

"ቴክ ኢት ኢዚ እንዳለ፣ ሴት በሴት ይተካል:: እንኳን እሷ ስንቱ ስንቱ ይቀራል::" ብሎ ጀመረ አፋን በግራ እጁ እየከደነ::

"የሞራል ግንባታህን ተወውና ወሬህን ብቻ ተርትርልኝ::" አለ እንዳለ በልቡ ተናዶ::

"ነገሩ እንኳን አዲስ አይደለም:: በፊቱኑ ሥር የሰደደ፤ አሁን ግን ከሥሩ ወደ ግንዱ እያደር እየጐላ የመጣ ጉዳይ ነው:: አለና ሲጋራውን ሳብ ሳብ አደረገ::" ለማንኛውም ነገሩን ከምንጩ ብትሰማው ይመረጣል:: ወደ ሳቢ ዞረ:: 'ተናገሪ' እንደማለት ዓይነት::

"የምን ነገር?" አለች ነገሩ ቢገባትም ያላወቀች መስላ::

"ስለ ዳርምየለሽ ቅድም የነገርሽኝን ነዋ!"

"እ! እሱማ ያው በቃ ምን ታሪክ አለው! አረገዘች አስወረደች::"

"ምን!?" አለ በጥፊ የተመታ ያህል ወደ ኋላ ተስፈንጥሮ እንደመነሳት እየቃጣው::

"ምን ያስደነግጣል?" አለች ሳቢ ሁኔታው ቢያስፈራትም ነገሩን አቃልላ ለመዝናናት እየሞከረች:: "ፋራ!" አለችው በልቧ እንዳለን::

"በፍጹም:: በፍጹም አላምንም:: ፍጹም ውሸት ነው::" አለ ተስፋ መቁረጥን በሚያመለክት ቀዝቃዛ ድምጽ::

ከባድና ቀፋፊ ፀጥታ በመሀላቸው ወረደ:: ሀብቴ ከኪሱ ሲጋራ አውጥቶ ለኮሰና የቀረውን ከነፓኬቱ ገፋ አድርጎ በግንባሩ እንቅስቃሴ ጠየቃት:: 'ትፈልጊያለሽ?' እንደማለት:: ሳቢ ግብዣውን ተቀብላ አከታትላ ሳበችው::

"ልቅ!" አለ እንዳለ በልቡ አጫጫሷን እያስተዋለ:: ያበሸቀው ግን አነጋገሯ ነበር::

'አረገዘች አስወረደች'

ደግሞ ደጋግሞ ለራሱ ቢያብጠለጥለውም አልዋጥልህ አለው::

"በርግጥ ዳርምየለሽ ከኔ ሌላ ወንድ ሄደች? ከመሄድም አልፋ ለማርገዝና ለማስወረድ ደረሰች?. . . . ሌላውስ ይሁንና መቼ ያረገዘችውን ነው ያስወረደችው? ጉድ?. . . ነው ወይስ በፊቱኑ ሀብቴ እንደሚለው ሌላ ሰው በኔ ላይ ደርባ ነበር?" አለና ሀሊናውን በጥያቄ አጣደፈው::

ሀብቴ ዝናቡ እንደነገረውሜ ከሆን እነ ዳርምየለሽ ቤት ከሚመገቡት ወንደላጤዎች መሐል አንዱን ከያዘች ቆይታለች:: ሌላስ? ከዚህ ሌላ የማድመጥ እድል ሰጥቶ ስላልተቀበለው በዳርምየሾሽና በሰውየው መሐል ስላለው ግንኙነት የሰማው ዝርዝር ታሪክ የለም:: ሀብቴ በእርሱና በዳርምየለሽ ፍቅር ላይ ገና ከጅምሩ የነበረውን ጥላቻ ስለሚያውቅ ለወሬው ቦታ ሰጥቶት አያውቅም:: ለራሱ እስካላጋጠመው ለማንም ቢሆን የወሬ ቀዳዳ ላለመክፈት በርሷ ላይ ያለውን እምነትና ፍቅር ብቻ ነበር አጥብቆ የያዘው:: ሰሞኑን ግን ከንክኖታል::

ትንሽ የነገር ጠርዝ እያደር ይመዘዝ:: መጀመሪያ ንቀው ያለፉት ወሬና አጋጣሚ በድጋሚ ሲመዘዝ ጉልቶና ደምቆ ይታያል:: በዳርምየለሽ ፍቅር የተቀለፈ የውስጥ ልቡን ባይከፍትም በቅናትና በብስጭት የጦፈ የላይ ከላይ ቀናኢ ስሜቱን ግን ሲያንኳኳው ነው የሰነበተው:: -ጥርጣሬ::

አሁንም የሰማው ነገር ሀሊናውን ቢፈታተነውም በይፋ ተቀብሎ እንዳይረታ ተከላከለ:: ለዳርምየለሽ ሳይሆን ለራሱ ሞራል::

"ማርገዟንም ሆነ ማስወረዷን በምን አወቅሽ?" አላት ብሽቀቱን ተቆጣጥሮ እንደበቱን ለማለሳለስ እየሞከረ::

"በምን አወቅሽ? የሰፈር ሰዎች የሰሞኑ አጀንዳ ምን ሆነና? ሁሉ የሚያወራው ስለእሷ በድብቅ ማስወረድ ነው:: እሺ ካልሆነ አሥራ አምስት ቀን ሙሉ በድብቅ ተዘግቶባት የተኛችው ለምን ይመስልሀል? የመኝታ ቤታቸው በር ሁሌ እንደተዘጋ ነው አሉ የሚውለው:: እናትየው ሲጠይቋቸው 'አሚታል' እያሉ ይደባብቃሉ::" አለችው በማጣጣል::

"በፍጹም ላምንና ልቀበለው አልችልም::" አለ እንዳለ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ:: አፉ ቢያስተባብልም የልቡ እምነት ሲርድ እና በቅናት መንከታከት ሲጀምር ተሰማው::

"ኧረ ይሄ የማነው. . . ካላመንክ ታዲያ ምን አስጠየቀህ?"

"እንዳትሰድቢኝ" አለ በልቡ::

"ድሮስ እንደኛ እንደኛ ዓይነቷን እንጂ ጓዳ ለጓዳ የሚልከሰከሱትን ማን ይጠረጥራል:: 'አንገት ደፊ አገር አጥፊ' አቀርቅራ ደየመችና አቀርቅራ ቀረቻት:: አይታወቅ መስሏት:: 'ልጅ ማለት የብዙነሽ ልጅ ናት' እያለች የምትጨቀጭቀኝ እናቴ እንኳን ሰሞኑን ታመሰግነኝ ጀምራለች::"

"ምን ብለው?" አለ ሀብቴ ነገሬ ብሎ ሳይሆን የወሬው ተሳታፊነቱን ለማሳየት::



"እንዴ ምን ማለትህ ነው? ራሴን ስለጠበቅኩኝ ነዋ! ስሚን:: ሳቢ ገርል በርጫና ሴሽ ላተራምስ፣ ከቦይ ፍሬንዶቼ ጋር ውጬ ሳድር አንድም ሰው አይደፍረኝ:: እናቴ ግን እኔን ዱርዬ እሷን ጨዋ አድርጋ ትሰድበኝ ነበር:: አሁን ታዲያ ማን አስወረደ? -ዳርምየለሽ:: ማን ነው ባለጌ? -ዳርምየለሽ:: ሳቢ ገርል ነፃ!" አለች:: ተኩራርታና ተዝናንታ::

"ግን ለነገሩ፣ ከማን ነው አረገዘች የሚባለው?" አለ እንዳለ ካፉ የሚወጡት ቃላት ለራሱ እየከበዱት::

"አንድ አለ 'ፈጠነ' ነው ምናምን እሚሉት ፋራ:: ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ነው የሚሠራው:: እነሱ ቤት ይበላል:: ሙሉ ቀን ተወትፎ ማደር ነው የሚቀረው:: አሁንም አረገዘች የሚባለው ከሱ ነው::"

እንዳለ ከመቀመጫው ብድግ አለ::

"እሺ እኔ ልሂድ"

"ቆይ እንጂ ትንሽ እንጫወት" አለው ሀብቴ::

"ይመሽብኛል" አለና ሳይጨብጣቸው ወጣ::

# 12

ሀብቴና እንዳለ ዳርም የለሽን ለመጀመሪያ ጊዜ ያዩዋት እኩል ነው:: በአራት ኪሎ ቀልጣፎች ሳይ በለመደው ድፍረት ከእንዳለ ቀድሞ ለከፋት:: ለራሱ ገንኖ ለሚታየው መልክና ቁመናው ደንታ ስላልሰጠችም በጋዜጠኝነቱ ሊግርካት፣በድርቅናው ሊያምበረክካት ራሱን ክቡ ቀረባት:: እርሷ ግን ቅንጣት ትኩረት አልሰጠችውም:: እንዲያውም አጣጥላው ሄደች:: ያ እንኳን አንዳንዴ ደረቆቹ የአራት ኪሎ 'ጨላጦች' ልብ ለመስቀልና፣ለማጓጓት የሚጠቀሙበት አለበለዚያም ምንም የማያውቁት የቤት ውስጥ 'ድመቶች' የሚያሳዩት የዓይን አፋርነት ምልክት ነው:: ለጊዜው በሴት ጉዳይ ዓይን ለበላ ድፍረቱ ቁብ አልሰጠውም:: ከዚያ ያለፈም ሊያስባት አልፈለገም:: የኋላ ኋላ ግን ሁለቱ ተቀራርበው፣ በፍቅር ነደውና ጦፈው ሲያይ አዲስ ስሜት፣ ቁጭትና ቅናትን ያዘለ ዕኩይ ሀሳብ በህሊናው አቆጠቆጠ::

'ለምን?' አለ:: በመልክና አለባበሱ ስካራም ከሚመስለው ባለ ፊዛዛ ፊቱ እንዳለ እንደሚበልጥ ተሰማው:: ሌላው ቀርቶ ሌሎች ሰዎች ላይ እንደ እንከን የሚታየው የጥርሱ ገጣጣ ችምችም ከሚባልላቸው እኩል ልብ ስንጣቂ ፍቅር ለቃቂ መሆኑን አንዳንድ የሚቀርባቸው ሴቶች አረጋግጠውለታል:: ንጣቱም ቢሆን የአጫሽ ጥርስ አይመስልም:: እንዴት እሱን እንደ አውሬ ለንግግር ጠልታ ጥርሱ በሲጋራ የበለዘውን በተለይ ደግሞ ሴት 'ለመልከፍ' እንደወንጀል የሚፈራውን፣ ሥራ ከገባ የረባ ኮት እንኳን ያልቀየረውንና ኮንትራቱ ሲያልቅ ይባረር ይሥራ የማይታወቅለትን ፊርማው ያልደረቀ -ሰሙ ያልፀደቀ 'ድብርታም' መረጠች? ነው ወይስ እንዳለ ከእሱ የሚበልጥበት ነገር አለ?

የዳርምየለሽን ቀጥተኛ መጥፎነት ሳይሆን ቀላል የሚመስሉ ነገር ግን ለጥርጣሬ በር የሚከፍቱ 'አሉ' እና 'አየሁ'ን ተመርኩዞ ብዙ 'እዚህ ቦታዎችን እና 'እንዲህ አረገችን' ሲያቀብለው፣እንዳለም ሰምቶ ችላ ሲልበትና የርሷን ጥሩ እያነሳ በር በሩን ሲዘጋበት በካንገት በላይ ግንኙነታቸው እንደቆዩ ሀብቴ ሳቢ ጋይድን መቅረብ ይጀምራል::

ሳቢ ጋይድና ዳርምየለሽ የአንድ ሠፈር ልጆች እንዲያውም የልጅነት አብሮ አደጉች መሆናቸውን ሲረዳ ቀድሞውንም ወንዳወንድነቷን በርቀት



ይወድላት ከነበረው ሳቢ ጋይድ ጋር ያለውን አግባብ በጥብቅ ያዘና ርግብን በጭልፊት ብሎ ተነሳ:: 'የፍቅር ደላላ' እያሉ የአራት ኪሎና አካባቢዋ ወጣቶች ሲያዳንቋት የስማላት ሳቢ ጋይድ ገንኖ በሚነገርላት ተአምሯ ዳርምየለሽን ከእጁ እንደምታስገባለት እርግጠኛ ነበር:: ሀብቴ ከዳርምየለሽ ፍቅርም ሆነ ጥላቻ እንደሌለው ራሱን ለማሳመን ቢሞክርም ስለርሷ በተለይ ከእንዳለ ጋር ባላት ግንኙነት መጥፎ መጥፎዋን ከማሰብና ከመመኘት ሊመለስ አልቻለም:: በህይወቱ ከሚያውቃቸው ምስለ ሄዋኖች ሁሉ በማንኛውም ነገር ዝቅተኛና ርካሽ አድርጐ ሊመለከታት፣ ሊንቃትና ሊረሳት ይፈልጋል:: ነገር ግን አንድ ቀን ተከትሎ እንደለከፋት፣በልቡ እንደሚመኘው እርሱ ሳይሆን እርሷ እንደናቀችው:: ይባስ ብላም አብሮት የነበረውና በዕለቱ ምንም የመቅረብ ምልክት ያላሳያት እንዳለን ማፍቀሯ የፍቅር ቀልቧ አርፎበት ወይንም ደግሞ ከእርሱ የሚበልጥ መልክና ቁመና ወይንም ሌላ ውበት አይታበት ሳይሆን ሆን ብላ እርሱን ለማብሸቅ የፈፀመችው ተንኮል ነው ብሎ ደመደመ:: በመሆኑም አንድ ቀን በሆን ዘዴ ከእጁ ወድቃ እርሱም በተራው ንቆና ስቆ ሊተዋት፣ ሊበቀላት ተነሳ::

በሌላ በኩል ደግሞ ሁልጊዜ ራሱን ከፍ አድርጐ የሚመለከትና በሌሎች መበለጡን አሜን ብሎ መቀበልን የማይወደው ምቀኛ ተፈጥሮው በዳርምየለሽ ዓይን ዝቅ ተደርጐ መታየቱን እየነገረው ራሱን ከእንዳለ ጋር በማነፃፀር ካላሰበው ፉክክርና ውድድር ውስጥ እንዲገባ አደረገው::

ሀብቴ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በውጭ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ የባችለር ዲግሪውን የተቀበለ ከመሆኑም በላይ ከእንዳለ በሁለት ዓመት ቀደም ያለ የሥራ ልምድ ስላለው የዩኒቨርሲቲን ደጃፍ ያልረገጠውና ከኋላው የተቀጠረው እንዳለ በተሰለፉበት የጋዜጠኝነት ሙያ ከእርሱ ማነስ እንዳለበት ያምናል:: ይህ እምነቱ እንዳለ ገና ሳይቀጠር ጀምሮ እና ከተቀጠረም በኋላ በንባብና በተፈጥሮ ማስተዋሉ ያዳበረውን ዕውቀትና ተስጥኦ ተጠቅሞ ያሳየውን የሥራ ስኬት የተመለከቱ አለቆቹ የሚሰጡት ከበሬታና ከጅምሩ ያሳደሩበት እምነት እንዳይዋጥለት አድርጎታል:: ራሱን ከፍ አድርጎ ማሰቡ ለመጀመሪያው የበታችነት ስሜቱ ይበልጥ ማዘቅዘቂያ፣ለቅናትና ብስጭቱ ማቀጣጠያ ከመሆን ባሻገር በራሱ ህሊና ለፈጠረው ፉክክር ማሸነፊያ አልሆነውም::

በፍቅር ሳቢያ ተቀናቃኞች አድርጐ የፈጠራቸው ተፋላሚዎች የማያውቁት የፍልሚያ መድረክ አዘጋጅቶ ራሱ ተሸናፊ ሲሆን፣ ህሊናዊ ሽንፈቱን ተቀብሎ ሳይሆን በበለጠ ቁጭትና በቀል ተወጥሮ ሌላ የመንፈስ ማጽናኛ የሞራል ማረጋጊያ የሚሆነው ራሱን ማበላለጫ ሀሳብና ተንኮል ሲያዘጋጅ ሲያቅድና በእነሱ ላይ ምንም ለውጥ አጥቶ የራሱ መውደቅና ማነስ ሲሰማው፣ እንደገና እንደገና እንደገና. . . ሲሞክር ሲከሽፍበት፣እያደር ተስፋ ሲቆርጥም በእልህ ያቆጠቆጠው ዕኩይ ፍላጐትና ጥረቱ የማይነቀል የተንኮል

ሰሎሞን ሹምዬ

ሉስ ሆኖበት የምቀኝነት አደ
በእንዳለ ዙሪያ ሲያንዣብብ

ለእርግቢቱ ዳርምየለ
ተጋንኖ የሚነገርላት ወ
አልቸረችውም። ይልቁንም
ሲያነሳባት በር በሩን እየዘ
ያላትን ጥላቻ ተረዳ። እንዳ
አኮማትራና አጨፍግጋ ከም
የሚፈልገውን ለማግኘት ማ
ግን ከሁሉም የላቀ ነው።
አድርጓለታለች።አንጀቱ ር

እኔንም ባሌንም በዘፈን ይነካኩን ጀመር፡፡ እኔም አላርፍ አልኩኝ፡፡ መጨረሻውን እንደተኛሁ ያዘኝ፡፡"

"ኡ! ቅሌትሁ! ማን?" አሉ ወ/ሮ ብዙ ራሳቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው፡፡

"ያው ባሌ ነዋ! ጧት ተነስቶ ወደ እርሻው ይወጣና ለካስ ውሽሜ የሚመጣበትን ሰዓት ሰልሉ ኖሮ ተደብቆ ይጠብቃል፡፡ አቶ ውሽሜ በለመደበት የሱን እግር ጠብቆ መግባት፡፡ ተያይዘን እንደወደቅን ወለል አርጐ በሩን በረገደና ዘው አለብና፡፡ ምን ይዋጠኝ! የት እንግባ! አቤት አቤት!" አሉ አሁን አሁን መሰላቸውና ቁጢጥ ብለው በተቀመጡበት እጆቻቸውን ወደላይ እንጨፍርረው ዓይኖቻቸውን ወደ ጎን እያንከባለሉ፡፡

"ምን ይዋጥሁ! ምን ይዋጥሁ!" አሉ ወ/ሮ ብዙ ያላዩት አጋጣሚ ለእርሳቸውም በህሳብ እየመጣባቸው፡፡

"አንድስ የሚያክለውን መጥረቢያ እየነቀነቀ 'ዛሬ ሴት አውልና ጉበዙ ይለያል፡፡ ተነስ!' ብሎ እንደመብረቅ ሲጮህ ትኩሳቴ ሙሽሽ አለና ድንዝዝ ብዬ ቀረሁ፡፡ ተንደርድሮ ሲመጣብን ሽልቅቃችንን ብድግ"

"እንዲያ ሆናችሁ ወደውጭ ልትሸሹ እንዳይሆን!?" አሉ ወ/ሮ ብዙ ሁለት ርቃኖች መንተዕፍረታቸውን ጋርደው ሲሮጡ፣ ገጠሬው መንደርተኛ 'ጉድ!' እያለ ከየጐጆው ወጥቶ ሲስቅና ሲሳለቅባቸው፤ እረኛ ከብቱን ጥሎ በስድብ ሲከተላቸው. . . በዓይን ህሊናቸው እየታያቸው፡፡

"በየት በኩል? እስክናመልጥ ማን አድርሶን? አቶ ውሽሜ እንዳላመለጠ ሲያውቅ የለበስነውን ጨርቅ ጠቅልሎ ደመነፍሱን መኩተና ሁለቱ ሲጋጠሙ እኔ ጨርቁን አንጠልጥዬ ሹልክ አልኩኝ፡፡ ጥግ ይዤ ልብሴን ለበስኩና ነጠላ እንኳን ሳልደርብ እግሬ አውጪኝ፡፡"

"ጥለኋቸው?"

"ኋላ ምን ላረግ ኖሯል? እሪ ብዬ ገላጋይ አልጠራ የራሴው ጉድ ነው፡፡ ውሎዬን ሸሽሁና ማምሻው ላይ እናቴ አገር ደረስኩ፡፡ እዛ የእናቴ ትልቅ እህት ቤት አንድ ሳምንት ተደበቅኩና አክስቴን እግሯ ላይ ወድቄ ትንሽ ገንዘብ ስትሰጠኝ ዓይኔን ጨፍኔ አዲስ አባ፡፡"

"እሺ!" አሉ ወ/ሮ ብዙ ወጣቸውን እየከለሱ፡፡ ደግኑቱ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እየተመላለሰች የምታቀርብላቸው ኑንሽ መሆኗ እንጂ እንደወትሮ ብቻቸውን ቢሆኑ የእማማ ሸዋን ታሪክ በተመስጦ ሲያዳምጡ ወጡ ተሰርቶ ማለቁ ያጠራጥር ነበር፡፡ ዛሬ ግን የዳርምየለሽ ጉዳይ ስላሰባቸው ኑንሽ ከዕረፍት በኋላ ያለ ትምህርቷን አስፈቅዳ ልታግዛቸው መጥታለች፡፡

"እነሱስ መጨረሻቸው ምን ሆነ?"

"ማ? ወንዶቹ? ያኔማ ምን እንደሆኑ ምኑን አውቄላቸው፡፡ ይቅር ይበላቸውና አዲስ አበባ መጥቼ ከስንት ዓመት በኋላ አንድ ያገሬ ሰው አገኘሁና ሲነግረኝ፣ ፍጥረቱን አሉ፣ ሜዳ ለሜዳ ሲያሩዋሩጠው ሰው ደርሶ ያስጥለዋል፡፡"

"አይ ቅሌት! አይ ሞት! እንዴት ቆሞ ሊሄድ ይሆን?"



"ምን ቆሞ ይሄዳል!? የማግስቷን ጀምበር አላየም አሉ፡፡"

"ምን ሆነ ታዲያ?"

"ጠፋአ! ጠፋ፡፡" አሉ እማማ ሸዋ፡፡

"መጥፋትም ሲያንሰው ነው፡፡"

"አለዚያማ አገሬው መች ቆሞ ያስኬዳል፡፡ ያውም ቄስ"

"ቄስ? ይኼስ ጉድ ነው! ቅስናቸውም ፈረስ በሉኛ፡፡ ለመሆኑ የት ደረሱ ታዲያ?" አሉ ወ/ሮ ብዙ በቀደም አብረው የሄዱባቸውን ቄስ በጥርጣሬ እያስታወሱ፡፡

"የት እንደደረሰማ ምኑን አውቄው፤ ወሬውንም ስምቼ አላውቅ፡፡" አሉ ቄስነቱን መናገራቸው ቆጭቷቸው፡፡ ወ/ሮ ብዙ እንዳያውቁባቸው ሰግተዋል፡፡

"ታሪክ ነው!" አሉ ወ/ሮ ብዙ፡፡

"ይኼውልሁ፣ በእንዲህ ያለ ጉድ ነው ዓርብ ቀን ላይ፣ አሥራ አንድ ዓመት ያሳለፍኩበት የልጅነት ትዳሬን አፍርሼ፣ ካገሬም ወጥቼ ኩቲካላ ቸርቻሪ ሆኜ የቀረሁት፡፡ ከዚያ በኋላማ በክፉ ቀን ተለክፌ ትዳር ብይዝ ውዬ አላድር፣ መቅኖ አጥቼ ቀረሁ፡፡"

"እንዲያው የፈጣሪ ትዕዛዝ ሆኖ እንጂ ከቀኑ ነው ብለሁ ነው?"

"ነገሩማ የእግዚሃር ትዕዛዝ ነው፡፡ ብቻ በኔ ላይ የሚያዝብኝ ዓርብን አንተርሶ ስለሆን ዓርብ ሲደርስ እፈራለሁ እንጂ፡፡ ለዚያውስ ዐዋቂ ሰው ከነገረኝ በኋላ እንጂ ፊትማ ምኑን አውቄው፡፡"

"ምን ብሎ ነገረዎት?"

"ዕኩይ ቀንሽ ዓርብ ነው፡፡ ከቤትሽ አትውጪ፡፡ ካልተጠነቀቅሽ ያጠፋሻል አለኝ፡፡ ውነትም ታዲያ ከዚያ ወዲህ ልብ ብዬ ስከታተለው ዓርብ ዓርብ ቀን አንድ ሳንካ አያጣኝም፡፡ ለዚያውም ስንት ተጠንቅቄ፡፡ መንገድ ብሄድ አይቀናኝ፤ ሥራ ብይዝ አይሄድልኝ፤ የቀረው ቀርቶ ሌላ ጊዜ የሚሻሙበትን ኩቲካላ ዓርብ ዓርብ ሲሆን 'ውሃ ነው? ምንድነው?' የሚለኝ አላገኝም፡፡ ዐፈር ይብላና ያ! የተረገመ ሰውዬ ሰክሮ መጥቶ በጩቤ ከዘረከተኝ ወዲህ ግን እኔም የቀረ ይቅርብኝ ብዬ ዓርብ ዓርብ መሸጥ ካቆምኩ ይኸው ስንት ዓመት ሆነኝ፡፡"

"እ! አንድ ጊዜ እኒያ ጐረቤትሁ የነበሩት ጫማ ሰፊ የደበደቡዎት?" አሉ ወ/ሮ ብዙ፡፡

"መስፌያውን ያሳጣውና ማታ ማታ እየሰከረ እየመጣ ቁምስቅሌን ነበር የሚያሳየኝ፡፡"

"አስታውሳለሁ፡፡ ያኔ እንዳሁን ቅርበት አልነበረንም እንጂ ትዝ ይለኛል፡፡ ጩኸት ስምቼ ወጥቻለሁ፡፡ ዓርብ ቀን ነበር?" አሉ ወ/ሮ ብዙ በእማማ ሸዋ የግራ አገጭ ላይ ያለውን ትልቅ ጠባሳ እያስተዋሉ፡፡

"ዓርብ ቀን!" አሉ እማማ ሸዋ ዓይናቸውም እጃቸውም ከአፋቸው ጋር የማረጋገጥ እንቅስቃሴ እየታየበት፡፡ "የፊታችን ህዳር ስላሴ ዘጠኝ ዓመት ሊሆነው ነው፡፡"

"ውነትም አሳይቶዎታል"

"ካንዴም ሁለት ሦስት ጊዜ እንጂ:: ኧረ ቁጥር የለውም::" አሉ እማማ ሸዋ ዓርብ ዓርብ የሆኑትን ጥቃቅን ነገር ሳይቀር ወደኋላ እያስታወሱ::

ወ/ሮ ብዙ ድስቱን ስለጨረሱ ወደ ማቶቱ አወረዱና "ኑ! እስቲ ወደ ቤት እንሂድ:: ልጆቼ ሰዓታቸው ተቃርቧል::" አሉ:: 'ልጆቼ' የሚሉት ተቀላቢዎቻቸውን ነው::

፨

"ፈጠን" ሲሉት ልቡ ስንጥቅ ያለች መሰለው:: ወይዘሮ ብዙነሽ ቢላምና ቢላዎ እያፋጩ "መቼም ሰው የሚወደውንና የሚያቀርበውን ነው ለእንዲህ ያለ ብርቱ ጉዳይ የሚያስቸግረው:: ትጾም የለም?"

"ይሁና ምናለ:: ሰውኮ የሚዛመደው በችግር ጊዜ ነው::" አለ የሆዱን በሆዱ ይዞ::

እጁ እየተንቀጠቀጠ ዶሮውን ተቀበለና በአፉ በስማምን በልቡ ግን አውጣኝን እየደጋገመ ወደ መውጫው በር ጠጋ ብሎ ባረከው::

"ተባረክ:: እግዚአብሔር ይባርክህ:: የእኛ ቤት ጉረምሳማ ገና ካሁኑ ወላሂ ብሎ ሰልሟል:: እንጂማ እርሱ እያለ ሰው ማስቸገር ነበረብኝ?" አሉ ወይዘሮ ብዙ::

"ማቴዎስ ዛሬ የት ሄዶ ነው?" አሉ እማማ ሸዋ ተጨማሪ ከርቤ ማጤሻው ላይ እየበተኑ:: ወይዘሮ ብዙ ሲያማርሩት ትዝ ብሏቸው ነው::

"ኧረ ምን ዛሬ ብቻ! አሁንማ እንድያውን ማደር ነው የሚቀረው:: ጠዋት የወጣ አዙሪት የያዘው ይመስል አስፋልት ላስፋልት ሲሽከረከር ነው አሉ የሚውለው:: ትምህርቱንም መማሩን እንጃ:: እዚህ ቦታ አየነው የማይለኝ የለም::. . . በቃው ፈጠን፣ አሁን ሳይሞት አይቀርም:: ተወውና ቁጭ በል::" አሉ ማቴዎስን ማማረሩን አቋርጠው:: ፈጠን ዶሮው ላይ የተደፋውን ማጠቢያ ሳህን እንደረገጠ ቆሞ ነበር::

"ኑንሺ ለእጁ ውሃ አምጭለት:: አስኑ ደግሞ ራት አቅርቢለት::"

"እንዴ፣ ገና መች አለቀና! ይጣላል እኮ" አሉ እማማ ሸዋ::

"እኛ እንጥለዋለና እሱንማ"

"ይቅር ይበልሁ! ሴት እንዴት ትጥላለች?"

"እንግዲያማ ማን ሊመጣ ነው?"

"ይቅር ይበልሁ! አይሆንም እንጂ! አለደምቡ መች ይሆናል:: ያው መቼም አንዴ ጀምሮታል . . ." አሉና በግንባራቸው ወደ ፈጠን አመላከቱ::

"ቀዥቃዣ አሮጊት! ዝም ብላ ቡናዋን አትጋትም!" አለና በልቡ "የቀረ ነገር አለ እንዴ?" ሲል ጠየቀ:: እንደማይቀርለት በመረዳቱ ሳይቀድሙት የልብ አውቃ ለመሆን::

"ዶሮው የሚጣል ነው::" አሉ እማማ ሸዋ::

"ለምን?"

"ጦስ ነዋ! የኔ ልጅ:: ልጃችን የዞረባት ይኼ ምናምኑ ሁሉ አብሮት ውልቅ ይላል::"

"ጦስ!" አለ በልቡ የዶሮውን እግር ይዞ እያንጠለጠለ::

"ጦስ! የሰው ጦስ!"



# 15

የሦስተኛ ዓመት ኢኮኖሚክስ ተማሪዋ ሩቂያ መሐመድ ለዳርምየለሽ እኩያ የልብ ጓደኛ ናት:: የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ጨርሰው ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት እንደተመደቡ ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ነው ጓደኝነታቸው:: ከዚያም እንደጨረሱ ባላቸው ጊዜ ሁሉ አልተለያዩም:: በየሳምንቱ ቅዳሜና እሁድ ይጠያየቃሉ:: ካልቻሉም በስልክ ይገናኛሉ::

ሰሞኑን ታዲያ የንሩቂያ ስልክ ተበላሽቶ በመስንበቱ በዚያ ላይ ጥናት በዝቶባት ስለነበር በስልክም ሆነ በግንባር ልትጠይቃት አልቻለችም:: ለራሷ ባይሞላላትም ዳርምየለሽን ትመጣለች ብላ ሁለት ቅዳሜና እሁዶች በሃሳብ ጠብቃት ነበር:: ዛሬ ግን መጥፋቷ ስላሳሰባት ራሷ ልትጠይቃት መጣች::

"እንዴት መሰለሽ የናፈቅሽኝ::" አለች ተቃቅፈው ከተሳሳሙ በኋላ::

"እኔም!" አለች ዳርም የለሽ እንባ እየተናነቃት::

በብቸኝነት ሀሳብ ያኰሳቆለው መንፈሷ የምትወዳት ጓደኛዋን ስታይ ደስታ አይሉት መረበሽ በተሳከረ ስሜት ተጥለቀለቀ:: ሆኖም እንድታውቅባት ስላልፈለገች "ትምህርቱስ?" አለቻት::

"ጥሩ ነው:: ጥናት በዛና የምመጣበት ጊዜ አጣሁኝ:: አንቺ ግን የዛሬ አሥራ አምስት ቀንም ሳምንትም ትመጪለሽ ብዬ ጠብቄ ነበር:: ስትቀሪ የዛሬዋን ቅዳሜ እንዴት መሰለሽ የናፈቅኳት:: ከካምፖስ እቤት ከቤት ወደ ካምፖስ መብረር ሆነና አንዳፍታ በዚሁ እንኳን እንዳልመጣ ቢዚ ሆኜ ሰነበትኩ:: ደሞም መምጣትሽ አይቀርም ብዬ ነበር:: ምነው በደህናሽ ነው 'ዴሪ?'" ሩቂያ ዳርም የለሽን ስታቆላምጣት 'ዴሪ' ነው የምትላት::

"ደህና ነኝ" አለች ዳርምየለሽ ዓይኖቿ እንባ ማቅረር እየጀመሩ::

"ደህና እንኳን አይደለሽም:: ደህናማ እንዳይደለሽ ሰውነትሽ ይናገራል:: ጥውልግልግ ብለሽ የለም እንዴ? ወር በማይሞላ ጊዜ ይሄን ያህል ለውጥ በጤናሽ ነው? ደግሞምኮ አሁን ስገባ ታመሽ መሰንበትሽን እናትሽ ነግረውኛል::

"እነሱ ዝም ብለው ነው ባክሽ"

"ዝም ብለው እንኳን አይደለም:: እንዴት መሰለሽ የተጨነቁት::

እኔን ሲያዩኝማ እንባቸው ተንከባለለ። እንዴት አሳዘኑኝ! ለመሆኑ እንዴት ነው የሚያረገሽ?"

"እኔ ምንም በሽታ የለብኝም።" አለቻት በደፈናው።

"እንዴት? ታዲያ ካላመመሽ ለምን እናትሽን ታስጨንቂያቸዋለሽ? አንቺስ ብትሆኝ ያለ አንድ ምክንያት እንዲህ ሆነሽ ታልቂያለሽ? አንድ ነገር መኖር አለበት መቼም።"

"ምን የሚሉት ነገር?"

"እኔ ምን አውቃለሁ ዴሪ፣ አንቿው ታውቂዋለሽ እንጂ ባትታመሚም አንድ ችግር ደርሶብሽ መሆን አለበት፤ እንጂ ከሰው ለይቶ የሚያስተክዝሽና የሚያስለቅስሽ በደህና ሊሆን አይችልም።"

"ደሞ ይኼን ሁሉ ከየት አመጣሽው?"

"ሁሉንም እናትሽ ነግረውኛል። 'ምናምን' ለክፏታል ነው የሚሉት። እሱን ለእምነታቸው እንተወውና አንድ ነገር እንደሆንሽ ግን ለኔም ይገባኛል።"

"ካልሽስ ምንም አልሆንኩም።"

"ለምን ትደብቂኛለሽ ዴሪ?" አለች ሩቂያ ቅር ብሏት። "የስድስት ዓመት በላይ ጓደኝነታችን በከንቱ ነው ማለት ነው? አዝናለሁ! የራሴን ያህል አቅርቤ የማውቅሽ ይመስለኝ ነበር። ለካ ከበድ ያለ ችግር ገጥሞሽ ስለማያውቅ ነው። እንደምወድሽ የምትወጂኝ፣ እንደማምንሽ የምታምኚኝ ይመስለኝ ነበር። አዝናለሁ!"

ዳርምየለሽ የሩቂያ አነጋገር ጭንቀቷን አባባሰባት። እርሷም ለሩቂያ ያላት ፍቅር ከፍተኛ ነው። ግን. . . ምን ብላ ትንገራት?

"ምን ተብሎ ይወራል?" አለች በሀሳቧ። ምን ተብሎ ይወራል? በእርሷ እድሜ ልክ ሀያ አንድ ዓመት ሙሉ ከራሷ እንኳ ሳይቀር በጥንቃቄ ተጠብቆ የኖረን የቤተሰብ ሚስጥር የሚያፈርስ፤ በእርሷና 'ልጄ' ብለው ባሳደጓት አባቷ፣ በአባቷና በእናቷ፣ ከዚያም አልፎ በእህቶቿና በወንድሟ መካከል ያለውን ጤናማ የቤተሰብ ግንኙነት የሚያደፈርስ ሚስጥር በጓደኝነት እምነት ተገፋፍታ ልትነግራት? ብትነግራትስ ምን መፍትሔ ልታገኝላት? እንደገና በአቶ ባህሩ ዘር ልትፈጥራት ወይንስ እርሷ እንኳን የማታውቀው አባቷን ልታገናኛት? ተናግሮ መቅረት እንጂ ምን ይፈይድላታል? በፍጹም ከአቶ ባህሩ ሌላ ወላጅ አባት እንዳላት ማውራቱ ክህደት ነው።

"እንደዚህ አትበይኝ ሩቂያ። አንቺ ከምትወጂኝ በማያንስ ደረጃ እኔም እወድሻለሁ። አምንሽማለሁ።"

"የታለ ታዲያ? አንድ እሚያስጨንቅሽና የሚያሳስብሽ ችግር እንዳለ ከግንባርሽና ከሁኔታሽ እየተነበበ ምንም አልሆንኩም ትይኛለሽ?"

ዳርምየለሽ ደንገጥ አለች።



"ከግንባርሽና ከሁኔታሽ?" አለች በሀሳቧ የሩቂያን ቃላት እየደገመች። ትናንት በመስተዋት ያየችው ፊቷና ሁኔታዋ ትዝ አላት። ሁለመናዋ ሚቃላነቷን የሚገልጽ መስላት።

"አንቺም አውቀሽብኛል ማለት ነው?"

በሃሳቧ የተናገረች ይምሰላት እንጂ ሳይታወቃት ድምጽ አውጥታለች።

"እየነገርኩሽ! አንቺ ብትደብቂውም ግንባርሽ፣ ሁኔታሽ ይናገራል።" ስትላት ከአፏ እንዳመለጣት ገባትና እንደገና ደንገጥ አለች።

"ይልቅ ችግርሽን ብታካፍይኝ በምችለው ሁሉ ልረዳሽ ዝግጁ ነኝ። ለችግርሽ መፍትሔ የማላገኝልሽ አድርገሽ ብትገምቺኝ እንኳን የሚስጥርሽ ጠባቂ የሃሳብሽ ተጋሪ ጥብቅ ጓደኛሽ መሆኔን አትርሺ። ካላራቅሺኝ በቀር የእኔ ላንቺ ተፈላጊነትም ይበልጡኑ በዚህ በዚህ ጊዜ ይመስለኛል። እውነተኛ ጓደኝነት የህይወት ልውውጥሽ ነው። አንደኛው የሌላውን ችግርም ሆነ ደስታ የሚጋራበት። አለበለዚያማ ለየብቻቸው ከልለው 'የራሴ' የሚሉት ችግር ካለ ሁለቱ አንድ በመሆን ፋንታ የተራራቁና በተወሰነ ጥቅምና ፍላጐት ብቻ ተገድደው የተቆራኙ ናቸው። እኔና አንቺ ግን በእስካሁኑ እምነቴ ለየራሳችን ፍቅርና ህሊናዊ ደስታ ከልብ ተጎዳኝተናል፤ ህይወቴ ህይወትሽ፣ ህይወትሽ ህይወቴ ሆኗል ብዬ አምን ነበር።"

"አሁንም ቢሆን የእኔም እምነት እንዳንቺ ነው ሩቂ" አለች ዳርምየለሽ ጓደኛዋ እንደተቀየመቻት ተሰምቷት።

"አይመስለኝም ዴሪ፣ ቢሆንማ ኖሮ እንኳንስ እንዲህ ወትውቼሽ ራስሽ ብቁም ነገር ፈልገሽ ትነግሪኝ ነበር። ያሳለፍሻቸው ቀናትኮ ቀላል አይደሉም። አሥራ አምስት ቀን ሙሉ ብቻሽን ስታለቅሽና ስትተክዢ የቆየሽበትን ጉዳይ ባልፈታልሽ እንኳ አብሬ እንዳለቅስልሽ የጓደኝነት ውይይቴን ትፈልጊ ነበር። አንቺ ግን እንደ ሩቅ ሰው ከልብሽ ሳታገልይኝ አትቀሪም።"

ዳርምየለሽ ጨነቃት። የብቸኝነት መረብ ተብትቧትና በጭንቀት ተወጥራ በመሰንበቷ ከማንም በላይ የምትወደው ፍቅረኛዋን መገናኘት እንዳቃታት ሁሉ ሩቂያም ዛሬ ተቀይማት ከሄደች ዳግመኛ ራሷ ፈልጋ ልታገኛት ለመቻሏ ውጪ የመውጣት ድፍረቷን ተጠራጠረች። እንዲያውም ህሊናዋን ሲበጣብጣት የሰነበተውና አምቃ ልትፈነዳ የደረሰችበትን ሚስጥር፣ የሩቂያን ቅሬታና ውትወታ ምክንያት አድርጐ ስሜቷ እንድትተነፍስ አስገደዳት።

"ከልጅነቴ ጀምሮ በጭንቅላቴ ውስጥ የጥያቄ ምልክት ሠርቶ የኖረ ጉዳይ ነው። እኔ ግን መልሱን ቀርቶ ጥያቄውን ለማሰብ ድፍረት አጥቼ ስሸሸው፤ ኸረ እንዲያውም ስፈራው ያደግኩት። አንድም ቀን ካፌ ወጥቶ ከሰው ጋር ተነጋግሬበት ጠይቄም አላውቅም። እስከ እስትንፋሴ መጨረሻም

ላነሳው አልፈልግም ነበር:: አዳፍኜው የኖርኩት፣ ከልቤ ልብ ውስጥ የተቀበረ ጥርጣሬ ልለው የማልችል ቅሬታ ነበር:: እንዲሁ ብቻ ከአባቴ በተለይም ከዘመዶቹ ጋር በነበረኝ ግንኙነት የመዝናናት ስሜት አይሰማኝም:: በእናቴ ላይ የምቀብጠውን እና የምመካውን ያህል በአባቴ ላይ ቁጥብ ሆኜ ነው ያደግኩት:: 'ለምን?' ብዬ ህሊናዬን ከመጠየቅ ያለፈ መልሱን ከማንም ለማግኘት ወይንም ራሴ መገመት አልፈልግም ነበር:: ❖

"ብቻ. . .ምን ያደርጋል፤ የኔ መጠንቀቅና መደበቅ ከራሴው ብቻ እንደነበር ካወቅኩበት ከዚያን ቀን ወዲህ የመንፈስ ዕረፍት አጥቼ ነው የሰነበትኩት:: ጉዳዩ የኔ ቢሆንም የማይመለከታቸው ሰዎች በውስጤ የተዳፈነውን ሚስጥር ዳር ሆነው ንፋስ ሲያስሙቱት መኖራቸው ገባኝ:: እኔ የሸሸሁ ቢመስለኝም ውስጥ ውስጡን ሲጋጋም ቆየና የዚያን ዕለት በይፋ ሊያቃጥለኝ ጀመረ:: ሳልጠይቅ ሳልፈልግ መልሱን ማወቄ ይልቁንም ከሌላ ሰው እንደበት በይፋ ስሰማው ቆጠቆጠኝ:: ልቋቋመው አልቻልኩም:: እውነትነቱ አመመኝ:: ነበልባሉ ሰውነቴን ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ጥንካሬዬንም ለበለበው:: ባዶነት፣ ብቸኝነት ተሰማኝ:: ህእ!. . ." አለችና መንሰቅሰቅ ያዘች::

"ምንድነው እሱ?" አለችና ሩቂያ ከተቀመጠችበት የጠፍር በርጩማ ተነስታ የዳርምየለሽን ትከሻ በመያዝ አባበለቻት:: "ዴሪ! እኔኮ እንድታለቅሺ አልነበረም የጠየቅኩሽ:: በቃ ተይው. . . ወይኔ ምነው በቀረብኝ!"

ዳርም የለሽ ገና ሩቂያን እንዳየቻት ንፋስ የሚያጉላላው ደመና ይመስል ባይኗ እያንዣበበ ልርገፍ ልቅር ሲል የነበረ እንባዋን እስኪበቃት ካወረደች በኋላ ቀኛዝማች የተናገሯትንና ያደረባትን የመንፈስ ጭንቀት አንድ ባንድ እያለቀሰች ነገረቻት::

"ዴሪበቃ አታልቅሽ:: ለዚህ ነው ታዲያ ይኼን ያህል ቀን . . ." ብላ ልታጽናናት ስትጀምር አቋረጠቻት::

"አንደሱ አትበይኝ ሩቂያ! እንደሱ አትበይኝ:: ላንቺ ቀላልና ተራ ነገር ሊሆን ይችላል:: እውነተኛ አባትሽን ይዘሻላ:: እውነተኛ አባት:: በሰው ወሬ ቀርቶ በራስ ክህደት ሊበጠስ የማይችል የደም ሀረግ:: 'አይደለም' ቢሉሽ 'ነው' ብለሽ የምትረችበት የተፈጥሮ ገመድ:: እስቲ ይታይሽ፤ወልዶኛል ተወልጄዋለሁ ብለሽ ያመንሽበት አባትሽን 'እንጀራ አባትሽ ነው' ብለው ያሳወቅሽውን ሚስጥር እንደዋዛ በማፈንዳት የልጅነት ዕምነትሽን ከአፈር ሲደባልቁት ምን ያህል የመንፈስ ረብሻ ምን ያህል የህሊና ሙግት እንደሚገጥምሽ:: ምን ያህል ባዶነትና ብቸኝነት እንደሚሰማሽ ገምች እስቲ:: ለሰሚማ ቀላል ነው::" አለች ዳርምየለሽ ጓደኛዋ ችግሯን እንድታካፍላት ያልወተወተቻትን ያህል ስትነግራት አቅልላ ማየቷ ቅር አሰኝቷት::

"ይሰማኛል ዴሪ:: ማለት የፈለግኩት ግን ይኼን ያህል ቀን በልብሽ



ለብቻሽ ይዘሽ ከምትጨነቂና ከምታለቅሺ! በቀላሉ እናትሽን መጠየቅ ትችይ ነበር ለማለት ነው::"

"ምን ብዬ?"

"አባትሽ ማን እንደሆነ ነዋ!"

"እንዴት ብዬ ሩቂ እንዴት ብዬ እጠይቃታለሁ? 'አባቴ ማን ነው አሳዩኝ' ብዬ? በፍጹም አላደርገውም:: ብጠይቃትም ደስ አይላት:: ይከፋታል::"

"እንዴ ለምን? ለምን ይከፋቸዋል?"

"አይ ሩቂያ! የእናቴን ስሜት በደንብ አውቀዋለሁ:: አንድ ቀን እንኳን ካፏ ሳት ብሏት እኔ የእሱ ልጅ አለመሆኔን የሚያሳይ ቃል ተናግራ አታውቅም:: እንዲያውም ሁልጊዜ እያሳመረች የምታወራው ህፃን ሆኜ ታናናሾቼ ከመወለዳቸው በፊት ካባቴ ጋር ስለነበረን ፍቅር፣ እንዴት ያሞላቅቀኝ እንደነበርና ከእሷ ይልቅ እርሱን እወድ እንደነበር ነው:: ታዲያ ይኼን ያህል ተጠንቅቃ የኖረችው እኔ እንዳላውቅና ያሳደገኝ አባቴን ወላጅ ብዬ እንድኖር ብትፈልግ አይደለም? አሁን እኔ የአባት ጥያቄ ባነሳባት ማነው ያለሽ ብላ መቆጣቷና መቀየሟ ይቀራል?"

"ማነው ያለሽ? ካሉሽማ የገዛ አጐታቸው መሆናቸውን መንገር ነዋ! ምን አስጨነቀሽ?"

"ያማ ማጣላት ይሆናል"

"ምን ያጣላቸዋል?"

"እየነገርኩሽ! እናቴ ይኼን ሚስጥር እኔ እንዳውቅ እስካልፈለገች ከቀኛዝማች ጋር መጣላቷ የማይቀር ነው:: ለዚያውስ ቢሆን ሌላ አባት እንዳለኝ ብታምንና ብታገናኘኝ ከዚህኛው አባቴ ጋር ልትጣላ አይደለም? እኔ ንስ ቢሆን 'የሰው ልጅ የሰው ሆነና አባቷን አለች' ብሎ ሊጠላኝና ሊረግመኝ አይችልም? አንድ ቀን እንኳን አንጀራ አባትነቱን ሳያሳየኝ ያሳደገኝን አባት ካደግኩ በኋላ አባቴ አለመሆኑን ባሳየው የህሊና ቁስል አይሆንበትም? ከእናቴ ጋር የመሠረቱትን የረዥም ዘመን ትዳር እነርሱ እንደሚሉት ከእኔ አድሜ በላይ የቆየ ትዳር ሊያፈርሰውምኮ ይችላል:: ያ ማለት ደግሞ ታናናሾቼንም ወይ ከእናት ወይ ከአባት አንደኛቸውን አጥተው በፈረሰ ቤት ለአሳዛኝ የሥነ-ልቦና ችግርና ለአስከፊ የማህበረሰብ ጠንቅ መዳረግ ነው:: ነብስ ካወቁ በመሆኑ ከአባታቸው ጋር ሲሆኑ እናታቸውን ከእናታቸው ጋር ሲሆኑ ደግሞ አባታቸውን በመፈለግ ከወዲያ ወዲህ ሲሉ የሚገጥማቸውን የሥነ-ምግባር እና የሥነ-ልቦና ፈተና ማለፍ ተስኗቸው የቤተሰቡና የማህበረሰቡ እንከን ቢሆኑ የዛ ሁሉ ችግር መንስኤ እኔ መሆኔ ሲሰማኝ ህሊናዬ ሊቋቋመው የማይችል ፀፀት ውስጥ መግባቴ የማይቀር ነው:: ኡ! ታየኝኮ:: በፍጹም ሳደርገው አልችልም::" አለች የነገሩን ክብደት ለመግለጽ ዓይኖቿን ጨፍና::

"እንግዲያው ለምን እንደ እድገትሽ ሁሉ የአቶ ባህሩን ወላጅነት እምነሽ አሁን የገጠመሽን የመንፈስ ረብሻ አታስወግጂም:: ለምን ውሸት አድርገሽ አትረሽውም? ውሸት ሊሆንም ይችላል::"

"እንዴት አድርጌ? እንዴት አድርጌ ውሸት እለዋለሁ? እስካሁንማ ሳለማወቅ በአዕምሮዬ ብልጭ እልም ሲል የኖረውን ድፍን ጥርጣሬ እንዳላስበው ስፈራና ስሸሽ የቆየሁት ለዚሁ ነበር:: ሚስጥሩም ከኔ አእምሮ ውጪ ስለነበረ የማን ልጅነት ጥያቄ እንዲፈታተነኝ እድል ስጥቼው አላውቅም ነበር:: አሁን ግን የቀኛዝማች ቃላት ሀሊናዬን ወጋተው ካቆሰሉባት ከዚያች ቀን ወዲህ እንደመርዝ በሰውነቴ የተሰራጨው ሀሳብ የልጅነት ገጠመኞቼን ሁሉ እየሳበ ሌላ ታሪክ ያሳየኛል:: በአሳዳጊነቱና ለኔ ባለው የአባትነት ፍቅር ቀዳሚውን የአባትነት ሥፍራ ብስጠውም ከሌላ መፈጠሬን ያወቀው ሀሊናዬ የእምነቴን እርቴፊሻልነት እያስታወሰ መሞገቱን አይተወኝም::"

"እኔ ግን አንድ ያልገባኝ ነገር አለ ዴሪ፣ ያባትነት ቅድሚያውን የምትሰጭው ለእኚህኛው አባትሽ መሆኑን ተናግረሻል:: እኔም ብሆን የምደግፈውና የምመክርሽ ይኼንኑ ነው:: ቁም ነገሩ ማሳደጉ ላይ እንጂ መውለድማ በተለይ ለአባት ያንድ ቀን ሽንት ነው:: ግን እንዲያው ምናልባት፣ ምናልባት ነው፣ የወለዱሽ አባትሽን ብታገኚና ከሁለቱ አባቶችሽ የግድ አንዱን ምረጪ ብትባይ ለማንኛቸው ታደያለሽ?"

"ይኼማ ምን ጥያቄ አለው ማሳደጉ ቀርቶ እድሜዬን ሙሉ አንድም ቀን ፊቱን ያላሳየኝን አባት መምረጥ አይደለም፣ ላሳሳደገ ለማያውቁት አባት የተለየ ስም ባለመኖሩ እንጂ ከዚህኛው አባቴ እኩል 'አባት' ብዬ ልጠራው እንኳን አልፈቅድም:: እንዲያውም የሱ አባትነት ባፍንጫዬ በወጣ::" አለች ዳርምየለሽ::

"ግራ የገባ ነገር! ታዲያ ለምን ትፈልጊያቸዋለሽ? ለምንስ ይኼን ያህል ራስሽን በመንፈስ ጭንቀት ወጥረሽ ትሰቃያለሽ? ይኼን ያህል ቆራጥ ነት ይዘሽ. . . በጣም ታሳዝኛለሽ ዴሪ! ታዲያ ለምን የእቶ ባህሩን ብቸኛ አባትነት ተቀብለሽ አትኖሪም?"

"ነገርኩሽኮ ሩቂያ:: እንደዛ ብዬ ሀሊናዬን ለማሳመን ድንጋይን ዳቦ ነው ብሎ የማመን ያህል ይከብደኛል:: ድንጋይ ድንጋይ መሆኑን እያወቅሽ ዳቦ ነው ብለሽ ራስሽን ማሳመን ትችያለሽ? ምናልባት ዳቦን አይቶ የማያውቅ ሌላ ሰው ቢኖር ታታልይበት ይሆናል እንጂ:: የዚያን ያህል ነው የሚከብደኝ:: ደግሞም የኔ ጭንቀት አባት ብዬ የምጠራው ወይንም የምታወቅበት ማጣት አይደለም:: ለዚህማ ከዚህኛው አባቴ በላይ ማንም ሊመጣ አይችልም:: እኔን ያስጨነቀኝ ነገር ቢኖር የዘር ምንጬን የማወቅ ፍላጐት ነው:: ሰው መቼም ያለዘር አይበቅልም:: በውስጤ ለተፈጠረው የአርቴፊሻልነት ስሜት ማርከሻ ኦሪጅናልነቴን ለራሴ ማረጋገጥ ነው ፍላጐቴ:: እኔም እንደማንኛውም ሰው የተውሶ ሳይሆን የተፈጥሮ አባት እንዳለኝ ማረጋገጥ እስካልቻልኩ የመንፈስ ሰላምና እፎይታ ሊሰማኝ አይችልም::

"መጀመሪያ ነገር የለበስኩት የተውሶ አባት ልጅነት ጭምብል ከአካባቢዬ እንጂ ከራሴ ሀሊና ሊደብቀኝ አይችልም:: ሚስጥሩን እስካወቅኩት ድረስ:: ለዚያውም አይሆንም እንጂ ቢሆንልኝና ራሴን አታልዬ ልኑር ብል እንኳ እንደ ቀኛዝማች ሚስጥሩን የሚያውቁ ሰዎች አውቀውም ይሁን ሳያውቁ



በሚሰነዝሯቸው ቃላት፣ በሚያሳዩኝ ሁኔታ የሚደርስብኝን የሞራል ተጽዕኖ ልቋቋም አልችልም::"

"እሱ እንኳን አንቺ ካመንሽበት የሰውን ወሬ ችላ ብለሽ መኖር ትችያለሽ::"

"እንዴት ይቻላል ሩቂ? እስቲ እኔን ሆነሽ አስቢው:: ባሁኑ ወቅት ምን እንደሚሰማኝ ታውቂያለሽ? ትንሽ ትልቁ ስለኔ ዲቃላነት የሚወያይና የሚሳሳቅብኝ ይመስለኛል:: 'እባቷን እኮ አታውቀውም' እያሉ በሹክሹክታ ሲያሾሚጥጡኝ የሰማሁ የሰማሁ ይመስለኛል::"

"መቼ ነው ደሞ እንደዚህ የሚመስልሽ? አሁን?"

"በቃ ስሞኑን ሁሉ ጆሮዬ ላይ የሚጮህብኝ 'ዲቃላ' የሚል ቃል ነው:: በሃሳቤ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ከንፈራቸውን በመምጠጥ 'አባት የላትምኮ' እያሉ ሲያዝኑልኝ፣ አባባ ከፍያለውም 'ያ እንጀራ አባትሽ' እያሉ ከተሰበሰበው ሰው መሃል ሲያውጁብኝ ይታየኛል::"

"ይኼ ይኼ እንኳን የተረበሸ ህሊናሽ የሚፈጥረው ነው:: ዋናው ነገር ግን የጭንቀትሽ መንስኤ የሆነውን አዲስ ሀሳብ እርግፍ አድርገሽ ካሁን በፊት ባደግሽበት እምነትና ሀሳብ መኖር ወይንም የተፈጥሮ አባትሽን በማወቅ ፍላጐትሽ ከተሸነፍሽ ያለምንም ይሉኝታና ፍርሃት እናትሽን ጠይቆ ማረጋገጥ:: ከሁለት በአንዱ ሀሳብ ላይ መወሰን ካቃተሽ የሰነበትሽበት ሁኔታ ለወደፊቱም ማብቂያ የለውም:: እንዳልሽው እናትሽን ለመጠየቅ የሚያስፈራሽ ነገር ካለና ወላጅ አባትሽን መፈለጉ የሚያስከትለውን ቤተሰባዊ መዘዝ ከፈራሽ . . ."

"ለምን አልፈራም ሩቂ? ፈርቼማ ነው::" አለች ዳርምየለሽ አቋርጣት::

"እሺ ታዲያ እነዚህን ሁለት ተቃራኒ ፍላጐትና ሃሳቦች እስከ መቼ ተሸክመሽ ትዘልቂያለሽ? ምንድነው መፍትሔው ትያለሽ? ምን ለማድረግ አስበሻል? ማለቴ ምን ብናደርግ ይሻላል? ልክኮ አይደለሽም ዴሪ! በዚህ ሁኔታ ከቀጠልሽ ደግሞ እስካአሁን ከደረሰብሽ የአካል ድቀትና የመንፈስ ውድቀት አንጻር ወዴት እንደሚያደርስሽ ታውቂያለሽ?"

"ያው ነዋ! እኔም እንደ አጐቴ 'ዕብድ' መባል ወይንም ደግሞ ሞት::"

"ኡ! ዳርምዬ! ሞት? ኧረ ምን በወጣሽ:: ለምን ትሞቻለሽ?"

"ያው ነዋ! ሌላ ምን ይመጣል" አለች ተስፋ በቆረጠ አነጋገር::

"በቃ ተይው ወሬአችንን እንቀይር:: እኔኮ ነኝ ጥፋተኛ:: ቀስ እያልን መመካከር ስንችል ባንድ ቀን መፍትሔ ውለጅ ያልኩት:: ተይው በቃ:: አሁን ሌላ ወሬ እናምጣ::"

ሩቂያ 'ሌላ ወሬ' ትበል እንጂ እንዳሰበችው ሊመጣላት አልቻለም:: ሁለቱም በየራሳቸው ዝምታ እንደተዋጡ በርካታ ደቂቃዎችን አሳለፉ:: አንድ ሁለት ተብሎ በቁጥርና በተራ አይጀመር ነገር:: ወሬ ደግሞ እንደዋዛ እንጂ ምን ላውራ ብለው በተጨነቁ ጊዜ አይመጣም:: ቢመጣም እንኳ አያምርም:: ምናልባትም ለማስደሰት ሲሉ በፍለጋ ያገኙት ወሬ ካፍ ሲወጣ የአዳማጩን

ስሜት በመሳብ ፋንታ ሊያናድድም ይችላል:: ስለዚህ ከልብ ገፍቶ ካልመጣ ዝምታው ሳይመረጥ አይቀርም:: ጆሮ ላይ ነጥሮ ከሚመለስ የቃላት ጋጋታ ይልቅ በቦታው እና በጊዜው የሚፈጠር ዝምታ ጥሩ ጨዋታ ነው:: ሩቂያም ይህንን አስባ ነው ወሬ ለመቀየር ብቻ የባጥ የቆጡን ከመቀባጠር ዝምታን የመረጠችው:: በርግጥም እንዳሰበችው በዚያ ዝምታ መሃል በውይይታቸው ተፋፍሞ የነበረው የዳርምየለሽ ብሶት ሰከን እያለ ሄደ::

"ሩቂ! ሻይ እንኳን ሳላስፈላልሽ ችግሬን ብቻ በመዘብዘብ አዋልኩሽ" አለች ይቅርታ በሚጠይቅ ሁኔታ "እነ ኑንሼን ላስፈላልሽ?"

"አይ! ምንም አይደል:: አሁን ሻይ አላስፈለገኝም::"

"ለምን?ይፈላልሽ ጠጪ?"

"እሺ እንግዲያው እንደ ሁልጊዜው አንቺ ራስሽ አፍይልኝና እጠጣለሁ::" አለች ሩቂያ ሻዩን ፈልጋ ሳይሆን ጉድ ጉድ ማለቱ ትንሽም ቢሆን ከሃሳቧ እንደሚያወጣት ገምታ::

ዳርምየለሽ እምቢ ልትላት አልቻለችም:: ሰሞኑን ሁሉ የወደቀ ማሳ አንስታ ባታውቅም የምትወዳት ጓደኛዋ በእርሷ እጅ የለመደችውን ሻይ እንድታፈላላት ስትጠይቃት ለዚያውም ራሷ በጋበዘቻት አልችልም ማለቱ ከበዳትና ካልጋ እንደከረመ ገመምተኛ ቀሰስ እያለች ተነሳች::

"ምነው? ህመም ይሰማሻል እንዴ? ፊትሽ ቅዝዝ፣ ሰውነትሽ ጉትት አለሳ? እማትችይ ከሆነ ይቅርብኝ::" አለች ሩቂያ ሁኔታዋን አስተውላ::

"አይ ደህና ነኝ::"

"አሁን ስትነሺኮ ሁኔታሽ የህመም ስለመሰለኝ ነው::"

"ያደረብኝ ምንም ዓይነት ህመም እንደሌለ እርግጠኛ ነኝ:: 'የትጋ? እንዴት ያደርግሻል?' ቢሉኝ ከራስ ምታቱ በስተቀር 'እዚህ ቦታ እንዲህ ያደርገኛል?' ብዬ ልገልፀው አልችልም:: ብቻ ጠቅላላው ስሜቴ 'ታመሻል ታመሻል' ይለኛል:: አከላቴ ድቁስቁስ ልቤ ድክምክም ይልብኛል:: ፊቴን አቀጭሜና ሰውነቴን አኮስምኜ ለብቻዬ ከመቀመጥ በስተቀር ሥራ መሥራትም ሆነ ከሰው መነጋገር፣ ሰው ማየት ሁሉ አስጠልቶኝ ነው የሰነበትኩት::"

"እንግዲያውስ እኔ የማስበው አሁን ያልሽውን ሁሉ ያመጣብሽ ጭንቀትሽን ለብቻሽ አፍነሽ ያለመፍትሔ ስትታገይ መቱንፈሻ ማጣትሽ ነው:: አሁን ከአንድ ልብ ወደ ሁለት ልቦች በመግባቱ ውጥረትሽ ሙሉ በሙሉ ባይወገድም የተቀነሰ ይመስለኛል:: ገና ቀስ እያለ ይለቅሻል:: አሁን እስቲ ጠንከር በይና በቅመም ያበደ ሻይሽን አጠጪኝ" አለች ሩቂያ ተመልሳ ወደ ልቅሶዋ እንዳትገባ ልቧን ፍራት ፍራት እያለው::

ሻዩን እንደምንም አፍልታ አብረው እየጠጡ ሳለ "እንዳለ ደህና ነው?" አለች ሩቂያ::



"እኔ ምን አውቄ ተገናኝተን አናውቅም::" አለቻት ካነጋገሯ ግዴለሽ በመምሰል:: በልቧ አራት ጊዜ ያፈረሰችውን ቀጠሮ በሃዘን አስታወሰች::

"እንዴ! ለምን?"

"ስነግርሽ! ይኸው ደጁን ካየሁት ያለፈው ህሙስ አሥራ አምስት ቀን አለፈኝ::"

"እና ስልክም አትደዋወሉም ማለት ነው?

"ስልክማ በየቀኑ ይደውል ነበር::"

"እንደሱስ ከሆነ መገናኘት ማለት ነው:: ግን እንዴት አስችሎት ዝም አለ?"

"ምኑን?"

"እህ! አሥራ አምስት ቀን ሙሉ ዓይንሽን ሳያይ በስልክ ብቻ! እሚገርም ነው:: እንዳለኮ በጣም ነው የሚወድሽ:: ከኔ ጋር ሆናችሁ እንኳን እስኪያስታውቅበት ድረስ ነው በስስትና በጉጉት ዓይን እሚያስተውልሽ:: እንግዲህ ይታይሽ አጠገቡ ተቀምጠሽ እንደዚያ የሚሆን ይኼን ያህል ተደብቀሽ ስትቀጪው ያፈቀረ አንጀቱ እንዴት ይችል ይመስልሻል::"

"እሱ ብቻኮ አይደለም ሩቂያ፤ እኔስ ብሆን የያዘ ይዞኝ እንጂ ሳልናፍቀው ቀርቼ መሰለሽ? እሱማ በስልክ እንደወተወተኝ ነው::"

"ምን እያለ?"

"ያው ቀጠሮ ነዋ እንድንገናኝ"

"እምቢ ብለሽው እንዳይሆን?"

"እምቢ እንኳን እንዴት እለዋለሁ? ምክንያት እየፈጠርኩኝ አራት ቀን ቀረሁ::"

"ለምን? ልክ አይደለሽምኮ! የፈለገው ቢሆን ለእርሱ የሚሆን ጊዜ ማጣት አልነበረብሽም:: ደግሞም ብታገኚው የሚወድሽ የምትወጂው ፍቅረኛሽ እንደመሆኑ መጠን በፍቅር ጉዳይ መጠመዳችሁ ስለማይቀር ትንሽም ቢሆን ረፍረሽ ታረጊ ነበር::"

"እኔም ደጋግሜ የቀጠርኩት ይኼንኑ አውጥቼና አውርጄ ላገኘው እየጓጓሁ ነበር:: ነገር ግን እሱ ጋር እንዴት ልድረስ? እንደነገርኩሽ የማየውና የምሰማው ነገር ሳር ንፋሱ ሁሉ እኔን ለማስደሰት የተፈጠረ አይመስለኝም:: እና ከቤት ስለመውጣት ሳስብ ፍርሃት ፍርሃት ይለኛል:: ድፍረት አግኝቼ ብሄድ እንኳን አመሉን ሳታውቂው አትቀሪም:: እንኳን ሰውነቴ እያሳጣኝ ትንሽ ፊቴን ቋጥሬ ካየኝ 'ምን ሆንሽ?' እያለ በጥያቄ ማጣደፉ አይቀርም::"

"ካሰብሽበት ታዲያ ቀላል አይደል እንዴ? አሞኛል ብትይው ያምንሻል::"

"አሞኛልማ ብዬዋለሁ:: ሲያገኘኝ ግን 'ምንሽን ነው? እንዴት ያደርግሻል?' ሌላም ሌላም እያለ መጠየቁ አይቀርም::"

"ልማድ ሆኖበት ነዋ:: ጆርናሊስት አይደል:: ለሚያቀርብልሽ ኢንተርቪው አጥጋቢ መልስ መስጠት ግን ከባድ አይመስለኝም::" አለች በራሷ አነጋገር ፈገግ እያለች::

"ለሱ ሳይሆን ስለሚያስብልኝ ይመስለኛል። እንዳንዴ አመመኝ ስለው በጣም ይጨነቃል። ስለሚጨነቅ ደግሞ የህመሜን ቅልለትና ክብደት ለማወቅ እማይጠይቀኝ ጥያቄ የለም። እንዳንዴማ እኮ የምር ሀኪምም ይመስለኛል።"

"እንዴት?" አለቻት ሩቂያ ከት ብላ ሳቀችና።

"ሙች ውነቴንኮ ነው።" አለች ዳርምየለሽ አፌር ብላ የጓደኛዋ ሳቅ እርሷንም ፈገግ አድርጓት። ጨዋታቸው ወደ ፍቅር ጉዳይ በመዞሩ ይሁን ለብቻዋ ተሸክማው ስትሰቃይ የሰነበተችበትን ሀሳብ ለጓደኛዋ በማካፈሏ በየትኛው እንደሆነ ባታውቀውም መጠነኛ የስሜት መፍታታት ይሰማታል። ሌላ ቢቀር ካነጋገሯ ዘና ማለት።

"የህክምና ሰማቸውን እይጥራ እንጂ አንቺ የምትነግሪውን በሽታ ሁሉ እንዲ እንዲህ ብታደርጊ ይተውሻል፣ ይልሻል። ውነትም ታዲያ፣ እንዳንዴ የሚናገራቸውን እንደቀልድ ስሞክር ይተወኛል።"

"እ-ሺ! እኔ መቼም ጋዜጠኛ የወረቀት፣ የነገር ሀኪም እንጂ የበሽታ ዶክተር ነው ሲባል ሰምቼም አይቼም አላውቅ።" አለች ሩቂያ የዳርም የለሽን ሀሳብ ለመቃወም ወይንም ለማሾፍ ሳይሆን ያሰበችው ማረሳሳት እየተሳካላት በመሆኑ ጨዋታቸው እንዲቀጥል ፈልጋ።

"እረ እሱ ሁሉንም ነው! ከሰው ልጅ በሽታዎች ሰባ ከመቶ ያህሉ ከአዕምሮ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ለአዕምሮ መረጋጋትና ሰላም አስፈላጊውን ሁሉ ካደረግንና ይኼንኑ በምግብና በአካላዊ እንቅስቃሴ ካስደገፍነው ያለምንም መርፌና ክኒን ጋጋታ ራሳችንን እክመን ሙሉ ጤነኛ መሆን እንችላለን ::-የሚል መመሪያ አለው።" ንግግሯን ገታ አድርጋ "ለምን ነበር ይኼን ሁሉ ያመጣሁት? . . . አዎ፣ አሞኛል ብትይው በቀላሉ ያምንሻል ስላልሽኝ ነው። ፀባዩንና የማውጣጣት ችሎታውን ስለማውቅ ዕውነቱን ካልነገርኩት በቀር በስልክ በሰጠሁት ዓይነት ምክንያት አያምነኝም ለማለት ፈልጌ ነው።"

"ታዲያ ለምን አትነግሪውም? ፍቅረኛሽ እኮ ነው።" ልትላት አሰበችና ተመልሳ ብሶት መጫር እንዳይሆንባት ፈራች። በምትኩ "ናፍቆት በናፍቆት ሆናችኋላ! ይሄን ያህል ቀን መዘጋጋት የሚገርም ነው!"

"ትናንትናማ 'ዛሬ የመጨረሻ ነው' ብሎኝ ነበር የተቀጣጠርነው። የምሩን ነው መሰል ይኸው ከነጋ አልደወለም። ሰሞኑን ቀጠሮ ኖረንም አልኖረንም ጧት ጧት ቢሮ እንደገባ ይደውልልኝ ነበር።"

"ለመሆኑ ምን ሆኜ ነው ትይዋለሽ?"

"ስለሚያስቀምጠኝ ከቤት መራቅ እንደማልችል ነው ያመካኘሁት"

"ዋና ነሽ። ለመሆኑ እመነሽ?"

"ሌላ ጥያቄ እንዳያነሳብኝ ቶሎ ብዬ ነገር እቆርጥበታለሁ።"

"ታዲያ ሁሌ እሚደውልልሽ ከሆነ ዛሬ ለምን ሳይደውል ቀረ?"

"እኔ ምን አውቄ"

"ተቀይሞሽ ሊሆን ይችላልኮ"

"የራሱ ጉዳይ" አለች። ዳምርምየለሽ ለአፏ ግዴለሽ ትምሰል እንጂ 'መቀየም' ብሎ ነገር ስታስበውም ይከብዳታል።



"እንቺ ለምን አትደውይለትም? ለጊዜው ጥፋተኛዋ አንቺ በመሆንሽ ደውይለትና ይቅርታ ጠይቂው።"

"ከዚያስ?"

"ከዚያማ ምን ጥያቄ አለው ትገናኛላችኋ"

"አየሽ ሩቂ፣ ያለፈው አንሶት ሌላ የማይሆን ቀጠሮ ሰጥቼው ለቁም ነገር የሚውል ጊዜውን በከንቱ ላባክንበት አልፈልግም። ያለፈውም ይቆጨኛል።"

"እና ተለያይታችሁ ልትቀሩ? ፍቅራችሁን እስከወዲያኛው ሰርዘሽዋል ማለት ነው?"

ዳርምየለሽ ከእንዳለ ስለመለየት ስትሰማ ስሜቷን ቆነጠጣት።

"ለምን እንለያያለን?"

"ለምን አትለያዩም? ገልፀሽ ባልነገርሽውና እጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት የውሃ ሽታ ስትሆኚበት ምናልባት ሌላ ፍቅር ጀምረሽ ሊመስለውና ሊያጠራጥረው እንደሚችል መገመት ይገባሻል። የወደደ ሰው በሚወደው ላይ ሁለመናው ዓይንና ጆሮ ነው። የማይታይ ይታየዋል የማይሰማ ይደመጠዋል።"

"ውነቷን እኮ ነው።" አለች በሃሳቧ፣ ሳይታወቃት ስህተት መሥራቷ ተሰምቷት። ልቧ እስኪደክም የምትወደውና የምታመልከው እፍቃሪዋን እንደዋዛ ስትለየው ታያትና ተንደርድራ የስልኩን እጀታ ጨበጠች።

# 16

ጧት እንደገባ ከፊቱ ያስቀመጠው ወረቀትና በቀኝ እጁ ጣቶች መሃል ወድሮ የያዘው ብዕር እስካሁን አልተስማሙለትም። የብዕሩ ቀለም ደርቆ ወይንም ወረቀቱ ቀለም አይነኬ ሆኖ አይደለም። ሁሉቱም የሚያዝምዳቸውና የሚፈልጉትን ቃላት የሚለግሳቸው የፀሐፊው አዕምሮ በሌላ ሀሳብ ተጋርዶ ግንኙነቱን ስላቋረጠባቸው እንጂ።

ከሥራ ጠረጴዛው በስተኋላ እንደተቀመጠ ዓይኖቹን በማይሰበር ትኩረት ፊት ለፊቱ ካለው ግድግዳ ላይ ተክሎ በግራ እጁ አመልካችና አውራ ጣት መሐል የያዘውን ሲጋራ በተደጋጋሚ ክንዱን ከጠረጴዛው ሳይነቅል ወደ አፉ እያደረሰ ይመልሳል። የሳበውንም ጢስ የታችኛው ከንፈሩን ወደ ፊት እያስረዘመ ይተነፍሳል። እንዲያ ትክል በመሰለ ሁኔታ አይቶት ለማያውቅ በተወሰነ የጊዜ ፋታ ወደ አፉ እየደረሰ የሚመለስ ክንዱንና እርሱም እጥር እያለ ጢስ የሚተፉ ከንፈሩን እሱ የሚያዛቸው ስለማይመስሉ አንድ ዓይነት ሰው ሠራሽ አካል /ሮቦት/ ሊመስለው ይችላል። ሁኔታው በጽሑፉ ላይ የተመሰጠ ወይንም የፊት ለፊቱን ግድግዳ የሚያስተውል ቢመስልም አእምሮው የሚያሰላስለው የዳርምየለሽን ጉዳይ ነው።

ሌሊቱን ሲያገላብጠው አድሮ ጭንቅላቱን እንደከበደው ቢሮም ተከትሎት መጥቷል። -ሀሳቡ። ከነጋ አንድ ፖኬት ኒያላ ሲጨርስ ሁለት ቢቀሩትም፣ ሦስት ብርጭቆ ቡና ቢጠጣም አንጐሉን ከሚያዞረው ራስ ምታትና 'ድብርት' አላስጣሉትም። ሀሊናውን ወጥሮ ከያዘው ጭንቀት አልገላገሉትም። እናም ሥራውን መሥራት ስላልቻለ የተመሰጠውን ሙሉ መድረክ ለዳርምየለሽና ፍቅሯ፣ ለዳርምየለሽና ሸሯ፣ ለአምነቷ፣ ለክህደቷ. . . ለቋል።

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ ነው አጠገቡ ያለው ስልክ ጀሮውን ሰንጥቆ ያቃጨለው። ሳያስበው በመሆኑ ልቡ በድንጋጤ ትርክክ አለበት። አላነሳውም። ደጋግሞ አቃጨለ። የስልኩ ድምፅ ከምንግዜውም በላይ ጮኸበት። ራሱን ለማረጋጋት ከሞከረ በኋላ መነጋገሪያውን ብድግ አደረገ።

"ሃሎ? . . . ፕሬስ" አለ ሲሮጥ እንደደረሰ ሰው ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለበት።



"እንዳለ? . . . ነኝ። ደህና" አለና ፊቱ ተለዋወጠ። በስልክ የሚነጋገር ሳይሆን ፊት ለፊቱ የቆመን ሰው የሚገላምጥና የሚቆጣ በሚመስል ሁኔታ መነጋገሩን ቀጠለ።

"እ! . . . ለምን? . . . ከእንግዲህ? . . . አይመስለኝም። . . . አልችልም!. . . በቃ! ጨርሻለሁ።" አለና ስልኩን የማጋጨት ያህል ዘጋው። የመጨረሻዎቹን ሁለት ቃላት በመጨረሻ ድምጹ ነው የጮኻቸው።

አቶ ስምኦን በሁኔታው ስለተገረመ ቀና ብሎ አስተዋለው። እንዳለ ግን ሰው መኖሩንም የረሳው ይመስላል። "ከብት!" አለ ከተቀመጠበት ብድግ እያለ። ደብዛዛው ፊቱ የሐምሌን ጭጋግ መስሏል። ከደረት ኪሱ አዲስ ሲጋራ አውጥቶ ለኩሶና የጨረሳትን መተርኮሻው ላይ ከሚገባው በላይ ድፍጥጥጥ አድርጐ እየተንጐራደደ ማጨሱን ተያያዘው። በንዴት መጨሱንም።

አቶ ስምኦን መቅደድ የጀመረውን ፖስታ እደረሰበት አቆመና "እንዳለ ምነው የተረበሽክ ትመስላለህ!" አለው ሁኔታው አስገርሞት። ከጥዋት ጀምሮ በሥራው ጣልቃ የእንዳለን ተመስጦአዊ የአካል ድርቅታ ሰረቅ እያደረገ ያስተውለው ነበር። ሆኖም ያን ዓይነት የተመሰጠ ምልክት ካሁን ቀደም በረዥም ዘመን የጋዜጠኝነት ቆይታው በገጠሙት አንዳንድ የሙያ ባልደረቦቹ ላይ የሚያውቀው በመሆኑና እንዳለም የራሱን መጣጥፎች ሲያዘጋጅ ቃላት ከአዕምሮው የሚፈልቁለት በእንዲህ ያለ ተመስጦ ውስጥ ሲገባ መሆኑን አብረው በቆዩባቸው ጊዜአት ስለተገነዘበ ሊጠይቀውም ሆነ ከተመስጦው ሊያወጣው አልደፈረም ነበር።

"አይ ደህና ነኝ ጋሽ ስምኦን" አለ እንዳለ እስካሁን ይታዘበኛል ባለማለቱ ውስጥ ውስጡን እፍረት ተሰምቶት።

"ስልኩ ጥሩ መልዕክት አልነበረውም መሰል?"

"አዎ! ብቻ ትንሽ ችግር . . ." ስልኩ እንደገና መጮህ ሲጀምር ንግግሩን ገታ አድርጐ እንደሰው ገላመጠው። "ትንሽ ችግር ናት" አለና ዓይኖቹን ስልኩ ላይ ተክሎ ቀረ። እያንዳንዱ ጥሪ ልቡን ሰንጥቆ ሲገባ ይሰማዋል። ውስጣዊ ስሜቱ ተረብሾ በማንሳትና ባለማንሳት መሀል አመነታ። አሁንም እሷ እንደምትሆን አልተጠራጠረም።

"አላነሳም" አለ በልቡ እየተናገረ። "ከቆረጡ መቁረጥ ነው። ወለም ዘለም አያስፈልግም። 'ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ' ይባል የለም። ከእንግዲህ ዳርምየለሽ የምትባል ሴት አላውቅም። ያንኑ ግን አባቱ ነው ያሉኝ እሱን ታጃጅል። . . . ግን፣ ግን ለምን ትፈልገኛለች? ለምን ቀጠሮ አፍርሳ ቀጠሮ አስፈለጋት? ለምን በስልክ አትነግረኝም? ልትለኝ የፈለገችው ነገር መኖር አለበት። . . ." አለና አንድ ነገር ትዝ አለው። አንዳንዴ እንደቀልድ ስለመለያየት ሲያነሱ የምትለው።

"ከበቃሁህ ከበቃኸኝ በሥነ-ሥርዓት 'ቻው! ቻው!' ተባብለን መለያየት

እንጂ እንዳንዳንዶቹ አንተም ተደብቀህ ከሌላ ሴት እኔም ተደብቄ ከሌላ ወንድ መሆን የለበትም።. . ."

እና ደፍራ 'እንድሽ እስከዛሬ ያሳለፍነውን ፍቅር እርሳው። ከዛሬ ጀምሮ ቻው ብዬሀለሁ' ልትለው?

"ማወቅ አለብኝ" ብሎ አሰበና ወደ ስልኩ ተጠግቶ ቆመ። በሚቀጥለው ጥሪ ሊያነሳ። ስልኩ ግን በዚያው ፀጥ አለ። የተወሰነውን የጥሪ ድግግሞሽ ጨርሷል። እንዳለ ይቀጥላል ብሎ በጠበቀው የጊዜ ግምት አልጮህ ሲለው ተስፋ በቆረጠ ስሜት አነሳና ወደ ጆሮው አስጠጋው። የራሱን መስመር ክፍትነት የሚያመለክት ድምጽ። ንዴቱ ጉሮሮው ስር ተናነቀው። ዞር ሲል አቶ ስምኦን በአንክሮ ይመለከተዋል። ፊቱን ፈታ አድርጐ ንዴቱን ለመቆጣጠርና በውስጡ ለማስቀረት ሞከረ። እርሱ ወደ ወንበሩ ሲመለስ አቶ ስምኦን ወደሥራው አቀረቀረ። ከዚያ በኋላ እስከ ስድስት ሰዓት በቀረው የአምሳ ደቂቃ ጊዜ ከአሁን አሁን ይደወላል በማለት በዓይኑ ይሰማ ይመስል ስልኩ ላይ እንዳፈጠጠ ቆየ። አልደወለችም።

ቀኑ ቅዳሜ እንደመሆኑ ከስድስት ሰዓት እላፊ ይኖራል ብላ እንደማትደውል ያውቃል። ሊደውልላት አሰበና ተወው። እንደቆራጥ 'በቃ!' ብሎ በላይዋ ላይ ከዘጋባት በኋላ አንድ ቀን እንኳን ሳያድር መደወሉ ራሱን ለንቀት አሳልፎ መስጠት እንደሆነ ተሰማው። እስካልወደደችው የሚወዳት መሆኑን እንድታውቅም ሆነ እንዲመስላት አይፈልግም። ለምን እንደፈለገችው የማወቅ ፍላጐቱ ግን ከንክኖታል። የሸሚዙን ደረት ኪስ ሲደባብስ ባዶ ነበር። ልማድ ሆኖበት እጁ ወደ ኪሱ ይሮጣል እንጂ ሲጋራው ማለቁን የመጨረሻዋን ሲለኩስ አውቆ ነበር። የቀኝ እጁን በለበሰው ኮት የጐን ኪስ ጨምሮ ቅር ቅር እያለው ወጣ። ወደ ሲጋራውም ወደ ቤቱም።ኮሪደሩ ላይ ከሀብቴ ጋር ተገናኙ። ቢሮአቸው አንድ ላይ ሲሆን ሀብቴ ቤተመጻህፍት ውሎ ሰዓት ሲደርስ የተጠቀመባቸውን የጽህፈት መሣሪያዎች ሊያስቀምጥ መመለሱ ነው።

"ጠብቀኝ ይቺን አድርሼ አብረን እንወጣለን።" አለው።

"ደሞ መርዝህን ልትረጭብኝ?" አለና በሃሳቡ "እቸኩላለሁ። ከቻልክ ድረስብኝ" አለው ብሽቀቱን ደብቆ በመጀመሪያው ፍጥነቱ እየተወረወረ።

"ግን ለምን ጠላሁት?" በማለት ራሱን ጠየቀ። "እሱ ምን አደረገኝ? ያየውንና የሰማውን ለኔ ተቆርቁሮ ስለነገረኝ?

"ቢሆንስ፣ ምናባቱ ሊያረግለት የእርሷን ሃጢአት ያነፈንፋል? እሱ ባይነግረኝ እንዳመንኳትና እንደወደድኳት እኖር አልነበር? ያው መቼም ብላ ብላ ራሷ 'አልፈልግህም' እስክትለኝ። እኔኮ እምለው፣ ለምንድነው በተቆርቋሪነት ስም ሰው በሰው ጉዳይ ገብቶ የህሊና እሾህ የሚተክለው? ለምንስ ነው የሚፋቀሩ ንጹህ ልቦች መሃከል ገብቶ ጉድፍ እየነቀሰ አጉልቶ ለማሳየት እንቅልፍ አጥቶ እንቅልፍ የሚያሳጣው? ዳርምየለሽ ከዳችኝ አታለለችኝ የሚጐዳው የእኔ ልብ ነው። ምናለበት ነበር ራሴው ገብቶኝ እስክርቃት ቢታገሰኝ?"



# 17

ራንግለር ሱሪና ጃኬት በወንድ ጫማ ለብላ የጆሊ ባርን ግርጌ ግንብ ተደግፋለች። ግራና ቀኝ ከሥሯ ተኮልኩለው የሚያናግሯትን ሊስትሮዎች፣ እቸሎኒ፣ ማስቲካና ሎተሪ አዟሪዎች ችላ ብላቸዋለች።

"ሳቢ ጋይድ ዛሬ ምን ነክቷታል?"

"ባክህ ተዋት ደብሯት ይሆናል።"

"እሷኮ እንማይክ ካላጀቧት ዝጋታም ናት። ቢዝነስ ሄደው ነው መሰል" ይባባላሉ። -በሹክሹክታ።

እርሷ ግን ከአደባባዩ ባሻገር የሚመጡ የሾላ መስመር አውቶብሶችና ታክሲዎችን በጉጉት ዓይኖቿን ተክላ ትጠብቃለች። ወንዶች ጓደኞቿን ከቤ ቤት ገና በጥዋቱ ከዘረጉት ጫት ላይ ሸውዳቸው ነው የመጣችው። አራት ሰዓት ላይ ከሀብቴ ጋር ቀጠሮ ሰላላት።

"ስንት ሰዓት ነው አንተ?" አጠገቧ ጫማ ከሚያስጠርጉት ሰዎች መሀል ወደ አንዱ ልጅ እግር መሳይ ዞራ።

"እ! እኔን ነው?" አለ ሰውዬው ልቅ በሆነው አጠያየቋ ተደንቆና ግራ ተጋብቶ።

"አዎ!"

"አምስት ጉዳይ ለአራት"

"ምን አስገበገበኝ?" አለች በልቧ ራሷን እየታዘበች። "ይኼኔኮ የቀጠረኝ አንዷን እንዳቀላጥፈው ሊጀነጅነኝ ይሆናል። እኔ እንደሆንኩ እሱን ልጅ ለማንም አላቀላጥፈውም . . . ግን ለምን? ምን ቸገረኝ?"

ሲጋራ ከኪሷ አውጥታ ለኮሰች። ለጥያቄዋ ራሱ ህሊናዋ ያዘዘላት ነው።

"ኧረ በወላዲቷ! ምን ጉድ ነው በል!" አሉ ጫማ እያስጠረጉ ከተቀመጡበት መነሳት እየቃጣቸው። እንደወንድ የለበሰችው ሴት መሆኗን ሰዓት ስትጠይቅ በድምጿ ከለዩበት ጊዜ አንስቶ እንደ ጉድ ሲመለከቷት ነበር። ዘወር ብላ ገላመጠቻቸው። አዛውንቱ ደንገጥ አሉና ፊታቸውን መልሰው ለራሳቸው አጉረመረሙ።

"አይ ስምንተኛው ሺ! ፈጣሪዬ እንዴት ታረገኝ ይሆን? ከዚህ ወዲያ ምን ምልክት ታሳየናለህ? ኧረ ምህረቱን አምጣው! ምነው ኢትዮጵያን ፈረድክባት:: በዚህ ረሀብ፣ በዚ ጦርነት፣ የተወለዱት የሚወለዱት ሁላ ጉዶች:: ጾም የለ፣ ፀሎት የለ፣ ወንዱ አይታወቅ ሴቱ:: ሁሉ አንድ! ይኼ መቼም ያንተ ቁጣ ነው:: የኢትዮጵያ አምላክ አንተው ታረቀን እንጂ እኛማ ምን ማድረግ እንችላለን::"

እርሷ ግን ደንታ አልሰጣትም:: ሲጋራውን በረዥሙ ሳብ እያደረገች ባፍ ባፍንጫዋ ትተነፍሳለች::

"ወይንምኮ ዳሯን ያጥፋውና ስለዛችው ዳርምየለሽ እሚሏት ሞዛዛ ታሪክ ሊያናዝዘኝ ይሆናል:: የሞተ:: እኔ እምለው እሱ ስለሷ ይኼን ያህል ምን አስጨነቀው? ጓደኛውን ፈንግሎ ሊያብታት ይፈልጋል መሰል::" እርብ ዕለት ስለዳርምየለሽ ማስወረድ ሲሰማ ከፊቱ ላይ ባየችው የደስታ ስሜትና እንዳለን ፈልጎ እንድትነግረው በማድረጉ ታዝባዋለች:: እርሷ ግን ያወራችለት እርሱን ለማስደሰት ራሷ ፈጥራ አልነበረም:: እቤት፣ እናቷ ቡና ከሚጠጡ ሰዎች ጋር ሲያሙ ጠልፋ የሰማችውን እንጂ:: ለዚያውም ራሱ 'ምን ሆና ነው የጠፋችው?' ብሎ ስለጠየቃት:: ዛሬ ታዲያ ምናባቱ እንድታወራለት ይፈልጋል?

"ዛሬ ምንም ወሬ የለም:: እማዬ ትሙት::" ስለሷ ካነሳብኝ ሙልጭ አድርጌ ነው የምሰድበው:: የወሬ አንቴናው አደረገኝኮ!

ስላሳ ሦስት ቁጥር አውቶብስ መጥታ ስትቆም ህሳቧን ትታ በዓይኖቿ መጠባበቅ ያዘች:: ፈጠን ፈጠን እያለ አስፋልቱን አቋረጠና ወደርሷ መጣ::

ሰላምታ ተለዋውጠው በአድዋ ጐዳና መንገድ ሲጀምሩ "ታክሲ እንያዝ" አላት::

"የት ለመሄድ?"

"ትናንት ነግሬሽ የለም? ዛሬ እንደሌላው ቀን ሳይሆን ልዩ እንግዳዬ ስለሆንሽ የተለየ ቦታ ነው የምጋብዝሽ" አለ:: ወደሷ ዞሮ ሲናገር አፉን እንደተለመደው በግራ እጁ እየከለለ ነው:: መዳፉ ላይ ያረፉትን ነጠብጣቦች እግራ ኪሱ አስገብቶ ጠራረጋቸው::

"ልዩ እንግዳ!" አለች ለራሷ በመገረም:: ላባባሉ ተቃውሞም መስማማትም ሳታሳይ ወደ አስቆመው ታክሲ ተከትላው ገባች:: "ምን ለማለት ፈልጎ ነው? ሊያወጣኝ ነው ማለት ነው?" አለች የራሷ ግምት ልቧን እያሳቀው::

"ምነው ለብቻሽ ሳቅሽሳ!?" አለ ፈገግ ስትል አስተውሏት::

"ሳቅኩኝ እንዴ?"

"አይታወቅሽም ማለት ነው?"



ከታክሲ ታክሲ እየተቀባበሉ ኮልፌ አጣና ተራ ወረዱና ከትንሽ የእግር መንገድ በኋላ የሀብታም መኖሪያ እንጂ ቡና ቤት ከማይመስል ግቢ ገቡ:: ለጥንዶች ማረፊያ ሆን ተብሎ በመጋረጃ ከተከለሉት ክፍልፋይ መጠለያዎች ወደ አንዱ መራት::

"ምናባቱ ፈልጎ ነው?" አለች በሃሳቧ:: ለጸብ እንደተዘጋጀ ጐረምሳ ደረቷ ይንቀጠቀጣል:: እግሯ ግን ተከትሎታል::

"ግን ለምንድነው ተከትዬው የመጣሁት?" መልስ ያላገኘችለት ጥያቄ:: ሌላ ጊዜም እንደዛሬው አይሁን እንጂ እዚያው አራት ኪሎ ለሻይ ሲቀጥራት ሥራዬ ብላ መገናኘቷ ለምን እንደሆነ አይገባትም:: ወይ እንደሌሎቹ ወንዶች ሴት እንድታመጣለት ጠይቋት አያውቅም:: ራሷን ፈልጎ እንዳይመስላት ምንም ፍንጭ አላየችበትም:: ሥራዬ ብሎ ቀጥሯት ሻይ ጋብዞ አንዳንዴም ስለዳርምየለሽ ብቻ ጠይቋት ይለያያሉ:: ዳርምየለሽን ወዶ እንዳትል የጓደኛው ገርል ናት:: ደሞም ከርሷ ጋር አንድ ሰፈር በመሆናቸው ደህንነቷን ለማወቅ ይመስላል አጠያየቁ:: አሁን ሲታሰበው የእርሷና የሀብቴ መቀራረብ ምንም መሠረታዊ ምክንያት የሌለው ሆኖ ታያት:: በህይወቷ ግን እንደዛሬ ወንድ የተባለ ለብቻዋ ከአራት ኪሎ ራቅ አርጐ የተለየ ግብዣ አድርጐላት አያውቅም::

"ተጫወች እንጂ፣ ምነው ዝም አልሽ?" አለ ሀብቴ ራሱ እሚለው ጠፍቶት ዝም እንዳላለ ሁሉ::

"ኳስ የታለ ታዲያ!" አለች በማሾፍ::

"እያጠቃኮ ነው"

"ማን?"

"እሥር ቁጥሩ ነዋ! ወደ ግብ ተቃርቧል::" አለ ራሷ ባመጣችው ቀልድ ጥሩ በር ስለከፈተችለት ዘና እያለ::

"ተከላካዩን ማለፍ አይችልም" አለች አፏ እንዳመጣ::

ሀብቴ ግን ሀሳቡን አግኝታ የተቃወመችው መስሎት ስሜቱን ቆንጠጥ አረገው:: እንደገና ዝም አለ::

"ይልቅ ሲጋራ አምጣ!"

"ምናምን እንቅመስ ብዬኮ ነው"!

"እስከዚያው ማጨስ እፈልጋለሁ::" አለች ተዝናንታ የቀኝ እግሯን ቁርጭምጭሚት በግራ ጉልበቷ ላይ እየጫነች::

የሰጣትን ሲጋራ እንደለኮሰች ሀብቴ ወጣ ብሎ ተመለሰ:: ያዘዘው ሁለት ክትፎ ከአራት ቢራ ጋር ዘግየት ብሎ ተከተለው::

"አራት ቢራ ምን ያረጋል?"

"ልንጠጣው ነዋ!"

"እኔ ከአንድ በላይ አልጠጣም"

"ለምን?"
"አልጠጣማ:: እኔ መጠጥ ያን ያህል አልጠጣም:: ከጠጣሽው ይሁን::"
"ይመስላል፣" ሲል በሆዱ አሽሟጠጣት "ቀስ እያልን እንጠጣዋለን"

ልትግደረደር ሳይሆን አልጠጣም ያለችው እውነቷን ነው:: ሁሉንም ዓይነት መጠጥ ብትደፍርም ትንሽ ትንሽ ነው የምትጠጣው::ብቻ መጠጥ ቤት ገብታ በሰካራም ትንፋሽና በጠርሙስ ከመለኪያ ቻቻታ መስከር፣ ከወንዶች ጋር ወንድ መስላ ባንኮኒ መደገፍ ደስ ይላታል:: በዚህም ፀባይዋ ከቅርብ ጓደኞቿ በስተቀር በርቀት የሚያዩዋት ሁሉ አደገኛ ጠጪ ነው የሚሏት::

የቀረበላቸውን በልተው እንዳበቁ እንደምንም ሁለቱን ቢራ እስጨረሳትና ሲፈራ ሲቸር ክፍል እንዲይዙ ጠየቃት::

"እ!? ለዚ ነው ለካ! . . ." ስትል አቋረጣት::
"ምን መሰለሽ. . . በሌላ እንዳ. . . እንዳትተረጎሚው እ?" አለ ከንፈሩ እየተንቀጠቀጠ::
"እንዴት? ምንድነው ሌላው?" አለች ኮስተር ብላ::
"ማለቴ፣ አለ እይደል እንደ አንድ የቅርብ ወንድ ጓደኛዬ ስለማይሽ ተዝናንቼ እንጂ እንግባ ያልኩሽ ክፍሉን የያዝኩት ለራሴ ነው::" አለ አንደበቱን ለማረቅ እየሞከረ::
"ምን እንዲሆንህ?"
"ነገ ከለሊቱ አስር ሰዓት ጀምሮ እዚህ አካባቢ እምከታተለው ጉዳይ አለኝ::" አለ ማመኻኛው ጠፍቶት በደፈናው:: 'የምን ጉዳይ?' ብትለው ግን ምን እንደሚላት አያውቅም:: እንዳትጠይቀው ተመኘ::

"እና!?" አለችው:: ውሸቱን መሆኑ ገብቷታል::
"እናማ ለሰዓት ዕላፊም ለትራንስፖርትም ችግር እዚሁ ማደር ይሻላል ብዬ ነው::"
"ባክህ አትፎግረኝ ያራዳ ልጅ አታውቅም? ፖሊስ ነህ ሴኩሪቲ ይሄን ያህል::"
"ውነቴንኮ ነው:: ጋዜጠኛ ማለት ሁለገብ ነው:: በኛ አገር አልተለመደም እንጂ አንዳንድ ፊልሞች ላይ አይተሽ አታውቂም?"
"እሺ! አንተ ስታሩ ነህ ማለት ነዋ!" አለችና ከት ብላ ሳቀችበት:: የንቀት ሳቅ::
"ግን አንቺ መግባቱን ለምን ፈራሽው?" አለ ብሽቅ ብሎ::
"ማ? እኔ? ምን ያስፈራኛል? ግየዳህ ገርሞኝ ነው እንጂ" አለች በማናለብኝ አነጋገር::
ተያይዘው ሲገቡ ለትግል ወደ መድረክ እንደሚወጡ ተፋላሚዎች



የጉሪጥ እየተያዩ ነው::
"በሩን እንዳትዘጋው" አለችና ደረቷ እየተንቀጠቀጠባት ባለመደገፊያው ወንበር ላይ ተቀመጠች::
"ለምን? ንፋሱ አያስቀምጠንማ!"
"ይሁን ተወው:: ቤቱ ይሞቃል::" ህብቴ ሳይዘጋ አለፋትና አልጋው ላይ ተቀመጠ:: እንደ ዓይጥና ድመት በጥርጣሬ ተፋጥጠው ዝም ሆኑ:: እርሱም እርሷም ሲጋራቸውን መሳብ ብቻ:: ትንሿ ክፍል የቃልቻ ቤት መሰለች:: -ጢስ በጢስ::
"ፈሪነኝ ማለት ነው?" አለ በልቡ ወኔውን እየታዘበ:: "እሷ እንደሆነች ምኗም ምኗም ወንዲላ! ታዲያ ማንኛችን ሴት ሆነን ነው የምንጀናጀነው?" ብሎ አሰበና "ህም!" ሲል ሰማችው::
"ምን ሆንክ?"
"ምነው? ተጫወች" አላት ተደናግጦ::
"ምን እጫወታለሁ! አንተ ለራስህ ተደብረሀ፣ እርፌ ጫቴን ስቅም ብውል ይሻለኝ ነበር" አለች ግማሽ ለራሷ በሚመስል አነጋገር::

ህብቴ ግን ህሳቡን ቀጠለ "እሃ! ተደብረሃል? እንደጠበቀችኝ አልሆንኩም ማለት ነው:: ፈሪ ነኛ! አሁን እወድሻለሁ ብላት መቀለጃ ልታደርገኝ እንጂ ፍቅር ብሎ ነገር የት ይገባታል? እረ አፌን አላበላሽም:: ደሞስ ሲክስ እንጂ ፍላጎቴ ከርሷ ፍቅር አልያዘኝ:: ይኼን ያህል ህርዳም አትመስለኝም ነበር:: ግን እንዛ ሴት ይመስል ተሽቀርቅረው ሲከተሏት የሚውሉት ጉረምሶች እንዴት አድርገው ነው. . . መቼም ለዳማ መሆን አለበት:: እንጂ እንደሁኔታቸው ለማንኛቸውም የግል አትመስልም:: ለዚያውም እርሷው ናት ስታሽከረክራቸው የምትውለው" ድንገት ብድግ አለ::

"ምን ልትሆን ነው?" አለች ቆጣ ብላ::
"መጣሁ ሽንት ቤት ደርሼ" አለና ሃሳቡን ቀይሮ ወጣ:: ትንሽ ቆይቶ ተመለስና እንደገባ በሩን ከኋላው ዘግቶ በመወርወሪያው ሲቆልፍ "ክፈት!" አለችው ትዕዛዛዊ በሆነ ቁጣ::
"አንቺ ከበሩ ምን አለሽ?"
"ትከፍታለህ ክፈት! እራዳ ሚሆንህ ነው? ክፈትልኝ እንዳውም እወጣለሁ!" አለችው ጥቁር ፊቷ የውድቅት ጨለማ መስሎ እየተነሳች::

ብድግ ከማለቷ ግብ ግብ እንደማይቀር ተረዳና ተሽቀዳድሞ በጥፊ ጠረቀማት:: ዞረባትና እንደጣዕረሞት ዓይኗን ጨፍና እጆቿን እያወራጨች አንገቱን አነቀችው:: ቶሎ ብሎ ጠለፈና ወደ አልጋው በኩል ይዟት ወደቀ::

# 18

"አጅሬው፣ ወንድ ሳይወጣህ አይቀርም" አለ ህብቴ እንዳለ ወደ ቢሮ ሲገባ::

ከምሳ መልስ እሱና አቶ ስምእን ሰዓት አክብረው ሲገቡ እንዳለ አምስት ሰዓት የወጣ ሩብ ሰዓት ዘግይቶ መድረሱ ነው::

"እንዴት?" አለ ምን ሊለው እንዳሰበ ቢገባውም ከራሱ ይምጣ ብሎ::

"እንዴ! የቅድሙ ነዋ! እንዲያ ነው እንጂ:: አለዚያማ ችክ ማለቱ እንደ ቁርበት ያቆረፍዳል:: በአርብ ዕለቱ ንዴት ቅዳሜና እሁድን በባትሪ ፈልገህ መሆን አለበት ያገኘሃት::" አለ በፌዝ::

"ምን ለማለት ፈልገህ ነው?"

"ያው ነዋ! ምን ማለት ያስፈልጋል? 'ስንተዋወቅ እንተናነቅ' አሉ:: ምን አስደበቀህ?"

"ምኑን ነው ያወቅከው? ምንም የምታውቀው ነገር የለም" አለና ወደ ራሱ ጠረጴዛ ሄደ::

"እሱን እንኳን ተወው:: ምሳ ላይ ባታጋጥሙኝና ባላያችሁ . . ."

"በቃ ምሳ አብሮ የበላ ሁሉ . . ."

"ያ ሌላ ይኼ ሌላ:: ተራ ግብዣ አለመሆኑ ያስታውቃል::"

"እንዴት?"

"አንደኛ ነገር አምስት ሰዓት ገደማ ስልክ አንስተህ ስትነጋገር የት ሆና እንደደወለችልህና እዚያው ጠብቂኝ እንዳልካት ካንተ ንግግር ሰምቻለሁ:: ሁለተኛ ደግሞ ምሳ ሰዓት ላይ ቡና ልጠጣ ሰወጣ እዛው ቡና ቤት ከልጅቷ ጋር አየሁህ:: አይተኸኝ የለም?"

"ታዲያ ባይህስ? ብታየኝስ?"

"እንደኔ አስተያየትማ እንዳውም የረዥም ጊዜ ፍቅረኛሞች ትመስላላችሁ:: ከበፊቱም 'ሽሽጌ' ነበረች መሰል::"

"መኸገር" አለው በልቡ ለምን እንደሚከታተለው በሽቆ::

"ምናችን ነው የረዥም ጊዜ የሚያስመስለን?"

"ሁኔታችሁ ነዋ! ሌላው ቀርቶ ወሬአችሁ እንኳን ያለማቋረጥ ነበር:: እስኪላመዱ ድረስ ወሬው ሁሉ 'ተጫወች-ተጫወት' ብቻ ነው:: እናንተ ግን እንዳውም ከተራ ጨዋታ አልፋችሁ በአንድ ሲርየስ በሆነ ጉዳይ የጦፈ ክርክር



የያዛችሁ ነበር የምትመስሉት::"

እንዳለ እውነቱን በመንገርና ባለመንገር አመነታ:: "ግን ለምን እነግረዋለሁ?" አለ:: በሱ የግል ህይወትና ጉዳይ ህብቴን ምን የሚያገባው ነገር አለ? እንኳንስ በሥራ ቦታና አጋጣሚ የተወሰነ ጓደኝነት፣ አብረው ያደጉብትስ ቢሆን ለግሉ የሚይዘው የግል ሚስጥር ላይኖረው ነው? ሲበዛ ግልጽነት ደግሞ የዋህነት ነው:: ለምን ያን ያህል ግልጽ ይሆንለታል? ልቡ ያሰበውንና የደረሰበትን ሁሉ እንደ ነፍስ አባት እየተናዘዘለት በገዛ እጁ ህሊናውን ሰላም ለሚነሳ አስተያየት የሚጋብዘው ለምንድነው? አንዳንዴ በራሱ ክልል ለራሱ ያለሁለተኛ ሰው ህሳብና እርዳታ የግል ሚስጥሩን ደብቆና ተደብቆ መኖር የለበትም ማለት ነው? ታዲያ ለምን ሥራዬ ብሎ እየተከታተለ ያውጣጣዋል? ምንስ ያገባዋል? . . ."

"ደሞምኮ አሥራ አምስት ደቂቃ አርፍደህ የገባኸው ወሬአችሁ የሞቀ፣ እድሜአችሁ የራቀ፣ ፍቅራችሁም የላቀ ቢሆን ነው" አለና ወደኋላው ተለጥጦ ያልመጣለትን ደረቅ ፈገግታ አሳየው::

"አያገባህም!" አለ እንዳለ ከሚገባው በላይ ጮኾ:: እንደገባ በሥራ የተጠመደው አቶ ስምእን ሳይቀር ቀና ብሎ በመገረም አስተዋለው::

"እሱማእኔ ምን አገባኝ:: በጓደኝነቴ ከስሞኑ ሁኔታህ የወጣህ መሰሎኝ ደስ አለኝ እንጂ::" አለ ህብቴ ቆሌው ተገፍፎ::

"አመሰግናለሁ! የጓደኝነት ምክርና አስተያየትህን ስፈልግ ትለግሰኛለህ:: እስከዚያው ግን የኔ የግል ጉዳዬ ነው::" አለ እንዳለ ያን ያህል አምርሮ መናገሩ ውስጥ ውስጡን ለራሱም እየተሰማው::

ህብቴ ገና እንደገባ ሊጽፍበት ከፊቱ ወዳስቀመጠው ባዶ ወረቀት በዝምታ አቀረቀረ:: ሌላው እፍረት:: ወረቀቱ ውሀ ሲርከፈከፍ የደረሰው፣ እሊያም ካፊያ የመታው መሰሏል:: ቀና ብሎ ወደ ሁለቱም የሥራ ባልደረቦቹ ተገላመጠና ቀስ ብሎ ወደ መሳቢያው አስገብቶ ሌላ ወረቀት አወጣ::

ክፍሉን ዝምታ ጮኸበት::

# 19

ዕኩለ ቀን እንደመሆኑ ከስድስት ኪሎ እስከ አራት ኪሎ መንገድ ግርግር በዝቶበታል:: ከየመስሪያ ቤቱ ወጥቶ ምሣ ፍለጋ የሚሩዋሩዋጠው ሠራተኛ፣ የጥዋቱን ፈረቃ አጠናቅቆ ቤቱ ለመድረስ ወይንም የከሰዓቱን ፈረቃ ለመጀመር ከየትምህርት ቤቱና ወደየ ትምህርት ቤቱ የሚጣደፈው የተማሪ መአት፤ ለንግድ ለሙግትና ለሌላም ሌላም የቤትና ማህበራዊ ጉዳይ ሲያልፍና ሲያገድም መስመሩን ለመጠቀም የተገደደ መንገደኛ . . . ሁሉም ሁሉም ከላይ ከታች እየተሰባጠረ ይመጣል ይሄዳል::

ተሺ ስልከኛውም በግርግሩ መሃል የልምዱን እያደረሰ ነው::

"ሁላችሁም ተመልከቱ!" ይላል አንዳች ነገር እንደሚያሳይ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ:: ላካባቢው እንግዳ የሆነ ወይንም ሥራ የፈቱ ህፃናት ካልሆኑ በስተቀር ልብ ብሎ የሚከታተለው የለም:: የሚራመዱበት መንገድ አስፋልት መሆኑን ሳያስላስሉ እንደሚያውቁት ሁሉ ያ በትርምሱ መሃል እየለፈለፈ ላይና ታች የሚመላለሰውም ሰው ዕብድ መሆኑን ያውቁታል:: ቁም ነገር ካፉ ይወጣል ብሎ የሚያደምጠው የለም:: -እብድ ነዋ! የሚገርመው ግን እርሱም ለሌሎች ያለው ትኩረት የነሱን ዐይነት መምሰሉ ነው:: የሚያናግራቸው የእርሱ ታዳሚዎች ባጠገቡ የሚርመሰመሱት ጤነኛ ተብዬ ሰዎች ሳይሆኑ ሌሎች ረቂቅ መጢቅ ለሰው የማይታዩ ሰዎች፣ ምናልባትም ዕብድ መናፍስት ናቸው:: እንደተማሪ ጠይቆ እንደተማሪ ቢመልስም ተማሪዎቹም ክፍሉም በዓይን አይታዩም::

"አስተውል! አስተውል! አንድ ጭልፊት፣ ሁለት ጭልፊት፣ ሦስት . . . ሰማዩ ላይ ብዙ ጭልፊቶች -መሬትስ? መሬት ደግሞ ብዙ ዶሮዎች:: አስር ዶሮ፣ ሃያ ዶሮ፣ ሰላሳ . . . ላስር ዶሮ አንድ ጭልፊት:: . . . ዶሮ መሬት ይጭራል፤ ጭልፊት ጫጩት ይበላል:: ሁለቱም ግን ክንፍ አላቸው:: ድሮ ድሮ አብረው ነበሩ:: የት? መሬት ነዋ! መሬት . . . :: ጭልፊት ለምን በረረ? በብልጠቱ በብልጠቱ:: ዶሮ ለምን ቀረ? እንጃለቱ እንጃለቱ::" ይልና ሮጥ ሮጥ ብሎ ይራመዳል::

"ህሎ! ህሎ! ተማሪ አዳምጥ! እባብ የሚኖረው ከድንጋይ መሀል ነው::



እባቡ እባቡ እባቡ::" እያለ የቀኝ እጁን አመልካች ጣት አስፋልቱ ላይ ቀስሮ ወደፊቱ ይሮጣል:: ደሞ ቆም ይልና "ህሎ! ህሎ! ህሎ! . . . ህሎ ይዝጋሽ ዝጋታም:: ህሎ! ህሎ! . . . ህሎ! የራሷ ጉዳይ::" ይላል እጁን እያወናጨፈ::

ከቅድስት ማርያም መብራት እስከ አምስት ኪሎ ድህረ ምረቃ ባለው ርቀት ሁለት ዙር ደርሶ መልሱን ጨረስና እንዲያ ሲጮህ እና ሲለፈልፍ እንዳልነበር በዝምታ ትከሻውን እጉብጦ፣ አንገቱን ሰብሮ ፈገግ ፈገግ ደግሞ ኮስተር ኮስተርተር እያደረገው ወደ አራት ኪሎ አቅጣጫ ወረደ::

"ተሺ ስልከኛው!" እያሉ ሲከታተሉትና ሲያዳንቁት የነበሩ ትናንሽ ልጆችም ተሰላችተው ተበተኑ::

ከስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ በመውጣት የግርግሩ ተሳታፊ የሆነችው ሩቂያ መሀመድ የጓደኛዋ አጉት ሁኔታ ካሁን ቀደም ከምታውቀው በላይ አሳዘናት:: እንደ ሞኝ ቆማ ስትመለከትና ስታዳምጠው ቆይታ ቁልቁል ሲወርድ እርሷም መንገዱን ይዛ ወደ ቀኝ ታጠፈች:: -ወደ ዳርምየለሽ ቤት::

♣ ♣ ♣

ተሺ ስልከኛው ከዛሬ ሃያ ሁለት ዓመት በፊት የኮራና የከበረ ወጣት የአንደኛ ደረጃ መምህር ነበር:: አቶ ተሾመ ማመጫ ወይንም ተማሪዎቹ 'ቲቸር ተሾመ' የሚሉት ጤናማና መልከ መልካም፣ ከዕድሜው አንጻር ቀበጥ የማይባል ይልቁንም ህላፊነት የሚሰማው የራሱና የታናሽ እህቱ አስተዳዳሪ ነበር::

እርጋታውና አስተዋይነቱ ከመልከ መልካምነቱ ጋር የማረካት አንዲት ፍቅረኛም ነበረችው:: ምሥራቅ . . . የምትባል:: ከእርሱ ወገን ያባቷን ስም የሚያውቅና የሚያስታውስ ባይኖርም በጣም ያፈቅራት እንደነበር በእርሷ ምክንያት ከተከሰተበት የህይወት ለውጥ ማንም መረዳት ይችላል:: ቀለበት አስሮላት ለጋብቻ ሲዘጋጁ ነው አንድ ቀን አብረው ውለው እስከ አራት ኪሎ በእግር ሸኝቷት የተመለሰው:: ሰፈሯ ካዛንቺስ ነበር:: ከአንድ ሰዓት ልዩነት በኋላ ስልኩ ሲያቃጭል አነሳ::

"አሎ! . . . አዎ፣ አዎ!" ብሎ ትንሽ እንዳዳመጠ "ኸ?" በማለት የስልኩን እጀታ በቁሙ ለቆ ራሱን ያዘ:: ፊቱ ጥቀርሻ ለብሶ ደርቆ ቀረ:: እንባ እንኳን አልነበረውም:: ከትንሽ ቆይታ በኋላ እንደገና ተስገብግቦ በማንሳት ሃሎ! ሃሎ! ሃሎ! . . ." እያለ ወተወተና መልስ ሲያጣ "ቺድ! የራሷ ጉዳይ!" ብሎ የስልኩን እጀታ በሀይል አሽቀነጠረው:: ግድግዳው ተቀብሎ ሰነጠቀው:: ስልኩን የደወለው ወንድ ይሁን ሴት በምን ዓይነት አነጋገር ምን እንዳለው

ወይንም የደዋዩን ማንነት ያወቀ አልነበረም:: ከእርሱ በስተቀር:: በኋላ ላይ የወሬ ወሬ ምሥራቅ በመኪና አደጋ መሞቷ ሲሰማ የታወቀና የተገመተ ነገር ቢኖር የስልኩ መልዕክት የሚወዳት ፍቅረኛውን ሞት የያዘ እንደነበር ነው:: አልቅሶ እንኳን አልቀበራትም:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ግን ስልክና ተሾመ አይጥና ድመት ሆኑ:: "ቲቸር ተሾመ" ይሉት የነበሩ የራሱ ተማሪዎች ሳይቀሩ 'ተሼ ስልከኛው' ብለው ጠሩት::

'ተሼ ስልከኛው፣ ድሮ የሳይንስ አስተማሪ የነበረው:: ተሼ ስልከኛው፣ ለቁርስ ለምሳና ለራት ሁለት ዙር ምክ የሚበላው:: ተሼ ስልከኛው -ያ! በስልክ ያበደው::' ሴላም ሴላም ይሉታል ያራት ኪሎ ሰፈር ልጆች ስለእርሱ ማውራት ሲፈልጉ::

ይህ በአጭሩ ዳርምየለሽ ከእናቷ ሰምታ ራሷም አገናዝባ ለሩቂያ የነገረቻት የተሼ ስልከኛው ታሪክ ነው::

"እንዴት ቢወዳት ነው?" አለች ሩቂያ በፍቅር ጦስ ማበዱ ሳያንስ እስካሁን "ሀሎ" እንዳለ አብዶ መቅረቱ ልቧን ነክቶት:: ሁል ጊዜም ያሳዝናታል::



# 20

ዳርምየለሽ ብቻዋን ተሸክማ ስትጨነቅበት እና ስታብጠለጥለው ሳይታወቃት ራሷን ለአካላዊና መንፈሳዊ ጉስቁልና የዳረገችበትን ችግር፣ እንደሲኦል ከብዶና ቀፍፎ ያስፈራትን አባት የለሽ ህይወት በማወቅና ባለማወቅ፣ በማመንና ባለማመን መሃል እያመነታች በውስጧ ሲፋጭና ሲተራመስ የሰነበተውን የህሊና ቁስል ለጓደኛዋ ካካፈለቻት ወዲህ መፍትሄውን ባታገኝለትም በመተንፈሷ ብቻ በመጠኑ ቀለል ብሏታል::

ሩቂያም ከቅዳሜ ዕለት ወዲህ እሁድና ሰኞን እየመጣች አጽናንታታለች:: ሆን ብላም ሻይ ወይንም ቡና እንድታፈላላት ትጠይቃትና ለሥራ ጉንበስ ቀና ስትል ከሃሳቧ እንድትሸሽ ታደርጋታለች:: አንድ ሁለቴ ካየችው በኋላ ግን ራሷ ዳርምየለሽም የጉልበት ሥራ ጥሩ የሃሳብ ማቃለያ መሆኑን ተገንዝባ በቤት ሥራ እናቷን መርዳቱን ተያይዛዋለች:: አልቀነስ ያላትና መፍትሔ ያጣችለት ነገር ቢኖር የለሊቱ ሃሳብና ጭንቀት ብቻ ነው::

ዛሬም ከጧት ጀምሮ በልብስ አጠባ ነው የዋለችው:: ወይዘሮ ብዙ በነዚህ ሦስት ቀናት ልጃቸው ያሳየችው ለውጥ እያስደነቃቸው ነው:: አንዴ ፈጣሪያቸውን ሌላ ጊዜ አባ ደርብን እያመሰገኑ ለቅድስት ማርያም የተሳሉትን ያስር ብር መጋረጃ በሚቀጥለው ክብሯ ዕለት እንደሚያስገቡላት ደጋግመው ቃላቸውን ያድሱላታል:: እማማ ሸዋም አሥር አሥር ጊዜ እየመጡ በምክራቸው ውጤታማነት ተደስተው "እሳቸውኮ ለሁሉ እሺ አይሉም እንጂ መዳኒት ናቸው::" ይላሉ አባ ደርብን እያሞካሹ:: ቀለብተኞቹም ለምሳ ሲመጡ ዳርም የለሽን ከደጅ ሲያይዋት ተደስተዋል:: ሩቂያም ገና የአጥሩን በር ስትገባ ዳርምየለሽ ፈገግ ስትል በማየቷ አብሯት ፈገግ አለች::

♣ ❧ ♣

"አባባ ከፍ ያለው ናቸው ጠላቴ" አለች የቀረበችውን እንጀራ ወጥ ሳታስነካ እጇ ላይ እንዳለ በጥርሷ ነክሳ:: አጠባውን ጨርሳ በወ/ሮ ብዙነሽ መኝታ ቤት ምሳ እየበሉ ነው::

"እንዴት?" አለች ሩቂያ ምሳ እየበሉ በፈጠሩት ዝምታ መሃል

ዳርምየለሽ ሃሳቧን ስታሰላስል እንደቆየች ገብቷት:: እያሳየች ያለችው ለውጥ ቢያስደስታትም የወሬዋ መክፈቻ ተመልሶ ያው መሆኑ ያበሽቃታል::

ዳርምየለሽ ደግሞ ሚስጥሯን የተነፈሰችው ለእርሷ ብቻ በመሆኑ የሚሰማትን በነገረቻት ቁጥር መፍትሔ የምታገኝ ይመስላታል:: "መርዝ ቃላቸውን ተናግረው የሀሊና እሾህ ባይተክሉብኝ ኖሮ ይኼን ያህል ራሴን አስጨንቄ እናንተንም እሚያስጨንቅ ችግር ውስጥ ባልከተትኳችሁ ነበር::"

"እንደእኔ ግን ምንም ጥፋት የለባቸውም:: ስልሽ፣እንደነገርሽኝ ከሆነ ሆን ብለው አንቺን ለማስጨነቅ እና ለመጉዳት የተናገሩት አይመስለኝም:: ምናልባት ካንቺ የተደበቀና ሳታውቂ ያደግሽው ሚስጥር መሆኑን አያውቁም ወይንም ደግሞ በጥያቄ ወጥረሽ ስለያዝሻቸው ለጊዜው ካፍ አምልጧቸውም ሊሆን ይችላል:: አንቺን ያስከፋሽ ያስደለትሽ በምን ያውቃሉ?"

"እሳቸው ቢያውቁም ባያውቁም ለኔ ዕድሜ ልኬን ተደብቆ የኖረውን የቤተሰብ ሚስጥር ማወቄ በውስጤ የፈጠረብኝ የስሜት ረብሻ ቀላል አይደለም:: ባልሰማና ባላውቅ ኖሮ ቢከፋም ቢለማም በተለመደው ሁኔታዬ የዚህኛውን አባትነት ብቻ እንደተቀበልኩ እኖር ነበር:: 'አባቴ ማን ነው? የት ነው ያለው?' እያልኩኝ በእንጀራ አባትና በተፈጥሮ አባት መካከል ያለውን ልዩነት በማሰላሰል እኔ ልመልሰው በማልችለው የጥያቄ ጋጋታ ራሴን አላስጨንቅም ነበር:: አየሽ ለዚህ ሁሉ የዳረገኝ 'ያ እንጀራ አባትሽ' የምትለዋን እስከአሁን ከነድምጻቸው ጆሮዬ ላይ የምትደውል ቃል ካንደበታቸው መስማቴ ነው::"

"ይኼ ይመጣል ወይንም ይደርስብሻል ብለው አላሰቡት ይሆናል ለማለት እንጂ እሱማ ባትሰሚ ኖሮ እንደዚህ እንደማትሆኚ እኔም ይገባኛል:: አንዳንዴ በእንደዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በሌላው በሌላው ማኅበራዊ እንቅስቃሴም ውስጥ ቢሆን አለማወቅ ከማወቅ የሚሻልበት ጊዜና አጋጣሚ አለ:: ከግንዛቤሽ ውጪ ተደብቆ ስለቆየ ጉዳይ ጫፍ ስትይዢ 'ለምን? እንዴት?' እያልሽ ራስሽን መጠየቅ ትጀምሪያለሽ:: ለጥያቄሽ በቀላሉ አጥጋቢ ምላሽ ስታገኚ በማወቅሽ የምትደሰችና የምትረኪውን ያህል ምላሽ ሲታጣለትና ጥያቄ ጥያቄን እየወለደ ወጥሮ ሲያስጨንቅሽ ማወቅሽን ትጠይዋለሽ:: ሳታውቂ ባሳለፍሺው ጊዜ የነበረሽን ሰላምና ደስታም በማወቅሽ ታጫዋለሽ:: በተለይ መታለልና መበለጥን ማወቅ ቁጭትን በቀልንና አመጽን ይወልዳል:: አለማወቅ ግን ከመሠረቱ ትክክልና ዕውነት ያልሆነን ዕውነት አሜን ብለሽ እንድትቀበይና ተስማምተሽበት እንድትኖሪ ያደርግሻል:: 'የማያውቁት አገር አይናፍቅም' ይባል የለ ከነተረቱ:: ገነት መኖሩን እስካላወቅሽ ሲኦልን ገነት አድርገሽ ትኖሪያለሽ:: እንደዛ ስልሽ ግን አንቺ ሌላ አባት እንዳለሽ ሳታውቂ ያሳለፍሺው ጊዜ መጥፎ ነበር ለማለት አይደለም::" አለች ሩቂያ ሳይታወቃት የጓደኛዋን ስሜት የነካች ስለመሰላት በስተመጨረሻ ራሷን ለማረም እየሞከረች::



"መጥፎም ነው፣ ጥሩም ነው::"

"እንዴት?"

"እንጀራውን ተውሺው እንዴ? ትንሽ ብይ እንጂ?"

"በቃኝ ዴሪ! በላሁ"

"በቃኝ ያለና ፈራሁ ያለን አይገለግሉትም ትላለች እማዬ" አለች ዳርምየለሽ እርሷም ስለበቃት ትሪውን ይዛ እየተነሳች::

"ውነታቸውን ነው" አለች ሩቂያ እጇን ልትታጠብ እየተከተለቻት::

"ጥሩ ነው ያልኩሽማ" አለች ዳርምየለሽ ተመልሰው እንደ ተቀመጡ::

ሩቂያ ጓደኞዋ ነገሩን የረሳችው መሰሏት ነበር:: ሆኖም አወራሯ የመጨነቅ ሳይሆን በውይይት ዓይነት ዘና ያለ በመሆኑ ዝም ብላ ልታዳምጣት ወሰነች::

"የልጅነት፣ የሀፃንነት ዘመኔን በእንዲህ ዓይነቱ ሀሳብ ሳልወጠር እንደማንኛውም ሰው ጭቃ አቡክቼና አቧራ ተራጭቼ እኩዬቼ ሲመቱኝና ሲያስለቅሱኝ 'አባዬ ሲመጣ . . .' እያልኩኝ ለለጋ አዕምሮዬ መከታ አድርጌ ሳስፈራራበትና ውጪ ቆይቶ ሲመጣም በሙሉ ልብ እጆቼን እያርገበገብኩ ስቀበለው ይሰማኝ የነበረው ንጹህ የልጅነት ስሜት ልጁ አለመሆኔን ባውቅ ኖሮ ገና ከማለዳው በህፃን አዕምሮዬ ላይ ሊያስከትል ይችል ከነበረው የሥነ-ልቦና ችግርና በርሱም ሳቢያ ሊደርስብኝ ከሚችለው የሥነ-ምግባር ብልሽት፣ እንዲሁም ቤተሰባዊ ልዩነት እና አለመጣጣም እንደጠበቀኝ ሳስብ ጥሩነቱ ጐልቶ ይታየኛል:: በሌላ መልኩ ግን አሁን ያለሁብትን ሁኔታ ሳገናዝብና እስካሁን ያሳለፍኩት ባለአባትም ባለእናትም የነበርኩበት ሙሉው እኔነቴ ይሰጠኝ የነበረው የልጅነት ደስታ ከእንግዲህ በኋላ ሊቀጥል እንደማይችል ጐዶሎነቴ ሲሰማኝ መጥፎነቱ ገዝፎ ይታየኛል:: አለችና እንዳጀማመሯ ሳይሆን ቅንድቦቿ ቁጥር ዓይኖቿ ቅስሟን ይዘው ሰብር እንዳሉ አቀረቀረች::

"ደሞ ጀመራት" አለች በሆዷ አዝማሚያዋ አስፈርቷት:: ሆኖም ምንም አልተናገረችም:: ዝምታዋን በዝምታ ማዳመጥን መረጠች:: የዳርምየለሽ እንባ ቀስ እያለ መንከባለል ሲጀምር ግን አላሸቻላትም::

"ኤጭ አሁንስ አበዛሽው፣ አባቴ ይሙት ልክ አይደለሽም!" አለቻት ቆጣ ብላ የተቀየመች በመምሰል::

ዳርምየለሽ ግን የጓደኛዋ መቀየም ሳይሆን የተሰማት መሃላዋ ነው:: ጓደኛዋ የማያጠራጥርና የማያሻማ አባት ስላላት፣ ልጅነቷ ስለማያጠራጥርና ሙሉ ዕምነት ስላላት በአባቷ ስትምልባቸው ቅር አይላትም:: እርሷም እስከ ቅርብ ጊዜ እንዲህ ነበረች:: "ባህሩዬ ይሙት! አባቴ ይሙት!" አሁን ግን

ገና በዘሩ እለዚያም በቡቃያው ሀብትሽ በሀብቴ የሚላትና የችግሯን ገፈት ቀምሶና ቀንሶ አይዞሽ የሚላትን የህይወት ተጋሪ ካገኘች ደግሞ አባትነቱን እንዲያውሳት ቃል ኪዳኑን ተቀብላ እውነተኛውን ሚስጥር ከልቧ እንደቀበረች መኖር ትጀምራች:: ልጇን በአባታዊ ፍቅርና አቀራረብ እስካየላት የቱንም ያህል የኑሮ በደልና ምሬት በራሷ ላይ ቢያደርስባት፣ ሳትወደው ተስማምታ፣ ሳይመቻት ታግሳ ለልጇ ስትል እህል ውሃዋን አርዝማ እንዳቀረቀረች ህይወቷን ትገፋለች::

በዚህ መሀል ያንድ ጉን ሀረጉ ተቆርጦ ከሌላ የተቀጠለሰትን ልጅ ሚስጥር የሚያውቅ ዘመድ አዝማድ እለዚያም የውጭ ታዛቢ አውቆም ይሁን ሳያውቅ መጋጠሚያው ላይ ይነካካውና የልጁ ህልውና ተናግቶ በይሉኝታ የተቀጠለሰትን በጥሶ የራሱን የተፈጥሮ ሀረግ መምዘዝ ይፈልጋል:: ነህ ተብሎ በተሰጠው ሰው ሠራሽ ማንነት ተቀጥላ ሆኖ ሰመኖር ሲችገርም የሥነ-ልቦና ጭንቀት ውስጥ ይዘፈቃል:: ለችግሩ ማቃለያ ሰውሳኔው መዳረሻ ይረዳው ዘንድ ድፍረት አግኝቶ የአባቱን ማንነት ከጠየቀ፣ ከእውነተኛው ታሪክ ርቃ አዲሱን የልጇን ልጅነትና የባሏ አባትነት እንደተፈጥሮ ነባር፣ እንደቀንና ለሊት ዕውነት ብላ ለራሷ ሳይቀር ያሳመነችው እናት ለዓመታት ተንከባክባና ስስታ ያደረሰችው ፍሬዋ ለሁለት መሆኑ ሲሰማት ክፉኛ ልቧ ቆስሎ ያሳዝናታል:: ያስቆጣታል:: ያስመርራታል::

“ሰባብሺና እንውጣ እንጂ” አለች ሩቂያ ከገባችበት ህሳብ አይሉት ትካዜ ወጥታ በመሃላቸው የገባውን የዝምታ ግድግዳ በመስበር::

“ገና አይደል እንዴ ሰዓቱ?”

“ሰዓቱ እንኳን ገና ነው:: ቀደም ብለን እንውጣና እስከዚያው ዘወርወር እያልን እንቆይ::”

“አሁን ስንት ሰዓት ነው?” አለች ዳርም የለሽ ለእንዳለ የሰጠችው ሰዓቷ ትዝ እያላት::

“ለዘጠኝ ሩብ ጉዳይ ሆኗል:: እስክትዘገጃጂ፣ ቡተለይ ፀጉርሽን እስከታጫውቺ ያን ያህልም ብዙ ሰዓት አይቀረንም::”

ሩቂያ፣ ዳርምየለሽ ከሞላ ተፈጥሮዋ ፀጉሯን አብልጣ እንደምትወድ ታውቃለች:: ሥራ በፈታች ቁጥር የእጇ ማረፊያ ፀጉሯ ነው:: ዳግማዊ ምኒልክ አብረው ሲማሩ በእረፍት ሰዓት ወይንም አስተማሪ በሚቀርበት ፔሬድና በሚዘገይበት ፋታ ሁሉ ፀጉሯን በትከሻዋ ወደፊት አውርዳ መፍታት ማሰር ነበር ሥራዋ::

“ጀመርሽ እንግዲህ ፀጉርሽን ማጫወት” ትላት ነበር::



# 21

በሀሳብ ስለተወጠረ ድካምና ጊዜን ለመቆጠብ ታስቦ ከረዥሙ ህንፃ መሃል የሚሹለከለከው አሳንሰር ትዝ አላለውም:: እርሱ ብቻ ሳይሆን አብዛኞቹ የሰባተኛ ፎቅ ጋዜጠኞች ህሳባቸውን እየገመዱ በጠመዝማዛው የእግር መወጣጫ ሽቅብ ቁልቁል የሚሉት ሳይታወቃቸው በመሆኑ ብዙ ጊዜ አይጠቀሙበትም:: -አሳንሰሩን::

በስልክ በሰጠችው ቀጠሮ መሠረት እዚያው አካባቢ ከሚገኝ አንድ ቡና ቤት እየጠበቀችው ነው:: የሚያስሳስሰውም ለለእርሷ ነው:: የከትናንት ወዲያው አጋጣሚ ለመናገር የሚያስቸግር መገረምን አሳድሮበታል:: ማንም ሊያምነው ስለማይችል እስካሁን ለማንም አልተነፈሰው:: ገጠመኙ ግን እንደ ተአምር አስደንቆታል:: ትናንት ለእንዳለ ሊነግረው አስቦ በዛች ልጅ ምክንያት ስለተበሻሸቁ እንደማያዳምጠው ገምቶ ተወው:: ዛሬም ብዙ አልተነጋገሩም:: ሲሰማ ምን ያህል እንደሚደነቅ ለማየት ጓጉቶ ነበር:: ራሱማ አሁን አሁን እያሰበ ፈገግ ይላል:: እንዳዲስ እያስገረመው::

♣ ♣ ♣

እንዲያ ዞሮባት አልጋው ላይ ከጣላት በኋላም የነበረው ግብ ግብ ቀላል አልነበረም:: ሀይሏን ሳታሰባስብ ሁለቱን እጆቿን ደረቷ ላይ አጣምሮ በቀኝ እጁና በደረቱ ተጭኖ ወደ አልጋው እየደፈቃት እንደምንም የሱሪዋን ዚፕ በአንድ እጁ ከፈተው:: ወደጐን ተንሸራትታ ባለ ኃይሏ ገፈተረችው እና ብድግ ስትል የሱሪዋን ቀበቶ መዋያ ከኋላ ቀብ አደረገው:: ሱሪዋ ለእርሱ እንዳገዘ ሁሉ ዝቅ ብሎ የውስጥ ሱሪዋን አጋለጠው:: አልጋው ላይ እንደተቀመጠ በገዛ ሱሪዋ ሳበና ከለር እግሯን በእግሩ ሲጠርባት ወደርሱ ወደቀችለት:: ይዟት ተንጋለለ:: በአንድ እጁ ሀይሏን እየተቆጣጠረ አንደኛውን እጁን የውስጥ ሱሪዋ ላይ ሲያሳርፍ አንድ እጁን አስለቅቃ በጥፊ ጠረቀመችበት::

“እናትህ ትወቃ!”

ከዚያ በኋላ እንዴት እንዴት አድርጉ እንደመታት አያውቀውም::
“እሺ በቃ! አትምታኝ” አለችው በተዳከመ አነጋገር::

ዱላውን አቁሞ መሬት እንደቆመ ጉልበቷ ላይ የደረሰ ሱሪዋን ሊያወልቅ ሲታገል "እራሴ አወልቃለሁ!" ስትል አምባረቀችበት። ቁጣዋ የመሸነፍ መሆኑ ስለገባው ውስጡን ደስ እያለው ወደ አልጋው ወጣ።

በብርድ ልብሱ እንደተከለሉ ፍርሃቷ ከምን የመጣ እንደሆነ ባይገባውም ጆሮዋን ጡቷን ጀርባዋንና ጭኗን እያሻሸ ቀስ በቀስ ሰውነቱን አላመዳት። ዓይኖቿን አስለምልማ ከናፍሯን ስታስጠጋለት ግጥም አድርጐ መጠጣት። በዚህ ጊዜ ነበር ከናፍሮቻቸው እንደተጋጠሙ ወገቡን አጥብቃ ይዛ ጭኖቿን የፈለቀቀችለት።

እንደመጀመሪያው ሁሉ የፈቃዷን ትግልም በአሸናፊነት ጨርሶ በአጋጣሚው የራሱን ዕውቀት እየተጠራጠረ ተነስቶ ሲደነቅና ሲያጉተመትም የህመም ስሜት ከገጽታዋ እየተነበበ ቀስ ብላ አንሶላውን ከጠርዙ ወደ መሃል አጠፈችው።

"ሶፍት ይዘሀል?"

እንደዋዛ የያዛትን ሶፍት ሰጣትና ሌላም ስትጠይቀው መሃረቡን ሰጣት።

"እናትክንና አሸነፍከኝ አይደል?"
"አውሬ እኮ ነው የሆንሽብኝ!"
"እንዳውም ምን እንዳቀመስከኝ እንጃ"
"እንዴት?"
"ከዚ በላይ ምን አለ? እዚህ ድረስ እንደ በግ ተጐትቼ መምጣት። የቁጩህን ክላስ ይዘህ ስትገይደኝ እያወኩኝ መግባት።. . ."
"ቁጩ መሆኑን ካወቅሽ ለምን ገባሽ? ከገባሽ በኋላስ ምን አታገለሽ?"
"መጀመሪያማ ንቄህ ነው የገባሁት። ካነቀኸኝም በቦክስ ነፍቼው እወጣለሁ። ምናባቱ ያረገኛል ብዬ።"
"እንደ ወንድ ስለለበስሽ እና ከወንድ እኩል ስለዋልሽ ሴትነትሽን ረስተሽዋል ማለት ነው?" አለ ባድናቆት እየሳቀ። "ወንድ ልጅ ምንም ቢሆን ወንድ ነው"

"እሱን እንኳን ተወው። በጉልበትህ አይደለም ያሸነፍከኝ።"
"ታዲያ በምንድነው?"
"እኔ እንጃ! ከበፊቱም ሳንቱ ያለኝ ልብና አቀራረብ የተለየ ነበር።"
"ምን ዓይነት?"
"አላውቅም" አለች እንደ ማፈርም እንደ መቆጣትም እያደረጋት።
"እንዴት አታውቂም? ትጠይኝ ነበር?"



"ብጠላህማ ለባዶ ሻይ በየቡና ቤቱ ስትቀጥረኝ ምን ያመጣኛል። እናትክንና አንተ፣ እኔኮ ምንም ይሁን ምንም ወንድ አሸንፎኝ አያውቅም" አለችው።
"ታዲያ የመውደድ ከሆነ ለምን ያን ያህል ተፋለምሽኝ?"
"በቃእ! እንዲህ ይሆናል ብዬ አልጠበቅኩም። ለዛውምኮ ምንም ቢሆን ገርልነቴ እንድፈራ ያደርገኛል።"
"ግን ርግጠኛ ገርል ነሽ ማለት ነው?" አላት ሊጠይቃት ሲፈራ ሲቸር ራሷ በማንሳቷ ተደስቶ።
"ኸረ ይኼ ጤባ! ይኼን እንኳን አታውቅም? ይኼ ሁሉ ደም አባትህ ያረደው ዶሮ መሰለህ!" አለችው ብርድ ልብሱን ገልጣ ደም የነካውን አንሶላ እያሳየችው።
"ማለቴ፣ ከዚያ ሁሉ መልክ ሰሎሞን መህል እየዋልሽ መቼም እስከዛሬ መቆየትሽን ለማመን ያስቸግራል።"
"ያ! ሌላ ጥያቄ ነው። ከወንድ ጋር ስላፋ ብውል ወንድ ሆኜ ነው። ኩዴ፣ ምርቃና፣ ጨብሲ ከሚያተራምሱት መሃል ውዬ ላድር እንኳን ሊደፍሩኝ ጠይቀውኝ አያውቁም።"
"እሺ እነሱስ አይድፈሩሽ። መቼም ሰው ነሽና እንዴት አንቺ ሴትነትሽ አይፈታተንሽም?"
"ወይ ሴትነት! ሴትነቴን ያወቅኩት ገና አሁን ነው። እስከ ዛሬ ካንድ ነገር በቀር ወንድ ነኝ ብዬ ነበር የማምነው።"
"ይኼ መቼም ተአምር ነው! ዛሬስ?"
"ዛሬማ ምን ጥያቄ አለው?"
"አሳመንኩሽ አይደል?" አለ ወደርሷ ጐንበስ ብሎ ትከሻዋን ግራና ቀኝ ያዘና። ዝም አለችው።
ከንፈሯን ሳም አድርጐ "ወንድ ነኝ አይደል?" አላት እየሳቀ።
"ቡዳ!" አለች ትክ ብላ እያስተዋለችው።
"ቡዳ ነህ!"
"እንዴት?"
"በቃእ! ቡዳ ነህ። እኔ ግን ቅድም አምልጬህ ቢሆን እስከ መቼም አልቀርብህም ነበር።"
"ለምን?"
"በቃእ! ከዛሬ ጀምሮኮ 'ሳቢ ገርል' ብዬ ለመናገር አፍራለሁ።"
"አሃ! ለካ ይኼ ነበር ሚስጥሩ! ቅዲያ ምን ችግር አለው? 'ሳቢ ሌዲ' ብለሽ መቀየር ነዋ!" አለ ከት ብሎ እየሳቀባት።
"እናትክንና ምን ያስቅሃል? ሴት መሆን ከጀመርኩ በኋላማ ከሰውነቴና ካለባበሴ በስተቀር ወንድ የሚያስመስለኝ ድፍን ልብ እንደሚኖረኝ ያጠራጥራል።"
"ለምን?"
"አላውቅልህም! ይልቅ ሲጋራ ጠማኝ"

♣ ♣ ♣

የቅዳሜ እለት ገጠመኙን እንደገና በሀሳብ እያጠነጠነ እቀጠሮአቸው ቦታ ደረሰ። ሳቢ በረንዳው ላይ በተለመደው አለባበስና ወንዳ ወንድ ሁኔታ ተቀምጣለች።

"ሃይ!" አለች አጠገቧ ሲደርስ እፍረት ይሁን መሽኮርመም ከሁለት አንዱ ገጿ ላይ ተነበበው። -አዲስ ነገር።

ለሰላምታዋ አፀፋውን ሰጣትና ቆመ። እንዲቀመጥ ጋበዘችው። ሌላ ቦታ ቢሄዱ እንደሚሻል ገለፀላትና ተያይዘው ወደ መንገድ ገቡ። ሲጋራ ለኩሶ ለእርሷም ሰጣት።

"አይ ሲ!" ብሎ ቆመ የስድስት ኪሎን መንገድ ይዘው አዲስ ባንክን ከፍ እንዳሉ።

"ምን ሆንክ?"

"ሹፌያቸው"

በግንባሩ ወዳመለከታት አቅጣጫ ዓይኖቿን ስትወረውር ዳርምየለሽን ከአንዲት ልጅ ጋር አየቻት። ከፊት ለፊታቸው እየመጡ ነው።

"ታዲያ ምን ይሁን? ምን አስደነገጠህ?"

ወዲያው ሲተላለፉ ሀብቴና ዳርምየለሽ የርቀት ሰላምታ ተለዋወጡ። ሳቢ ዳርምየለሽን በግልምጫ መሬት ደባለቀቻት።

"እናትክንና ከኔ ጋር ስላየችህ ነው አይደል የደነገጥከው?" አለች ወደ ሀብቴ ዞራ።

"ሳቢ ደግሞ ዝም ብለሽ ነው እምታወሪው። የጓደኛዬ ሚስትኮ ናት።" አለ ሀብቴ።

"ባክህ ዝጋ! ጓደኛህንማ ፈንግላዋለች። ያደረ አፋሽ ልትሆን ፈልገህ ይሆናል እንጂ" አለችው ተቆጥታ።

"መቀናቱ ነው?" አለና በልቡ "አልገባሽም"

"ምኑ?"

"እነሱን ሳይ መደንገጥ ሳይሆን የተገረምኩበት"

"እሺ ምንድነው?"

"አየሽ ትናንት ጧት ያችኛዋን ልጅ እንዳለ ሲጀነጅናት ነበር። ስልክ ደወለችለትና አምስት ሰዓት ላይ የወጣ በምሳ ሰዓት ሁሉ አብረው ሲዝናኑ ስላየኋቸው ዛሬ ደግሞ ሳታስጠጣ ከሷ ጋር ሳያት ገርሞኝ ነው።"

"ታዲያ ይኼ ምን ያስደንቃል? ጤባ! አሪፍ ፍንገላ ነው እንጂ! ሲያዩት ገገማ ፊት ነው፤ ለካ አልም ያለ ጭስ ነው። ጓደኛዋ ናት ማለት ነው።"

"መሆኗ ነዋ! ሌላም ነገር ገባኝ።"

"ምን?"



"ማነው ስሙ በቀደም የነገርሽኝ?"

"ማን?"

"ይኼ እንኳን አስረገዛት ምናምን ያልሽኝ?"

"እ!ያ ሾላ? ፈጠነ ነዋ"

"አዎ ፈጠነ፤ አየሽ ሳስበው እሱንና ዳርምየለሽን ያጋየደቻቸውም እሷ ልትሆን ትችላለችኮ። ሁለቱን አጋያይዳ እሷ በጐን እንዳለን። እንጂ መቼም ዳርምየለሽ ራሷማ ከእንዳለ በቀር ወንድ ያለ እንደማይመስላት አውቃለሁ።"

"ባክህ ተዋቸው። ምን ይጠበስ ነው እምትለው?" አለች ወሬው ሁሉ እያበሸቃት። ስለ ዳርምየለሽ ማሰብም መስማትም አልፈለገችም።

"እሱማ የራሳቸው ጉዳይ። ግን . . ." አለ እንደገና ቆም ብሎ።

"ግን ምን?" አለች እሷም አብራው እየቆመች።

"አሁን ወዴት እንደሚሄዱ. . ."

"የትም ይሂዱ። ሲፈልጉ ገደል ይግቡ።" ብላ አቋረጠችው። በንዴት ደረቷ ይንቀጠቀጣል።

"ለምን ትንሽ ተከትለናቸው የት እንደሚሄዱ አናይም?" አለ።

"ለምን? ለምንድነው እምንከተላቸው?"

"ምን መሰለሽ? እንዳለኮ ጓደኛዬ . . ." ሊናገር ያሰበውን ሳይጨርስ አሁንም አቋረጠችው።

"እንዳለ ምናምን ገደል ይግባ!"

"ሳቢ ደግሞ ምን ያስቆጣሻል። ቀስ በይ እንጂ ደግሞ ስትናገሪ ድምጽሽን ቀንሺው። በመንገድኮ ሰው እየተላለፈ ነው።"

"ሲፈልጉ እናታቸው ትወቃ!" አለች የቀኝ እጇን ማህል ጣት ቀስራ ዞሪያዋን የሚተላለፈውን ሰው በንዴት ፊት እየቃኘች።

"ተይ እንጂ። ይኼማ ደስ አይልም። ከኔ ጋር ሆነሽ እንደዚህ . . ." ሲል ለሦስተኛ ጊዜ አቋርጣ በጥፊ ላሰችው።

"ለእናትህ ንገራት!"

# 22

"ምን መስለሽ እማዬ ጨንቆኝ ነው::"

"እኮ ምንድነው ልጄ ንገሪኝ እስቲ ምንድነው?" አሉ የልጃቸው ጭንቀት በእናትነት ስሜት እየተጋባባቸው::

በህያ ቀን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሩቂያ ጋር ወጣ ብላ በመምጣቷ ወደ ቀድሞው ጤንነቷ የተመለሰች መስሏቸው ተደስተው ነበር ያመሹት:: እንደመጣች ራት አቅርበው ማዕዱ ሲነሳ መኝታ ቤት ይዛቸው ገባች:: ለሚስጥር ስለፈለገቻቸው የእናትነት ወግና ኩራት ተሰምቷቸዋል::

ዳርምየለሽ አንገቷን አቀርቅራ ቀረች:: እናትም ልጃቸው የምትነግራቸው ሚስጥር አስቀድሞ ስላስፈራቸው ደግመው ለመገፋፋት ድፍረት አጡና ራሷ እስክታመጣው በትዕግስት መጠበቅን መረጡ:: እርሷ ግን ፈራቻቸው:: ምን ብላ ትጠይቃቸው? የትኞቹን ቃላት ብትናገር ነው የእናቷን ልብ አራርታና የእስከዛሬ እምነትና ፍላጐታቸውን በማላላት ካለምንም ግጭትና ጥላቻ እውነተኛውን ሚስጥር ልታውጣጣቸው የምትችለው? ለጊዜው የመጣላት ሁሉ ከበዳት::

በእናትና ልጅ መሀከል የተፈጠረው መፈራራት በቀላሉ የሚወገድ አልሆነም:: ሁኔታው ያሳሰባቸው እናትም ሰሞኑን ሁሉ 'ይሆን እንዴ?' እያሉ በአዕምሮአቸው ሲያጉላሉትና ሊሆን እንደማይችል ሲደመድሙ ያቆዩትን ግምት ራሳቸው አፍርጠው ጥርጣሬአቸውን ለማስወገድ አለዚያም በጊዜ እንደሚሆን እንደሚሆን ለማድረግ ቆረጡ::

"እኔምለው ልጄ?" አሉ የገዛ ልጃቸውን እንደ ንጉስ ፈርተዋት አፋቸውንም ሀሳባቸውንም ያዝ እያረጉ:: "እኔ እምለው . . . እንዲያው . . መቼም ትክሻ ጠበብ ዳሌ ሰፋ ማለት ከጀመረ በኋላ መቼም. . . እንዳው መቼም ብዙ ችግር . . ." ሲሉ አቋረጠቻቸው::

"ምንድንነው እምትይው እማዬ? ምን ለማለት እንዳሰብሽ ገብቶኛል::"

"እንግዲያውስ ከገባሽ፣ እንዲያው ምናልባት ችግር ገጥሞሽ እንደሆን ብዬ ነው::" አሉ በደፈናው::

"የኔ ችግር አንቺ እንዳሰብሺው አይደለም:: ደግሞስ እማዬ፣ በእንዲህ ዓይነቱ ነገር ትጠረጥሪኛለሽ ማለት ነው?"



"እረ! ምን በወጣሽ የኔ ልጅ! እንኳን እኔ ሠፈርተኛው የሚያወራው የብዙነሽ ልጅ ጨዋ ናት፣ ጉብዝ ናት፣ መውለድ እንደሷ ነው:: እያለ ነው:: ትንሽም ስሜን በክፉ ያስነሳዋል ብዬ የምፈራው ይኸው የተረገመ ወንድምሽን ነው:: እርሱም ቢሆን ወንድ በመሆኑ ከእንዲህ ዓይነቱ ጉድ ነፃ ነው:: አንቺማ ምን በወጣሽ የኔ ልጅ:: ልፋቴም ድካሜም እንደዚህ የማዲያት መጫወቻ ሆኜ የወደቀ ጣሳ መምሰሌም እንደዛ እንድትሆኚ አይደለም:: ወላዲት አምላክ ምን አድርጌአት:: እንዲያው መቼም የዛሬ ጊዜ ልጃገረዶች የዲቃላ ነገር ሳንቲካቸው ስለሆነ ምናልባቱን ፈራሁ እንጂ. . . አንቺማ ምን በወጣሽ:: ልጃችን ገና ድል አድርገን ደግሰን በወግ በማዕረግ ድረንሽ ኩለንሽ ነው የምትወልጂው::" አሉ የዘወትር ምኞትና ፍላጐታቸውን እግረ መንገድ እየፎከሩ::

"በእናንተ ጊዜ ዲቃላ የሚወልድ አልነበረም ማለት ነው?" አለች ዳርምየለሽ እናቷ የራሳቸውን የቆየ ጉድ አስቀምጠው የዛሬዎቹን ልጃገረዶች ሲኮንኑ በልቧ ታዝባቸው::

ወ/ሮ ብዙ ውስጣቸውን ቆንጠጥ ቢያደርጋቸውም አፋቸው በሙሉ ልብ የዳርምየለሽን ጥያቄ መመለስ አላቃተውም::

"እረ በፍጹም:: ከእናት ከአባት ቤት ተቀምጦ ልጅ ሊታቀፍ? ምን ሲደረግ::የት ሊገባ? እንዲህ ዓይነቱ ጉድ ባሁኑ ጊዜ የመጣ የእግዚአብሔር ቁጣ ነው:: ልጆቹ ከልጅነት ሳይወጡ ልጅ ይዘው ያለአባት . . ." አሉና እንደበታቸውን ያዝ አርገው እንደገና ሊቀጥሉ ሲሉ ቀደመቻቸው::

"የኔም ጥያቄኮ እሱ ነው::"

"ምኑ?" አሉ ወይዘሮ ብዙ ሳይታወቃቸው እየተቆጡ::

ዳርምየለሽ ካፏ ባፈተለከው ሀሳብ የእናቷን ቁጣ መሰል ጥያቄ ስትሰማ መልሳ ደነገጠች::

"አይ እማዬ፣ ጨንቆኝ ነው::"

"ምኑ ነው የጨነቀሽ?" አሉ ግራ ተጋብተው:: ጥያቄአቸው ቢያስፈራትም ከዚህ የተሻለ አጋጣሚ እንደማታገኝ አስባ ራሷን አደፋፈረች::

"ያባቴ ነገር"

"አባትሽ ምን ሆነ? ከኔ የተደበቀ እና የሰማሽው ነገር አለ?"

"አዎ!"

"ምን ሆኗል አሉሽ? ያንኑ አፈሩን ሲዝቅ ከነትራክተሩ ገደል ገብቶ እንዳይሆን? ንገሪኝ እንጂ ዳርምየለሽ? ባህሩ ምን ሆኗል?" አሉ በድንጋጤ እየተቅበጠበጡ::

"እሱን አይደለም ያልኩሽ?"

"እንዴ! ያማታል እንዴ ልጅቷ! ምንድነው እምታወሪው?"

ድምጿን ዝቅ አድርጋ ጠየቀቻቸው:: "አባቴ ማን ነው?"

"ምን!?" አሉ ግንባራቸው ላይ እንደመብረቅ ብልጭ ብሎባቸውና ግራና ቀኝ ፊታቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው ወደ ኋላቸው እየሸሹ::

"ጆሮ አይሰማው የለ!"

## 23

“ቆይ እንጂ ቡናውን ሳታከትም?” አሉ ወይዘሮ ብዙ ፈጠን ድንገት ተሰናብቷቸው ሲነሳ።

“የለም ልሂድ። አቦሉን ከጠጣሁ ይበቃኛል። እቸኩላለሁ።”

“እሺ ቆየኝ” አሉና ወደ ውስጥ ገቡ።

ፈጠን እቸኩላለሁ ያላቸው ውሸቱን ነው። እንዲያውም ጧት ፍየሏን ለማረድ ሲመጣ ውሉውን ከዚያው አድርጐ ከዳርምየለሽና ከቤተሰቧ ጋር ሊጫወት ነበር ያሰበው። እንደምኞቱ ግን አልተሳካለትም። ፍየሏን አርዶ እንደ ጨረሰ ቁርስ ቀርቦለት አቦል ቡና ላይ እንዳሉ ዳርምየለሽ ከክሳቷ በቀር የጥዋት ጀምበር መስላ ወጣች። ልቡ በቅናት ተናወጠ። ፈገግ ብላ ሰላምታ ስጥታዋለች። አፀፋውን ምላሱ ከጥርሱ እየተማታበት ቢሰጣትም ስትሄድ እያየ መቆየት አልቻለም። ልቡ ‘ተነስ’ አለው። ተከትሏት ምን እንደሚያደርግ ባያውቅም ተነሳ።

“እግዜር ይስጥልኝ ልጄ የዘመድ አውራ ያድርግልኝ።” አሉ ወይዘሮ ብዙ አምስት ባለ አሥር ብር ኖቶችን ይዘው እየተመለሱ።

“ምን?!” አለ ፈጠን ምንነቱ ቢገባውም።

“ገንዘብህን ውሰዳ! . . .”

“ኧረ በፍጹም” አለና አቋረጣቸው። “እኔ አልወስድም። እውን ሰሷ መድሃኒት ከሆን ሌላም ባወጣ ቅር አይለኝ። ይያዙት ላንድ ችግር ይሆንዎታል።” አለ የዘረጉት እጃቸውን እየገፋ።

“ባክህ ያዝ! አንተስ ብትሆን ከየት ታመጣለህ? በዛሬ ጊዜ ሁሉ ነገር ጨው ነው። በቀደምም ይቆይ አልከኝ እንጂ ልስጥህ ነበር።”

“እግዚያብሔርን እኔ አልወስድም። አሁን ይኼ ውለታ ሆኖ ነው? ሰው የሚዛመደው እንዲህ እያለኮ ነው። ይልቅ ደህና ዋሉ።” አለና ጥሏቸው ወጣ።

“እግዚሃር ይስጠው እናቴ። እኔማ ምንተፍረቴን ውሰድ አልኩት እንጂ ገንዘብም አልነበረኝ።” አሉ ወደ ሁለቱ ልጆቻቸው መለስ ብለው።

አስናቀች ሁለተኛውን ልትቀዳ የተጠጣባቸውን ስኒዎች ከዳር ባስቀመጠቻት ሽራፋ ስኒ ላይ ታጫልጣለች። ኑንሽ የዳንቴል መለማመጃ ውጥኗን እያውተበተበች አጠገቧ ተቀምጣለች።



“ደግ ሰውዬ ናቸው” አለች ኑንሽ።

“ደግ እንጂ! የመጨረሻ ደግ። ሦስት ዓመት እኔጋ ሲበላ ምኔን አይቶ ያውቃል? በገዛ ገንዘቡ ነው። እንዲያው ሰው ወዳድ ሆኖ ዝምድና ፈልጐ እንጂ ስሞኑንም እኮ እንደልጄ ከላይ ከታች ሳሮጠው ነው የስነበትኩት።” አሉ በፈጠን ውለታ ልባቸው ተነክቶ።

“ምን አይነት ዝምድና ነው እማዬ? ጋሽ ፈጠንም ሁልጊዜ ዘመዳችን መሆን እንደሚፈልግ ይናገራል።” አለች አስናቀች።

ወይዘሮ ብዙ እስከዛሬ ያላሰቡት ነገር ታያቸውና ከንከን አደረጋቸው። ቢሆንም ግን እንደዛ ሊያስቡትና ሊገምቱት አልፈለጉም።

“ዝምድና ነዋ። ያው የባዳ ዘመድ አለ አይደለም? እንደ ስጋ ዘመድ ቅርብ የሆነ፣ ውለታ እሚሠራ” አሉ በደፈናው። የልጃቸው ጥያቄ ግን ከንክኗቸዋል።

በዚያም አለ በዚህ ሰሞኑን ባለማወቅ ለማይሆን ነገር የከሰከሱት ገንዘብ አንሶ ዛሬ ደግሞ ፍየሏ መድሃኒት እንደማትሆን እያወቁ ቃላቸውን ላለማጠፍ እየቆጫቸው ሊከፍሉት የነበረውን ገንዘብ ስለተወላቸው ተደስተዋል።

“ድሮውንም ወላዲት አምላክ፣ ቸሩ እግዚአብሔር እያሉ ከሰው ደጅ መሄድ ሀጢአት ነው። መቼም ‘ጐሽ ለልጇ ተወጋች’ ነውና ወላዲት አምላክ ጭንቄን ተረድታ ታማልደኝ። ፈጣሪ አምላክ ይቅር ይበለኝ።” አሉና በልባቸው ንስሃ ገቡ። በእማማ ሸዋ ግፊት እንጂ እርሳቸው ቀድሞውንም ለአመብርሃን ስጥተው እንደነበር፣ አሁንም እርሷው እንደፈቀደች እንድታረጋቸው ተናዘዙ። –በልባቸው።

አባ ደርብ ቀጠሮ የሰጧቸው ለዛሬ መሆኑ ትዝ አላቸው። ምን ብለው ሊመልሷቸው ነው? የዳርምየለሽ በሽታ እርሳቸው እንዳሉት ልክፍት አለመሆኑንና ምክንያቱንም አውቀውታል። ደብተራ ሆነ ጠንቋይ ቢደረደር የሌለባትን በሽታ እንደማያድናት፣ ያባ ደርብ መጽሐፍም ልክ እንዳልተናገረ ገብቷቸዋል። ዛሬ ታዲያ ይኼን እያወቁ ቀሪውን ገንዘብ በነፃ ሊስጡ ነው? ለምን? በርግጥ አባ ደርብ እንዳሉቱ ተለክፋ ቢሆን ለልጃቸው መድሃኒት የተባለ እንኳን ገንዘባቸውን ነፍሳቸውን ከፍለው ቢያድኗት ፈቃደኛ ናቸው። ዛሬ ለአባ ደርብ የሚሰጡት ገንዘብ ግን መበስጥ መሆኑ ተሰማቸው። ወደ እርሳቸው የሄዱበትን ቀን ረገሙ። ቡናው ሲያከትም ወጥተው ለመሄድ ወሰኑ። ቀለብተኞቻቸው እሁድ እሁድ ስለማይመጡ ሥራ የለባቸውም።

ሲያሳስባቸው የቆየው የልጃቸው ሁኔታ ከቀን ወደቀን እየተሻሻለ መምጣቱ ‘ተመስገን’ ያሰኛቸውን ያህል ጭንቀቷ ወደ እርሳቸው ተጋብቶ

ሲተክዙ ነው የሰነበቱት:: 'እውነትና ንጋት . . .' ሆነና ምንም ያህል ቢጠነቀቁና ሚስጥራቸውን የጠበቁ መስሎ ቢሰማቸው ሲፈሩትና ሲሸሹት የኖሩት ጥያቄ አልቀረላቸውም:: ምንም ያህል ተንከባክበው ቢያሳድጓት፤ ምንም ያህል ልጅነቷን ከአቶ ባህሩ አባትነት ጋር አያይዘው 'ውሸት ሲለመድ እውነት ይሆናል' እንዲሉ ያህል ራሳቸውን ሳይቀር አሳምነው ለዚህ ቢያደርሷት እርሳቸው ባላወቁት ምክንያትና ባልጠበቁት ጊዜ ሚስጥራቸውን ሰምታ የማን ልጅነቷን እንዲነግሯት አፋጥጣቸዋለች::

የማን ልጅ ይበሏት?

የዚያን ዕለት ጥያቄዋ አስደንግጧቸው፣ ለቅሶና ፍጥጫዋ አስፈርቷቸው ሳይወዱ በግድ እውነቱ፣ ህቁ ቢያንቃቸው የአቶ ባህሩ ልጅ አለመሆኗን አምነውላታል:: ከዚያ ወዲህ ግን ሌት በመኝታ ቀን በቁማቸው የህሊና ረፍት አጥተዋል:: የሚወዷትና አይተው የማይጠግቧት ልጃቸውን ዓይኖች እንደጦር እየፈሩ መሸማቀቅና መሸሽ የእርሳቸው ተራ ሆኗል:: ከቤት ስትሆን ይጨንቃቸዋል:: የሚሠሩት ሁሉ አይሳካላቸውም:: ወጣ ስትል ወይ ደግሞ ጓደኛዋ መጥታ ስትወስዳት አለዚያም ቁጭ ብላ ስታጫውታት ይሻላቸዋል:: በተረፈ ብቻዋን ተቀምጣም ሆነ እየሠራች ዝም ስትል ነገር እየበላች ስለሚመስላቸው ይጨንቃሉ:: ዛሬም አስተካክላ ለብሳና አምሮባት ከቤት ስትወጣ የት እንደምትሄድ ባያውቁም ተቀምጣ ከምታስጨንቃቸው የትም ይሁን የት መሄዷ አስደስቷቸው በልባቸው ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ነው የሸኟት::

"እማዬ ሰው ይፈልግሻል" አለች ኑንሸ መኝታ ቤት ገብተው ሲለባብሱና ለመሄድ ሲዘገጃጁ ሳለ::

"የምን ሽማግሌ ነው እሱ? የለችም በይ!" አሉ ወይዘሮ ብዙ የህሳባቸውን ተቆጥተው::

"አይተሻቸዋል እንዴ? ሽማግሌነታቸውን እንዴት አወቅሽ?" አለች ኑንሸ በመገረም ፈገግ እያለች::

"ኡፍ! እንግዲህ ኑንሼ አታድርቂኝ ማንም ይሁን ማንም የለችም በይ አልኩሽ የለችም በይ::"

"እንዴ እማዬ ለምን? አለች ብያቸዋለሁ"

"ቀዥቃዣ! ምን አስቀባጠረሽ? እስቲ ቆይ ልያት አይባልም! መቼም አንቺ ወንጀል ሠርቼ ብደበቅ መንጥቀሽ ታስይዢኛለሽ" ለራሳቸው በልባቸው ያሰቡትን ከአባ ደርብ የመደበቅ ጉዳይ ልጃቸው እንደ ማታውቅ ሳያገናዝቡ ተማረሩባት::

"እንዴ እማዬ ምን አስቆጣሽ? ፖሊስ እኮ አይደሉም:: ቄስ ነው የሚመስሉት:: ከፈለግሽ በመስኮት እያቸው::" አለች ኑንሼ ቁጣቸው ግራ አጋብቷት::



"ኧረ አይንሽን ያጥፋው እቴ! ጭቅጭቅሽን ተይና የለችም በይ!" አሉ ይበልጥ ተቆጥተው::

በድንጋጤ ተሸማቅቃ ቀስ እያለች ስትወጣ ጠሯትና ህሳባቸውን ቀየሩ:: ዛሬ የለችም ቢያሰኙ ሌላ ቀን መምጣታቸው እንደማይቀር ገመቱ::

"ግቡ በያቸው" አሉ እየተበሳጩ::

አባ ደርብ በሴት ተይዘው ካገራቸው ከተሰደዱ በኋላ ያፈረሱትን ቅስና ትተው እንደዋዛ መነኩሴ ለመምሰል ራሳቸው የደፉትንና 'አባ' ያሰኛቸውን ቆብ ከራሳቸው ለይተው አያውቁም:: አሁን ያደረጉት ቡናማ ቆብም አዲስ አበባ በቆዩበት ሰላሳ አንድ አመት አራተኛቸው ነው:: ቆብ የደፋው ጭንቅላታቸው 'ሙሉ' ልብሳቸውን ሲለብሱ ከማነሱ የተነሳ በማይታይ አንገታቸው ላይ የተዋቀረ አካል ሳይሆን ከወገብ በላይ እስከትከሻቸው በልብስ በተከመረ ሰውነታቸው ላይ ቁጭ የተደረገ ባዕድ ነገር ይመስላል:: እርጅና ወደፊት ያጣመመው ስፊ ትከሻቸው ላይ ወፍራም ጋቢ ደርበዋል:: ከጋቢው ሥር አሮጌ ካፖርት፣ ከካፖርቱ ሥር ኮት፣ ከኮቱ ሥር ካኪ እጀ ጠባብ፣ ከእጀ ጠባቡ ሥር ወፍራም ሹራብ፣ ደሞ ሌላ ስስ ሹራብ፣ ቀዳዳ ሸሚዝ፣ ሁለት ካኒተራ መልበሳቸውን የሚያውቅ ቢኖር እንደ ሳጥን የልብስ ማስቀመጫ እንጂ እንደሰው ልብስ ለባሽ መሆናቸው ሳያጠራጥረው አይቀርም:: ወይንም ደግሞ ያን ሁሉ ልብስ ተሸክመው በጠራራ መቀቀላቸው ተስምቶት በተሳቀቀ ነበር:: ደግነቱ የላይኛው ማጣፊያ ጋቢ በመሆኑ ከካፖርታቸው በቀር የተሸከሙትን ጉድ የሚያውቅ የለም:: የገብርኤል ሠፈር ልጆች ብቻ በዚያ ረዥም ቁመና ከወገብ በላይ ተከምረው ሲያዩዋቸው "አባ ተራራው" እያሉ ያበሽቋቸዋል::

ወይዘሮ ብዙም አባ ደርብ እንዲያ ተቆልለውና ከወደ እግራቸው ተመልምለው ሲያዩዋቸው ከጉልበታቸው እንዳይቀነጠሱ ፈሩላቸው:: ያን ቀን እቤታቸው ያዩአቸው አባ ደርብ መሆናቸውን ተጠራጠሩ:: ገጽታቸው ግን ይለያል::

"ይምጡ እዚህ ይቀመጡ" አሏቸው ፊታቸውን እንዳጠቆሩ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ መጋረጃውን ገልጠው ወደ ባለ ሦስት መቀመጫው ሶፋ እየመሯቸው::

"እዚህ ይበቃኛል" አሉ አባ ደርብ ከዘራቸውን ተጭነው ቀድመው ያገኙት ባለ አንድ መቀመጫ ሶፋ ላይ እየተቀመጡ::

ወይዘሮ ብዙ ለአሮጌ ሶፋቸው ቢያዝኑም ይሉኝታ ይዟቸው ዝም አሉ::

"ብቻሁን ማን አሳየዎት ቤቱን?"

"ራሲው መጣኋ! አመላክተውኝ አልነበር? አያሳስትም:: ተሸዋ

ቤት የርስዎ መንገድ ዳር ነው::" አሉ አባ ደርብ በጭራቸው ወደ መውጫው እያመለከቱ::

"እሱስ እም!" አሉ ወይዘሮ ብዙ ብሽቀታቸው የሚያወሩትን አሳጥቷቸው::

ቡና አፍልተው እስኪጨርሱ ባለው ጊዜ ሁሉ አሁን ካሁን ስለ ልጃቸው አንስተው ጽሕፈቱን ይጠይቁኛል ብለው ቢጠብቁም የወይዘሮ ብዙ ችላ ማለትና ሌላ ሌላውን ማውራት ሲገርማቸው ቆይቶ አቦሉ እንደወረደ ራሳቸው አነሱት::

"እንዳው ያቺ ልጅ ተሻላት? ሰሞኑን መጥቼ ፀሎት አደርሳለሁ ብዬ ነበር ሳይመቸኝ ቀረ:: በባሉም ቅዳሴ ዝክር ስል ባዘቦቱም ከተማሮቹ ስዳረቅ አላደርስ አለኝ::"

"ደህና ናት:: ምን ይመቻል ብለሁ ነው" አሉ ወይዘሮ ብዙነሽ ባጭሩ::

"ብራናውንም ለማግኘት ሁለት ቀን የማስተምራቸውን ልጆች ዘግቼ ነው:: ለመጻፍ ደግሞ. . ." ብለው ድካማቸውን ሊዘረዝሩ ሲሉ አቋረጧቸው::

"እንዲያው ለማይሆን ነገር ስንቱን አስቸገርኩኝ:: እርስዎንም አደከምኩዎት::"

"እንዴት?! አልተሻላትም እንዴ? አሁን ይኼን ስታስር ድራሹ ይጠፋል:: የታባቱ ይኸ አረመኔ::" አሉ አባ ደርብ እጃቸውን በጋቢያቸው ስር አስገብተው ወደ ካፖርታቸው አልፈውም ወደ ኪታቸው እያሹለከለኩ::

"መሻልስ ተሽሏታል:: ይክበር ይመስገን ፈጣሪዬ ደህና ሆና ነው የለነበተችው::"

አባ ደርብ ለልጅቷ መዳን የእርሳቸው ውለታና ድካም ወደ ጉን ቀርቶ ምስጋናው ለእግዚአብሔር ብቻ የመድረሱ አዝማሚያ አላማራቸውም:: በገዛ ፈጣሪያቸው መቅናታቸው ተሰማቸውናም::

"ተመስገን ነው እንጂ! ሁሉስ ቢሆን በርሱ ሀይል አይደለ:: ከእርሱ በላይ ማን አለና!" አሉ በልባቸው የገቡትን ሀጢአት በአፋቸው እያስተባበሉ::

ከኮታቸው ኪስ ያወጡትን በቆዳ የተሠራ ክታብ በማንገቻው አንጠለጠሉና "እነሆ ይኼን ትሰር:: ስለቱም ፀሎቱም እንዳይረሳ:: ይኼን ካሠረች ባጠገቧ ዝር የሚል ነገር የለም::" አሉ::

"አባ እንዲያው ነው ያደከምኩዎት::" አሉ ወይዘሮ ብዙ ምን ብለው እንደሚቃወሙ ጭንቅ ብሏቸው:: "መቼ. . . የሷ በሽታ እኛ እንደገመትነው አልሆነም::"

"የምን ግምት አመጡ እሜቴ!? መጽሐፉ የሚናገረውን!" አሉ አባ ደርበው ያፈረ እጃቸውን መልሰው ገጽታቸው ቅሬታን እያስነበበ::



"እግዜር ይስጥልኝ አባ! እርስዎማ የበኩልዎን ደክመውልኛል::"

"እና አሁን በሽታዋ ምንድነው ነው የሚሉኝ?"

"ሌላ ሆኖ ተገኘ"

"ምን የሚባል? መቼም ተኔ ወዲያ ደብተራ ላሳር ነው:: ሌላ ሰው አስገልጠውላት ነበር እንዴ?"

"እረ የትም አልሄድኩኝ"

"እንግዲያው በምን አወቁ?"

"እራሷው ነገረችኛ፣ ጭንቀት ነው በሽታዋ"

"ምን የሚሉ ጭንቀት አመጡ! ይርባታል ወይስ ይጠማታል? እርስዎን የመሰሉ ለእግዜር ለሰው የከበዱ ደርባባ እናት እያሏት:: የምን ጭንቀት ነው?" አሉ አባ ደርብ እየካቡ ለማግባባት::

"ራብ ጥማትስ የለባትም:: ይመስገን ነው ለፈጣሪ፤ ልፋት እንጂ የኑሮ ችግር የለብኝም:: እሷም ብትሆን እኔ እናቷ እስካለሁ የሚጐላት ነገር የለም::"

"እንግዲያው ከሜዳ ጭንቀት የለም::"

"ከሜዳ እንኳን አይደለም"

"የለም የለም ምናምን ተጠግቷት ነው" አሉ አባ ደርብ ከወይዘሮ ብዙ አፍ ነጥቀው::

"እየነገረችኝ?"

"ምኑን?"

"የሚያስጨንቃትን:: እህል አላስበላሽ እንቅልፍ አላስተኛሽ ብሏት ከለው ነጥሎ ሲያስለቅሳት የሰነበተውን ሁሉ አንድ ባንድ እኮ ነው ዝርዝር አድርጋ የነገረችኝ::"

"ይኸውልኋ! ራሷን ካናገራትማ ከዚህ በላይ ምን ይፈልጋሉ ወትሮስ ቢሆን ጋኔን እራሱ አይመጣ:: በላይዋ ላይ ሠፍሮ ያናግራታል እንጂ::" አሉ አባ ደርብ ያልተዛነፈ ቆባቸውን እያስተካከሉ::

"አይደለም ስልዎት አባ! ያስጨነቃትን እኮ እሷ ባለችው ብቻ ሳይሆን እኔም ራሴ አውቄላታለሁ::" አሉ ወይዘሮ ብዙ የሸማግሌው ውትወታ ትዕግሥታቸውን አስጨርሷቸው::

"እንግዲያው ምንድን ነው አለችዎ?"

"የቤት ጉዳይ ነው::"

"ለቤቱ ጣጣማ የሚሆነውን ሁሉ ነግሬዎ የለም እንዴ?"

"እርሱ አይደለም:: የቤተሰብ ሚስጥር ነው ማለቴ ነው::"

"እረ!. . ." አሉ አባ ደርብ ነገር እንደገባው ሰው ጆሮአቸውን አቁመው ምላሳቸውን እያፍታቱ:: "መቼም የዛሬ ዘበን ልጆች ትንሽ ከፍ ካሉ ሚስጥራቸው ብዙ ነው:: እኔኮ ያን ቀንም መቼም እናት በመሆንዎ ቅር ይልዎታል ብዬ እንጂ ልነግርዎ ነበር::"

"ምኑን?"

"ዘር እንደያዘች መጽሐፉ ነግሮኝ ነበር::"

"ኡ! . . . አባ! እረ በስመአም በሉ! እረንሽ ብዙነሽ! የሰው ልክ

አለማወቅ:: የማን ልጅ መሰለችዎት? የኔ ልጅ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ውላበትም አታውቅ:: የታረመች የተቀጣች ጨዋ ናት:: ምነው አባ! እሷ ከመጽሐፍና ከእጅ ሥራ በቀር እንዲህ ዓይነቱን ቅሌት አታውቀውም::"

"ምነው እሜቴ አይቆጡ እንጂ ታዲያ:: እኔኮ መጽሐፉ ያለውን እንጂ እሜት አይደለ::" አሉ አባ ደርብ ለሁለተኛ ጊዜ በሀፍረት ተሽማቀው::

"አይ ምነው! የርሶ መጽሐፍ ደሞ በዛ::" አሉ ወይዘሮ ብዙ ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ ውስጥ እየተሽቀነጠሩ:: እንደ ንዴታቸው ቢሆን አባን ዘለው ቢያንቋቸው አለዚያም የጣዱትን ጀበና አናታቸው ላይ ቢፈረክሱት አይወጣላቸውም:: ሆኖም የውሽትም ቢሆን የደፉትን ቆብ በተሰይም እግዚአብሔርን ፈርተው ትተዋቸው ወደ እቃ ቤት ገቡ:: እዚያ ግን የሚሠሩትም ሆነ የሚፈልጉት ነገር አልነበረም::

አባ ደርብ ከወይዘሮ ብዙ አነጋገር እና ሁኔታ ቋምጠውና ጓጉተው እጃቸው ሳይገባ ለጉዳይ ያደላደሉትን ገንዘብ እንደማያገኙ ቁርጣቸውን አወቁ:: ይልቁንም ለማግባባት ሲሉ የዘባረቁት ውሸት አሳፍሯቸው ከተቀመጡበት ሲነሱ ወይዘሮ ብዙ ተመልሰው ብቅ አሉ::

"ይቆዩ እንጂ አባ ይቀመጡ" አሉ ካንገት በላይ በሆነ አነጋገር::

"የለም የለም እሄዳለሁ::" አሉ ማኩረፋቸው እያስታወቀባቸውና በቆሙበት እያመነቱ::

ወይዘሮ ብዙ መሀረባቸውን ከጡታቸው ሥር አውጥተው ሲፈቱ የአባ ደርብ ፊት ፈካ ማለት ጀመረ::

"ገንዘቤንስ ተሰጡኝ የራሳቸው ጉዳይ" አሉ በልባቸው::

"ይኸው:: እግዜር ይስጥዎት" አሉ ወይዘሮ ብዙ የመወርወር ያህል ድፍን አምስት ብር እያስጨበጧቸው::

"እረግ! ይኼንሳ ምን ላድርገው?" አሉ በእጃቸው ያንጠለጠሉትን ክታብ እያሳዩአቸው:: በአምስት ብር ለመስጠት እንደማይፈቅዱ ልባቸው ያውቀዋል::

"እሱንማ ለሌላ ሰው ይሆንዎታል:: እኔ አልወስደውም::"

"ያንዱ ለአንዱማ መች ይሆናል:: ለዚያውስ ስንት ደክሜ መስለዎ ያዘጋጀሁላት::"

"ምን ይሆናል? ውድ የሚያደርገው ብራናው ከሆነ ጽፈቱን ቀይሮ ለሌላ ሰው ማድረግ ነው::"

ቅር እንዳላቸው ቆባቸውን እየነካኩ ከዘራቸውን አስቀድመው ወጡ::

"እጭበርባሪ" አሉ ወይዘሮ ብዙ ለራሳቸው አባ ደርብ የአጥሩን በር ሲሾልኩ ከቤታቸው በር ቆመው በትዕዝብት እየሸኙአቸው::



"ድሮም እኔ ጠንቋይና ደብተራ አይሆነኝ:: ለሚሰግዱለትና ለሚያፈነድዱለት እንጂ እንደኔ ፈጣሪውን ለሚፈራ መች ይሆናል::" ብለው አሰቡ::

"የሰይጣን ሥራ" አሉና በድምጽ አወገዙት::